

# THE STATE and REVOLUTION

V. I. LENIN

# መንግስት እና አብዮት

ቪ. አይ. ሌኒን

# መ ን ግ ስ ት

## እ ና

# አ ብ ዮ ት

ትርጉም

በወንድማገኘሁ [ሊበን

1969

proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com



## ለመጀመሪያ እትም መግቢያ

የመንግስት ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ በቲዎሪም ሆነ በተግባራዊ ፖለቲካ የተለየ ከፍተኛ ስፍራ እያገኘ በመሄድ ላይ ነው ። የኢምፔሪያሊስቱ ጦርነት የሞኖፖል ካፒታሊዝምን ወደ መንግስት ሞኖፖል ካፒታሊዝም መለወጥ በሃይል አፋጥኖ አፋፍሞታል ። ሃይለኛ ከሆኑት የካፒታሊስት ማህበሮች ጋር በበለጠ በመቀላቀል ላይ ያለው መንግስት የሚፈፅመው አስከፊው የሰፊው ለፍቶ አደር ህዝብ ጭቆና ከመቼውም የበለጠ አስከፊና አሳፋሪ እየሆነ ነው ። የለሙት አገሮች ለሰራተኞቹ ወደ ወታደራዊ የፍርድ ወህኒ ቤቶች እየተለወጡ ነው ፣ ይህም « ደጀናቸውን » ማለታችን ነው ።

የተራዘመው ጦርነት ታይቶ የማይታወቅ ስቃይና ችግር የሰፊውን ህዝብ ሁኔታ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ በማድረግና ቅዋሜውንም በመጨመር ላይ ነው ። አለም አቀፍ የወዛደሮች አብዮትም በግልፅ በመብሰል ላይ ነው ። ከመንግስቱም ጋር ያለው ግንኙነት ጥያቄ ተግባራዊ ተፈላጊነት እያገኘ ነው ።

በመጠኑም ቢሆን በነበረው የአስር አመታት የሰላም እድገት ጊዜ የተጠራቀሙት የአድርባይነት ንጥረ ነገሮች በመላው አለም ይፋ የሆኑትን የሶሻሊስት ፓርቲዎችን የተጫጫነውን የሶሻል ትምክህት አዝማሚያእን ዲፈጠር አድርገዋል ። በቃላት ሶሻሊዝም እና በተግባር ግን ትምክህት የሆነው አዝማሚያ (ፔሊካኖቭ ፣ ፓትሬሶቭ ፣ ከሬሸኰቭስካዬ ፣ ሩባኖቪች ፣ እንዲሁም በትንሹ በተሸፈነ መንገድ ፣ እነ ሰርቴሌ ፣ ቼርኖቭ እና ጓደኞቹ ፣ በሩሲያ ፤ ሽድማን ፣ ሌጅዬን ፣ ዴብድ እና ሌሎች በጀርመን ፤ ኖሙኖድል ፣ ባንደርቤልድ ፣ በፈረንሳይና

በቤልጅየም ፤ ሄድማንና ፋብያንስ 2 በእንግሊዝ ወዘተ ወ
ዘተ)በቃል ሶሻሊዝም በተግባር ትምክህተኝነት የሚታወ
ቀው «በሶሻሊዝም መሪዎች» ወራዳና «እራሳቸው» ብሄ
ራዊ ቡርዧዎች ጥቅም ማገልገል ብቻ ሳይሆን «ለራሳ
ቸው» መንግስትም ፍላጐት ማገልገል ነው ምክንያ
ቱም እያሌ ትናንሽና ደካማ ብሄረሰቦች ለረጅም ጊዜ
ሀያል በሚባሉት አገሮች ይገዙና ይበዘበዙ ነበርና ።
እናም በእርግጥ የኢምፔሪያሊስት ጦርነት የዚህ አይ
ነቱን ጥቅም ደጋግሞ የመከፋፈያ ጦርነት ብቻ ነው ።
በአጠቃላይ ከቡርዧውና በተለይም ከኢምፔሪያሊስት
ቡርዧው ተፅእኖ ሰፊው ለፍቶ አደሩን ህዝብ ነፃ ለማ
ውጣት የሚደረገው ትግል ስለ «መንግስት» የአ
ድርባይን እምልእኮ ሳይታገሉ ነፃ ለማውጣት አይ
ቻልም ።

ከሁሉም መጀመሪያ ስለ መንግስት የማርክስንና
የኤንግልስን ትምህርቶች በመመርመር በተለይም ተረ
ስተው በነበሩትና ወይም በአድርባይነት የተጣመመ
ትርጉም እንዲያገኙ በተደረጉት የትምህርት ሁኔታዎች
ላይ እናተኩራለን ። ከዚያም በአሁኑ ጦርነት የሚያሳዝን
ውድቀት ያጋጠመው የሁለተኛው ኢንተርናሽናል
(1889—1914) የታወቀው መሪና በተለይ ለተጣመሙት
ትርጉሞች በይበልጥ ሃላፊነት ባለበት በካርል ካውት
ስኪ ላይ እናተኩራለን ። በመጨረሻም የ1905ቱንና
በተለይም የ1917ቱን የሩሲያን አብዮቶች ልምድ
ዋና ውጤቶች በአጭሩ እናጠቃልላለን ። ሁለተኛው
አሁን (ነሀሴ 1917 መጀመሪያ) የመጀመሪያውን የእድ
ገት ደረጃውን በመፈፀም ላይ ያለ ይመስላል ። ነገር ግን
ይህ አብዮት በጠቅላላው መታወቅ ያለበት በኢምፔሪ
ያሊስቱ ጦርነት የተቀሰቀሱ ተከታታይ የሆኑት የሶሻ



ሊስት ወዛደራዊአብዮቶች ማያያዣ በመሆኑ ነው ።ስለ
ሆነም ወዛደራዊ የሶሻሊስት አብዮት ከመንግስት ጋር
ያለው ግንኙነት ጥያቄ የሚያገኘው ተግባራዊ የፖለቲካ
ከፍተኛ ስፍራ ብቻ ሳይሆን የጊዜው አስቸኳይ ፕሮብ
ሌም የመሆን ከፍተኛ ቦታንም ነው ፤ ይህም ሰፊው
ህዝብ ራሱን ከካፒታሊዝም ቀንበር ነፃ ለማውጣት
በቅርቡ ምን ማድረግ እንዳለበት የማስረዳት ችግር ነው።

ነሐሴ 1917

ደራሲው




# ለሁለተኛው እትም መግቢያ

የአሁኑ ፡ ሁለተኛው እትም ፡ አንቀፅ 3 በምእራፍ 2 ውስጥ ከመጨመሩ በስተቀር የታተመው ምንም ያህል ለውጥ ሳይደረግበት ነው ።

ሞስኮ

ታህሳስ 17/1918

ደራሲው






ምዕራፍ 1

## የመደብ ህብረተሰብና መንግስት

1. መንግስት እንደ የማይታረቁ የመደብ ቅራኔዎች ውጤት

በአሁኑ ጊዜ በማርክስ ትምህርቶች ላይ የሚደርሰው ነገር በታሪክ ውስጥ በሌሎችም አብዮተኛ ፈላስፋዎችና ለጭቁን መደቦች አርነት በታገሉት መሪዎች ትምህርቶች ላይ ደጋግሞ የደረሰ ነው ። ታላላቅ አብዮተኞችን በህይወት ባሉበት ወቅት ጨቋኝ መደቦች ባለማቋረጥ ያሳድዳቸዋል ። የሚያስተምሩትንም አረመኔአዊ በሆነ ክፋት ፡ በጣም በጋለ ጥላቻና ከመጠን በላይ ወራዳ በሆነ የውሸትና የስድብ ዘመቻ ይቀበሉታል ። ከሞቱ በኋላ እነሱን ጉዳት ወደማያመጡ ምስሎች ለመለወጥ ፡ ቅዱሳን ለማድረግ ሙከራ ይደረጋሉ ። የተጨቆኑት መደቦችን ለማታለል እንዲመችና እነርሱንም «ለማፅናናት» ስማቸውን በአንድ አይነት ግርማ ሞገስ ቢከቡም በዚያኑ ጊዜም የአብዮታዊ ቲዎሪያቸውን ፡ እውነተኛ ይዘት በማኰላሸትና በማበላሸት አብዮታዊ ስለቱን ያደነዝዙታል ።

በአሁኑ ጊዜ ቡርዧዎችና ከወዛደሩም መደብ ንቅናቄም መሃል አድርባዮች ማርክሲዝምን ለማርክስ በሚደረገው በዚህ አይነት ሙከራ ተካፋዮች ሆነዋል ። የዚህን ትምህርት አብዮታዊ ጐን ፡ አብዮታዊ ህይወቱን ይዘላሉ ፡ ይደመስሳሉ ፡ ያጣምማሉ ። በቡርዧዎች ተቀባይነት ያለውን ወይም ያለው የሚመስላቸውን ብቻ ይደግፋሉ ፡ ያጋንናሉ ። ሶሻል ትምክህተኞቹ ሁሉ አሁን «ማርክሲስት» ናቸው (አትሳቁ!) ማርክሲዝምን ድራሹን ለማጥፋት ትናንት የተለየ ጥበብ የነበ

ራቸው የጀርመን ቡርዧ ፕሮፌሰሮች ደጋግመው በማዘ ውተር « የጀርመን ዜጋ » የሆነው ማርክስ የዘረፋ ጦር ነት ለማድረግ በሚገባ የተደራጁትን የሰራተኞች ማህ በራትን ያስተማራቸው እሱ ነው እያሉ ያስተጋባሉ !

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፣ የማርክሲዝም መጣመም ታይ ቶ በማይታወቅ ደረጃ በሰፊው በመሰራጨቱ ምክንያት ዋናው ተግባራችን ማርክስ በትክክል ስለመንግስት ያስተማረውን እንደገና ለመመስረት ነው ። ይህን ለማ ድረግ ከማርክስና ኤንግልስ ሥራዎች በሰፊው መጥ ቀስ አስፈላጊ ነው ። እርግጥ ነው ጥቅሶቹ ፅሁፉን ትልቅ ስለሚያደርጉት ለማንበብ ምቹ እንዲሆን አይ ረዳም ፣ ነገር ግን ይህን ማስወገድ አይቻልም ። ለአን ባቢው ስለ ሳይንሳዊ ሶሻያሊዝም መስራቾች ጠቅላላ አስተያየቶችና እነዚህም አስተያየቶች እንዴት እንደ ዳበሩ ደግሞም አሁን በሰፈነው « በካውትስኪዝም » እንዴት እንደተጣመሙ በማስረጃ ለማረጋገጥና በግ ልፅ በማሳየት የራሱን አሳብ ለመመስረት እንዲችል ማርክስና ኤንግልስ ስለመንግስት ከፃፉት በጣም አስፈ ላጊ ከሆኑት ቁምነገሮች የተቻለውን ያህል ሙሉ በሙ ሉና ካለመሰልቸት መጠቀስ አለበት ።

## የቤተሰብ ፣ የግል ሃብትና የመንግስት አጀማመር ፤

በተሰኘው የኤንግልስ ፅሁፍ እንጀምር ፣ የዚህ ፅሁፍ ስድስተኛው እትም በስቱትጋርት ገና በ1894 ታትሞ ነበር ። የሩሲያዎች ትርጉሞቹ ምንም እንኳን አያሌ ቢሆኑም አብዛኛውን ጊዜ ጉዶሎ ወይም በጣም የማ ያጠግቡ በመሆናቸው ጥቅሶቹን ከመጀመሪያው የጀ ርመን ፅሁፍ መተርጎም አለብን ።



የታሪክ ትንታኔውን በማጠቃለል ኤንግልስ እንዲህ ይላል ፤

"ስለዚህ ፣ መንግስት በህብረተሰብ ላይ ከውጭ በሃይል የተጣለ ስልጣን አይደለም ፤ ሄግል እን ደሚለውም "የሞራላዊ ሀሳብ እውነታ" "የም ክንያት ምስልና እውነታ" አይደለም ። ነገር ግን ህብረተሰብ በአንድ የእድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ የሚያስገኘው ነው ፤ ይህም ህብረተሰቡ ከእራሱ ጋር ሊወጣው በማይቻለው ቅራኔ ውስጥ መግባ ቱን ፣ ሊታረቁ በማይችሉ ተፃራሪዎች ፣ የሚጋጭ የኤኮኖሚ ጥቅም ያላቸው መደቦች ፣ ራሳቸው ንና ህብረተሰቡን ፍሬ ቢስ በሆነ ትግል እንዳይ ደመስሱ ለስሙ ከህብረተሰቡ በላይ የሆነ ስል ጣን ግጭቱን ለማብረድና ስርአት ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ፤ ይህም ስልጣን ከህብ ረተሰቡ መሀል የወጣ ነገር ግን ራሱን ከበላዩ ያደረገና እያደረ እራሱን እየነጠለ የሄደው መን ግስት ነው » (ገፅ 177—78 ስድስተኛው የጀ ርመን ቋንቋ እትም)[3]

ይህ ማርክሲዝም ስለ መንግስት ታሪካዊ ሚናና ትርጉም ጥያቄ ያለውን መሰረታዊ አስተሳሰብ እንከን በሌለው አኳኋን ግልፅ አድርጎ ያስረዳል ። መንግስት የማይታረቁ የመደብ ተፃራሪዎች ውጤትና ምልክት ነው ። መንግስት የሚፈጠረው የመደብ ተፃራሪዎችን ነባራዊ በሆነ መንገድ ማስታረቅ በማይቻልበት ቦታና ሁኔታ ነው ። እናም ፣ በሌላ መንገድ ፣ ደግሞ ፣ የመንግስት መኖር የመደብ ተፃራሪዎች ሊታረቁ እን ደማይችሉ ያረጋግጣል ።

ልክ ከዚህ በጣም አስፈላጊና መሰረታዊ በሆነ ነጥብ ላይ ነው የማርክሲዝም ፍልስፍና ፤ በሁለት ዋና ዋና አቅጣጫዎች ፤ መጣመም የጀመረው ።

በአንድ በኩል ፤ የቡርዧው በተለይም የንኡስ ከበርቴ ርእዮተ አለም አፈቀላጤዎች በማያከራክረው የታሪክ ሃቅ ክብደት የተነሳ መንግስት የሚኖረው የመደብ ተፃራሪዎችና የመደብ ትግል በአለበት ቦታ ብቻ መሆኑን ቢያምኑም ፤ መንግስት መደቦችን ለማስታረቅ የሚያገለግል አካል እንደሆነ በማስመሰል ማርክስን « ያርሙታል » ። እንደ ማርክስ ከሆነ ፤ መደቦችን ማስታረቅ የሚቻል ነገር ቢሆን ኖሮ መንግስት ሊመጣ ካለመቻሉም በላይ እራሱን ለማቆየትም ባልቻለ ነበር ። እንደ ንኡስ ከበርቴዎች ሃሞተ-ቢስ ፕሮፌሰሮችና የማስታወቂያ ሰዎች ከሆነ ደግሞ መንግስት መደቦችን የሚያስታርቅ ይመስላል ። ይህንንም ለማሳመን አዘውትረው በሰፊው ከማርክስ ይጠቅሳሉ ። ማርክስ እንዳስተማረው መንግስት የመደብ አገዛዝ አካል እና አንዱ መደብ ሌላውን የሚጨቁንበት አካል ነው ። በመደቦች መሃል ያለውን ግጭት በማብረድ «ስርአት» ለመፍጠርና ጭቆናን ህጋዊና ነዋሪ ለማድረግ የተፈጠረ ነገር ነው ። በንኡስ ከበርቴ ፖለቲከኞች አስተያየት ፤ ስርአት ማለት አንዱ መደብ ሌላውን የሚጨቁንበት መሆኑ ቀርቶ ፤ መደቦችን ማስታረቅ ማለት ነው ፤ ግጭቶችን ማብረድ ማለት ቅራኔዎችን በማስታረቅ እንጂ ተጨቋኙ መደብ ጨቋኞቹን ሊገለብጥበት የሚያስችለውን መሳሪያና መንገድ ማሳጣት ማለት አይደለም ይላሉ ።

ለምሳሌ ፤ በ1917 አብዮት ወቅት ፤ የመንግስት አስፈላጊነትና ሚና ወዲያውኑ ሰፋ ባለ ደረጃ በድር



ጊት መመለስና ሙሉ ክብደት ያለው የተግባር ጥያቄ ሆኖ ቢቀርብ ፤ ወዲያውኑ ሁሉም ሶሺያሊስት አብዮተኞችና ሜንሸቪኮች “መንግስት” መደቦችን « ያስታርቃል » ወደሚለው የንኡስ ከበርቴ ቲዎሪ ሙሉ በሙሉ ሰመጡ ። የእነዚህ ሁለት ፓርቲዎች ፖለቲከኞች ቁጥር ስፍር የሌላቸው ውሳኔዎችና ፅሁፎች በዚህ በንኡስ ከበርቴ ሀሞተቢስ «የአስታራቂነት » ቲዎሪ ሙሉ በሙሉ ተሞልተዋል ። መንግስት የአንድ የተወሰነ መደብ ሊታረቀው የማይችለውን ተፃራሪ (ለርሱ ተቃራኒ የሆነውን መደብ) የሚገዛበት አካል መሆኑን የንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች መቼም ሊገባቸው አይችልም ። ስለመንግስት ያላቸው አስተያየት የእኛ ሶሺያሊስት አብዮተኞችና ሜንሸቪኮች ከቶ ሶሺያሊስት ፤እንዳልሆኑ (ይህን ነጥብ እኛ ቦልሸቪኮች ዘወትር የምንለው ነው ) ነገር ግን ወደ ሶሺያሊስት የሚጠጉ ሀረጎች የሚጠቀሙ ንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች ብቻ ለመሆናቸው በጣም የጐላ ማረጋገጫ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ «ካውትስካይቶች» የማርክሲዝም ፍልስፍና ሲያወላግዱ በጣም ጮሌ ናቸው ። በ« ቲዎሪ» መንግስት የመደብ አገዛዝ አካል መሆኑን ወይም ደግሞ የመደብ ተፃራሪዎች ሊታረቁ እንደማይችሉ አይካድም ። ነገር ግን የሚታለፈውና የሚድበሰበሰው ይህ ነው ፤ መንግስት ሊታረቁ የማይችሉ የመደብ ተፃራሪዎች ውጤት ከሆነ ፤ ራሱን ከህብረተሰብ በላይ የሚያቆምና «እራሱንም እያደር በይበልጥ እየነጠለ የሚሄድ » ስልጣን ከሆነ ፤ የተጨቋኙ መደብ ነፃ መውጣት ካለ የአመፅ አብዮት የማይቻል ነገር ከመሆኑም ሌላ ፤ በገዥው መደብ የተፈጠረውና የዚህ « መነጠል » መንስኤ የሆነውንም የመንግስት የስል

ጣን መሳሪያ ካልተሰባበረ የማይቻል መሆኑ ግልፅ
ነው ። በኋላ እንደ ምንመለከተው ፣ ማርክስ ይህን
በእራሱ ግልፅ ከሆነው መደምደሚያ ላይ የደረ
ሰው ስለ አብዮቱ ተግባራት ተጨባጭ የሆነ ታሪካዊ
ትንታኔ በማድረግ እንደሆነ በጣም ግልፅ ነው ። እናም
እኛ ወደፊት በዝርዝር እንደምናሳየው ካውትስኪ . . .
«የረሳውና»ያጣ መመው ልክ ይህንኑ መደምደሚያ ነው።

2. የታጠቁ ሰዎች ፣ እስር ቤቶች ፣ ወዘተ
የተለዩ አካሎች

ኤንግልስ በመቀጠል ፣

«ከጥንቱ ቤተ ዘመድ (ነገድ ወይም ጎሳ) ድርጅት
ጋር ሲነፃፀር ፣ የመንግስት መጀመሪያ መለያ
ፀባዩ ዜጎቹን በግዛት መከፋፈሉ ነው ። »

የዚህ አይነቱ መከፋፈል ለኛ «የተለመደ» ይመስለ
ናል ፣ ነገር ግን በጥንቱ የቤተ ዘመድና ጎሳ ህብረተሰብ
ጋር ረዥምና ከባድትግል ከተደረገ በኋላ የመጣ ነው ።
« ሁለተኛው የተለየ ጠባዩ ህዝቡ ራሱን እንደ
ጦር ሃይል ከማደራጀቱ ጋር በቀጥታ የማይመሳ
ሰል የመንግስት ስልጣን መመስረቱ ነው ። ይህ
ልዩ የመንግስት ስልጣን አስፈላጊ የሆነው በመ
ደብ መከፋፈል ከመጣ ወዲህ በራሱ የሚሠራ
የታጠቁ የህዝብ ድርጅት የማይቻል ነገር በመ
ሆኑ ነው ። . . . ይህም ህዝባዊ ስልጣን በማንኛ
ውም መንግስት ስር ይገኛል ፤ የሚይዘው የታጠቁ
ሰዎችን ብቻ ሳይሆን የቤተ ዘመድ (የጎሳ) ህብረተ
ሰብ ከቶ የማያውቀውን የማቴርያል ተቀጥላዎ
ችን እስር ቤቶችንና ልዩ ልዩ የማስገደጃ ተቋ
ሞችን ነው » ።



ኤንግልስ መንግስት ተብሎ ስለተሰየመውና ከህ
ብረተሰብ ስለወጣውና እራሱን የበላይ በማድረግ ቀስ
በቀስ እየተነጠለ ስለሄደው « የሀይል » ፅንስ ሃሳብ
በተጨማሪ ያብራራል ። ይህ ሀይል ምንን በይበልጥ
ይይዛል ? እስር ቤቶች ፣ ወዘተ . . በቁጥጥራቸው ስር
ያላቸውን የታጠቁ ሰዎች ልዩ አካሎችን ይይዛል ።

የመንግስቱ ልዩ ጠባይ የሆነው የመንግስት ስል
ጣን ከታጠቀው ህዝብ ጋርና « በራሱ ከሚሰራው የታ
ጠቁ ድርጅት » ጋር « በቀጥታ ስለማይመሳሰል » ስለ
የታጠቁ ሰዎች ልዩ ክፍሎች ብናወራ በቂ ምክንያት
አለን ።

እንደ ሌሎች ታላላቅ አብዮተኞች ፈላስፎች ሁሉ
ኤንግልስ የመደብ ንቃተ ህሊና ያላቸውን ወዛደሮች
ትኩረት ለመሳብ የሚሞክረው በተራና በተለመደ አስ
ተሳሰብ ምንም ያህል ግምት ላልተሰጠው ፤ በጣም
የተለመደና በጠንካራ ጥላቻ ወደ ተቀደሰው (የተባረ
ከው) ነጥብ ነው ። የመንግስት ስልጣን ዋና መሳሪያ
ዎች ቋሚ ጦር ሰራዊትና ፖሊስ ናቸው ። ከዚህ ሌላ
ሊሆን ይችላል ?

ኤንግልስ በ19ኛው ምእተ አመት መጨረሻ ላይ
ይህን ይነግራቸው ከነበሩት በአንድም ትልቅ አብዮት
ውስጥ ባልኖሩትና በቅርብም ባላዩት አውሮፓውያን
አስተያየት አንፃር ፤ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም ።
« በራሱ የሚሰራ የህዝቡ የታጠቀ ድርጅት » ምን
ማለት እንደሆነ ፍፁም ሊገባቸው አልቻለም ። ከህ
ብረተሰብ በላይ የሆኑትና እራሳቸውን ከእርሱ የነጠ
ሉት (ፖሊስና ቋሚ ጦር ስራዊት) የታጠቁየሰዎች ልዩ
ክፍል አስፈላጊነቱ መቼ መጣ ለሚለው ጥያቄ ፣
የምእራብ አውሮፓና የሩሲያ አድርባዮች የማህበራዊ

ኑሮ ውስብስብነትን የስራ መከፋፈልን ፥ ወዘተ በመጥቀስ ከስፔንስርና ከሚካይሎቭስኪ አንዳንድ ሀረጎችን በመዋስ ለመመለስ ይቃጣሉ ።

እንደዚህ አይነቱ ጥቅስ « ሳይንሳዊ » ስለሚመስል መሰረታዊና አስፈላጊ የሆነውን እውነት ፥ ማለትም ፥ የህብረተሰብ ሊታረቁ በማይችሉ ተፃራሪ መደቦች መከፋፈልን ስለሚጋረድ የተራውን ሰው ህዋሳት በሚገባ ያደነዝዛል ።

ይህ መከፋፈል ባይኖር ኖሮ ፤ « በራሱ የሚሰራ የታጠቀ የህዝብ ድርጅት » በዱላ ከሚጠቀመው የዝንጀሮ መንጋ ጥንታዊ ድርጅት ፥ ወይም ከጥንታዊው ሰው፥ ወይም በጎሳ ከተዋሃዱት ሰዎች በውስብስብነቱ ፥ በከፍተኛ ቴክኒክና በመሳሰሉት ይለይ ነበር ፤ ይህ አይነቱ ድርጅት አሁንም ይቻል ነበር ።

ይህ ግን አይቻልም ፥ ምክንያቱም ፥ ህብረተሰብ በስልጣኔ ዘመን ተፃራሪ በሆኑና እንዲያውም ሊታረቁ በማይችሉ ተፃራሪ መደቦች በመከፈሉ « በራሱ የሚሰራ» ሁኔታ ማስታጠቁ በመሃከላቸው የትጥቅ ትግልን ያስከትላል ። መንግስት ሲነሳ ፥ ልዩ ኃይልና ልዩ የታጠቁ የሰዎች ክፍሎችም ይፈጠራሉ ፤ እና ማንኛውም አብዮት ፥ የመንግስት መሳሪያ በመደምሰስ በግልፅ የሚያሳየን የገዥው መደብ እራሱን የሚያገለግሉትን ልዩ የሰዎች ክፍሎች መልሶ ለማስቀመጥ እንደሚጣጣርና ፥ የተጨቆነው መደብ ደግሞ በዝባዦችን ሳይሆን ተበዝባዦችን የሚያገለግል እንደዚሁ አይነት አዲስ ድርጅት ለመፍጠር እንደሚጥር ነው ።

ከላይ በተጠሰው ፥ አመለካከት ኤንግልስ በቲዎሪ ያነሳው ማንኛውም ትልቅ አብዮት በተግባር ከፊታችን



የሚደቅነው ጥያቄ፥ ማለትም ፥ ግልፅ ባለና ፥ ከዚህም በላይ ሰፋ ባለ የድርጊት ደረጃ « ልዩ » በሆኑት የታጠቁ የሰዎች ክፍሎችና « በራሳቸው በሚሰሩት በታጠቁት የህዝብ ድርጅቶች» መሃል ስለአለው ግንኙነት ጥያቄ ነው ። ይህ እንዴት ተጨባጭ በሆነ መንገድ በሩሲያና በኤውሮፓ አብዮቶች ልምድ እንደ ታየ እናያለን ።

እስኪ ወደ ኤንግልስ ገለፃ እንመለስ ።

አንዳንድ ጊዜ ፥ ለምሳሌ ፥ በሰሜን አሜሪካ አንዳንድ ክፍሎች ውስጥ ይህ የመንግስት ስልጣን ደካማ እንደ ሆነ ይጠቁማል (በሃሳቡ ያለው በካፒታሊስት ህብረተሰብ ያልተለመደውን ሁኔታ ፥ ማለትም በቀድመ ኢምፔሪያሊስት ጊዜ ነፃ የሆኑት አቅኚዎች የሰፈኑበትን የሰሜን አሜሪካ ክፍል ነው፥ )ነገር ግን ያም በአጠቃላይ አነጋገር እየጠነከረ ይሄዳል

« . . . በመንግስቱ ውስጥ ያለው የመደብ ተፃርሮ እየከረረ ሲሄድ ፥ እንዲሁም ጎረቤት መንግስታት እያደጉና የህዝብ ቁጥራቸው ከፍ እያለ ሲሄድ የመንግስቱም ስልጣን እየጠነከረ ይሄዳል ። የመደብ ትግልና የቅኝ ግዛት ሽሚያ የመንግስቱን ስልጣን በጣም በማናጋት መላውን ህብረተሰብና እራሱን መንግስቱንም ለማጥፋት የደረሰበትን የአሁኑን አውሮፓ ሁኔታ መመልከቱ ብቻ ይበቃል ። »

በኤንግልስ መጨረሻው መግቢያ ላይ የተፃፈው ቀን ሰኔ 16,1891 በመሆኑ ፥ ይህ ጥቅስ የተፃፈው በአስራ ስምንት መቶ ዘጠና መጀመሪያ ባለፈው ምእተ አመት መጨረሻ ላይ ነበር ። በዚያን ወቅት ወደ ኢምፔሪያሊዝም መለወጥ ፤ ማለትም የትልልቅ ኩባንያዎች ትረስቶች ሙሉ በሙሉ መግነን ፥ ማለትም ትላላቅ

የባንኮች ተፅእኖ ከመጠን በላይ መጨመር ፣ ማለትም
ትልቅ መጠን ያለው የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲና ወዘተ–በፈ
ረንሳይ አገር ገና መጀመሩና በሰሜን አሜሪካና በጀር
መን ደግሞ ገና ደካማ ነበር ። ከዚያም በ20ኛው
ምእተ አመት በሁለተኛው አስር አመት መጀመሪያ
ላይ መላው አለም በ« ቅኝ ግዛት » ማለትም በትልልቅ
የዘራፊሃይሎች መሃል ከተከፋፈለ በኋላ ግን የ«ቅኝ ግዛት
መቀራመት » ትላልቅ እርምጃዎች ወደፊት ሄዶ ነበር።
ከዚያ ወዲህ የጦርና የባህር መሳሪያዎች ከማይታመን
ደረጃ ድረስ አድገዋል ፣ በ1914—17 እንግሊዝና
ጀርመን አለምን ለመግዛትና የተማረከውን ለመካፈል
ያደረጉት የዘራፊዎች ጦርነት ፣ የህብረተሰብን ሃይል
ሁሉ በስገብግብ የመንግስት ስልጣን ወደ «መዋጥና»
ወደ ጨርሶ መጥፋት አድርሰውት ነበር ።

ገና በ1891 ኤንግልስ « ለቅኝ ግዛት የሚደረግ
ውድድር » ዋና መለያ ነጥብ የሃያላን መንግስታት
የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንደሆነ ጠቁሞ ነበር ፣ ነገር ግን
በ1914—17 ፤ ይህ ውድድር ፣ በብዙ እጅ ከፍ በማ
ለት፣የኢምፔሪያሊስት ጦርነት ሲያስከትል ፣ የሶሺያል
ትምክህተኝነት ቡችሎች "የራሳቸውን" ቡርዧ የዝር
ፊያ ፍላጐት ለ "አባት አገር መከላከል" "ለሪፐብሊክና
ለአብዮት መከላከልና" ወዘተ ! በሚሉ ሀረጐች ሸፈኑት።

## 3. መንግስት — እንደየጭቁን መደብ መበዝበዣ መሳሪያ

የመንግስትን ሃይል ፣ ከህብረተሰብ በላይ ሆና
እንዲቆም ፣ ታክስና የመንግስት ብድሮች ያስፈልጋል ።
ስለዚህ ጉዳይ ኤንግልስ ሲፅፍ እንዲህ ይላል ፤
« የመንግስት ስልጣን በመያዛቸውና ግብሮችን



ለመወሰን መብት ስላላቸው ፣ ባለስልጣኖች ፣
የህብረተሰቡ አካል የሆኑት ፣ አሁን ከህብረተሰቡ
በላይ ሆነው ቆመዋል ። ለቤተዘመድ (ለጎሳ) አካ
ሎች ይሰጥ የነበረው ነፃና የበጎፈቃድ ክብር
አያጠግባቸውም ወይም አይሰማማቸውም ፤ ሊያ
ገኙትም ቢችሉ እንኳን ፣ . . . » ባለስልጣና
ችን ቅዱስና የማይሻሩ የሚያደርጉ ህጎች ይደነ
ገጋሉ ። "ከሁሉም ዝቃጭ የሆነው የፖሊስ አገ
ልጋይ" ከጐሳ ወኪሎች በላይ የሆነ "ስልጣን"
አለው ፤ ሆኖም የሰለጠነ መንግስት የጦር ሃይል
መሪ እንኳን ለጐሳ ሽማግሌ ከህብረተሰቡ "ያለ
ተፅዕኖ የሚያገኘው ክብር" የሚያስቀናው ነው ።

ከዚህ ላይ ባለስልጣኖች የመንግስት ስልጣን አካል
በመሆናቸው ያላቸው የተለየ የክብርና የጥቅም ቦታ
ፕሮብሌም ተነስቷል ። ዋናው ጥያቄ ፡— እነሱን ከህ
ብረተሰቡ በላይ የሚያደርጋቸው ምንድነው ? የሚለው
ነው ። ይህ የቲዎሪ ጥያቄ በ1871 በፓሪሱ ኮሚዮን
በተግባር እንዴት እንደተመለሰና እንዲሁም በ1912
በአድሀሪ ሁኔታ እንዴት በካውትስኪ ተድብስብሶ
እንደታለፈ እናያለን ።

« መንግስት የተነሳው የመደቦችን ተፃራሪነት በቁ
ጥጥር ስር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና ፣ እንዲሁም
የተነሳበት ጊዜ ፣ እነዚህ መደቦች በግጭት መካ
ከል በነበሩበት ወቅት ስለነበረ ከሁሉም ሃይለኛ ፣
በኢኮኖሚ በይበልጥ የበላይ የሆነው መደብ መን
ግስት ይሆናል ፣ በመንግስቱም አማካኝነት ይህ
መደብ በፖለቲካም የበላይ መደብ በመሆን ፣
ጭቁኑን መደብ ለመበዝበዝና ረግጦ ለመያዝ ፣
አዲስ መሳሪያ ያገኛል ። » የባሮችና የገባሮች

[illegible] መንግስታት ብቻ
ሳይሆኑ ፣ «የዘመናዊው ተወካይ መንግስት ደመ
ወዝተኞችን በካፒታል የማስበዝበዢ መሳሪያ
ነው ። አንዳንድ ጊዜ እንደአጋጣሚ ለነዚህ የሚ
ዋጉት መደቦች ወደ ተመጣጣኝነት ደረጃ የሚ
ደርሱበት ክፍለጊዜና ፣ የመንግስት ሃይል ለጊ
ዜው ከሁለቱም እስከተወሰነ ደረጃ ነፃነት በማ
ግኘት ከእውነተኛ ጠባዩ ውጭ አስታራቂ የሚሆ
ንበትጊዜ አለ ። »

የቦናፓርቲዝም መጀመሪያውና የሁለተኛው የፈረን
ሳይ ንጉስ ነገስት መንግስትና፣የጀርመን የቢስማርክ
ግዛት ማለትም የአስራ ሰባተኛውና የአስራ ስምንተ
ኛው ምእተ አመታት ፍፁም የሆነ ስልጣን ያላቸው
የዘውድ አገዛዞች የዚህ አይነት ነበሩ ።

በንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች አመራር የተነሳ ፣ ሶሻ
ሊስቶችም ድሮ ገና አቅመ ደካማ በሆኑበትና ቡርዧ
ውም ሊበታትናቸው ገና ሃይል ባልነበረው ጊዜ የሩ
ሲያ ሪፐብሊክ የከሬንስኪ መንግስት አብዮታውያን ወዛ
ደሮችን ማሳደድና ማሰቃየት ከጀመረ በኋላ የዚህ አይ
ነት መንግስት ነው ለማለት ይቻላል ።

በዲሞክራቲክ ፤ ሪፐብሊክ ፣ ኤንግልስ አባባሉን
በመቀጠል፣ «ሀብት ሃይሉን በተዘዋዋሪ መንገድ
ያገኛል፣ ግን የበለጠ ውጤት ለማግኘት » መጀ
መሪያ በቀጥታ ባለስልጣኖችን በማባለግ
(አሜሪካ) ፤ ሁለተኛ « በመንግስትና በስቶክኤ
ክስቼንጅ መካከል ቃል ኪዳን በመፍጠር» (ፈረንሳ
ይና አሜሪካ) ነው የሚጠቀምበት ።
በአሁን ጊዜ ፣ የኢምፔሪያሊዝምና የባንኮች የበላይ



ነት በሁሉም አይነት የዲሞክራቲክ ሪፑብሊኮች ውስጥ
የሀብትን ሀያልነት የመጠበቁንና ውጤት ሰጭም
የማድረጉን ሁለት ዘዴዎች ወደልዩ ጥበብ አሳድገዋ
ቸል ። ለምሳሌ ፣ በመጀመሪያዎቹ የሩሲያ ዲሞክራ
ቲክ ሪፐብሊክ ወራት ፣ እንበል « የሶሻሊስት »
(የኤስ አር ሶሻሊስት) አብዮታውያን እና ሜንሸቪክስ
ከቡርዧው ጋር በጫጉላ በነበሩበት ጊዜ ፣ በጥምሩ መን
ግስት ውስጥ ሚስተር ፖልቺንስኪ ካፒታሊስቶች የሚ
ያደርጉትን ዘረፋ የምዝበራ ስራቸውን ለመግታት የሚ
ወሰደውን እርምጃ ሁሉ ቢያደናቅፍና እንዲሁም ግምጃ
ቤቱን ለጦርነት አገልግሎት የሚያውሉ ውሎችን ቢፈ
ራረምና ቢያዘርፍ፣ከዚያም በኋላ ሚስተር ፖልቺንስኪ
ስራውን በገዛ ፈቃዱ ቢለቅ (እና ሆኖም ፣ ልክ እንደሱ
ባለ በሌላ ፖልቺንስኪ ቢተካ) እና ከካፒታሊስቶች በዓ
መት 120,000 ሩብል ደሞዝ የምታስገኝ « ለስላሳ » ስራ
በቀጥታ ቢሸለም ፣ ይህንን የምትሉት ቀጥታ ጉቦ ነው
ወይስ ተዘዋዋሪ ጉቦ ? የመንግስትና የስንዲኬት ድሬ
ክተሮች አንድነት ወይስ መልካም የጓደኝነት ግንኙነት
« ብቻ » ነው ? እንእቼርኖቭ እንሴሬቲ ፤ እነአቭ
ሴንቲቭ እና እነ ስኮቤልቭ የሚጫወቱት ሚና ምንድ
ነው ? የባለሚሊዮን ግምጃ ቤት ዘራፊዎች በ «ቀጥታ»
ወይስ በተዘዋዋሪ ብቻ ተባባሪዎች ናቸው ?

በዲሞክራሲ ሪፐብሊክ የ« ሀብት » ከሁሉ በላይ
መሆን በበለጠ የተረጋገጠበት ምክንያት ደካማበሆነ
በካፒታሊዝም ፖለቲካ ግርዶሽ ጥገኛ ስለሆነ ነው ።
ለካፒታሊዝም ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ከሁሉም
የበለጠ የፖለቲካ ግርዶሽ ነው ። ስለዚህም (በእ
ነፖሊችንስኪ ፣ ቼርናቭ ፣ ሴሬቴሊ እና ጓደኞቹ አማ
ካኝነት) ካፒታል አንድ ጊዜ ይህንን ከሁሉ የበለጠ

ግርዶሽ በመቆጣጠር ፣ በዚያ የሰዎችም ሆነ የድርጅ ቶች ወይም በቡርዧው ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች መለዋወጥ እንዳያነቃንቀው በርግጠኛ በማያወላውል ሁኔታ ይመሰርታል ።

እንዲሁም እኛ መገንዘብ ያለብን ኤንግልስ ህዝባዊ ምርጫ የቡርዧው የአገዛዝ መሳሪያ ነው በማለት በእ ርግጠኝነት መሰየሙን ነው ። የጀርመን ሶሻል ዲሞክ ራሲን ልምድ በማጠቃለል ሲናገር ህዝባዊ ምርጫ « የወዛደሩ መደብ ብስለት መለኪያ ነው ። በዛሬው ጊዜ መንግስት ውስጥም ከዚህ ሌላ ፈፅሞ ሊሆን አይ ችልም . . . . »

የንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች፣የኛን ሶሻሊስት አብዮተ ኛነት እና ሜንሼቪኮች የመሳሰሉት እንዲሁም መንታ ወንድሞቻቸው ፣ የምእራብ ኤውሮፓ የሶሻል ትምክ ህተኞችና አድርባዮች ሁሉ ከህዝባዊ ምርጫ ትንሽ « የበለጠ » ለማግኘት ይጠብቃሉ ። « ከዘመናዊው መንግስት ህዝባዊ ምርጫ » የአብዛኛውን ለፍቶ አደር ፍላጐት ለማረጋገጥ የሚቻልና በስራ ላይ የሚውል ነው በማለት ራሳቸው የማያምኑበትን የተሳሳተ አሳብ በሌሎች ሰዎች ጭንቅላት ውስጥ ስር ሰዶ እንዲገባ ያደርጋሉ ።

ከዚህ ላይ እኛ ለማሳየት የምንችለው ይህ ሃሳብ ስህ ተት መሆኑን ፣ « ይፋ » በሆኑት (ማለትም አድርባይ) ሶሻሊስት ፓርቲዎች ፣ የኤንግልስን ሙሉ በሙሉ ግልፅ ትክክለኛና መሰረታዊ የሆነውን ገለፃ በየፕሮፓጋንዳ ቸውና የቅስቀሳ እርምጃዎቻቸው ሁሉ የተጣመመ ትርጉም መስጠታቸውን በመጠቆም ብቻ ነው ። ከዚህ ላይ ኤንግልስ ችላ ያለው ሃሳብ ጨርሶ ስህተት መሆ



ኑን « በዘመናዊ » መንግስት ላይ የማርክስና ኤንግልስ አስተያየቶች በሚለው የወደፊት መግለጫዎቻችን ላይ በዝርዝር እንገልጣለን ።

ኤንግልስ ከሁሉም ታዋቂና ተወዳጅ በሆነው ስራው ውስጥ የእራሱን አስተያየት በሚከተሉት ቃላት በማ ጠቃለል እንደሚከተለው ይሰጣል ፡—

« እንግዲህ ፣ መንግስት ከአለም መጀመሪያ ጀምሮ የኖረ ዘለአለማዊ አይደለም ። ስለመንግስት ሃይ ልና ስለመንግስት ፅንስ ሃሳብ ያልነበራቸውና ያለ እርሱም የኖሩ ህብረተሰቦች ነበሩ ። በተወሰነ ኢኮ ኖሚ የእድገት ደረጃ ፣ ህብረተሰቦች በመደብ መከፋፈል ስለነበረባቸው ፣ በዚህ መደብ መከ ፋፈል የተነሳ መንግስት አስፈላጊ ሆነ ። አሁን የእነዚህ መደቦች መኖር አስፈላጊነት የቀረበት ብቻ ሳይሆን ፣ ለምርት ቋሚ እንቅፋት ወደሆኑ በት የምርት የእድገት ደረጃ ላይ በፍጥነት በመ ድረስ ላይ ነን ። ቀደም ባለው ጊዜ እንደተነሱትም ሁሉ እንደዚሁም ይወድቃሉ ። ከእነርሱ ጋር እን ደዚሁ መንግስት አብሮ ይወድቃል ። ነፃና እኩል በሆነ የአምራቾች ማህበር መሰረት ምርትን የሚ ያደራጀው ህብረተሰብ የመንግስት መሳሪያ ሁሉ መኖር ወደአለበት ስፍራ ፣ በቅርሳ ቅርስ ሚው ዚየም ውስጥ ከማዳወሪያና የነሃስ መጥረቢያ ጎን ያስቀምጠዋል ።»

በአሁኑ የሶሻል ዲሞክራሲ የፕሮፓጋንዳና የቅስ ቀሳ ፅሁፍ ውስጥ ይህ ጥቅስ እምብዛም አያጋጥመንም ። ቢያጋጥመንም እንኳን ፣ የሚጠቀሱ በምስል ፊት እን ደሚሰግድ ሁሉ ለይስሙላ ነው ፣ ይህም የተደረገበት ለኤንግልስ የይፋ ክብር ለማሳየት ይህም በቅድሚያ

የሚያሳየው « መላውን የመንግስት አቋም ሁሉ ወደ ጥንታዊ ቅርሳቅርስ» ሚውዚየም መላክ የሚለውን ውሳኔ እንጂ ፥ የአብዮትን ጥልቀትና ምጥቀት ለማመዛዘን የተደረገ ሙከራ አይደለም ። እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ ኤንግልስ ያ! መንግስት መሳሪያ ብሎ የሚጠራውን ለማወቅ አያስችለንም ።

4. የመንግስት « መመንመንና መጥፋት » እና በሃይል ላይ የተመሰረተ አብዮት

የኤንግልስ የመንግስትን «መመንመንና መጥፋት » የሚመለከቱ ቃላት በሰፊው የታወቁ ፥ በብዛት የተጠቀሱና ማርክሲዝምን በማርክስ አድርባይ እንዲመስል የሚደረገው የተለመደ ዘዴ ይዘቱን በግለፅ በደንብ ስለሚያጋልጡ በዝርዝር መመልከት አለብን። ጥቅሶቹ የተወሰዱበትን ክፍል ሙሉ በሙሉ እንጠቅሰዋለን ።

« ወዛደሩ የመንግስትን ስልጣን ይይዝና በመጀመሪያ የምርት መገልገያዎችን ወደ መንግስት ንብረትነት ይለውጣል ። ግን ይህን በማድረግ ፥ በወዛደርነት መቀጠልን ያቆማል ፥ የመደብ ልዩነቶችንና የመደብ ተፃራሪዎችን ሁሉ ጨርሶ ያጠፋል ፥ መንግስት እንደ መንግስትነት መቀጠሉም መጨረሻው ይሆናል ። የበፊቱ ህብረተሰብ ፥ በመደብ ተፃርሮ ውስጥ በመጓዝ ፥ በየወቅቱ የነበረውን የውጭ የምርት ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ፥ ይህም አብዛኛውን ጊዜ የተበዘበዘውን መደብ በጭቆና ሁኔታዎች (በባርነት ፥ በጭሰኝነት ወይም በገባርነት ፥ በደሞዝ ባርነት) ስር በሃይል ለመያዝ በመደራጀት የበዝባዥ መደብ መንግስት አስፈልጎት ነበር ። ጉልህ ሆኖ በሚታይ ድርጅት የተጠቃለለው መንግስት የህብረተሰብ የኑሮ ወኪል ነበር ፥ ነገር ግን ይህ ሊሆን የሚችለው በወቅቱ ህብረተሰቡን በሙሉ ይወክል ለነበረው መደብ መንግስት እስከሆነ ድረስ ብቻ ነበር ። በጥንት ጊዜ ፥ የባሪያ ባለቤት ዜጎች መንግስት ፤ በመካከለኛው ዘመን ፥ የመሬት ከበርቴ መሳፍፍንቶች መንግስት ፤ በኛ ዘመን ደግሞ የቡርዧው መንግስት። በመጨረሻ በእውነትም የመላው ህብረተሰብ ወኪል ሲሆን ፥ እራሱን የማያስፈልግ ያደርጋል። በጭቆና ስር መኖር የአለበት አንድም መደብ የማይኖርበት ጊዜ ሲመጣ ፥ ከመደብ መጨቆን ጋርና ለግለሰብ ህልውና ሲባል የሚደረገው፥እስከ አሁን ድረስ ባለውና ስርአት አልባ በሆነው ምርት ላይ ከተመሰረተው ትግል የሚመነጩት ግጭትና ሌላ ትርፍ ነገሮች ሲወድሙ ፥ የተለየ የሚጨቆን ነገር ስለማይኖር የተለየ ጨቋኝ ሃይል መንግስት አስፈላጊ አይሆንም ። በእርግጥ መንግስት መጀመሪያ እንደ መላው ህብረተሰብ ወኪል ሆኖ ብቅ የሚልበት የመጀመሪያ ድርጊት በህብረተሰብ ስም የምርት መገልገያን መውሰድ ሲሆን ፥ እንደ መንግስት ሆኖ የሚወስደው የመጨረሻ ነፃ ድርጊት ነው ። በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ የመንግስት ሃይል ጣልቃ መግባት ከአንድ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል አስፈላጊነቱ እየቀነሰ በመሄድ በራሱ ይቆማል ። የሰዎች አገዛዝ ነገሮችን በማስተዳደርና የምርት ሂደትን አቅጣጫ በመስጠት ይተካል ። መንግስት « አይደመሰስም » <u>በመመንመን ይጠፋል</u> እንጂ ።

« ነፃ የህዝብ መንግስት » የተባለውን ሃረግ ለቅ

ስቀሳ አላማ ጊዜያዊ አስፈላጊነቱንም ሆነ የመ
ጨረሻው ሳይንሳዊ ቁንፅልነቱን እንዲሁም በአ
ንድ ምሽት መንግስት መውደም አለበት የሚ
ሉትን የአናርኪስቶችን ጥያቄ ፤ ከዚህ አቋም
ነው መመዘን የአለብን ። » የሄር ኡገፔን
ዱሪንግ በሳይንስ አብዮት ፀረ—ዱሪንግ
ገፅ 301—3 ሶስተኛው የጀርመን እትም)[4]

ብዙ ሀሳቦችን ከያዘው ከኤንግልስ ሀተታ ውስጥ
ከዘመናዊ የሶሻሊስት ፓርቲዎች አስተሳሰብ አንድ
አካል የሆነው አንዱ ነጥብ እንደ ማርክስ አባ
ባል መንግስት «መንምኖ ይጠፋል» የሚለውና
መንግስት « ይደመሰሳል » ከሚለው ከአናርኪስቶች
የተለየ ነው ብንል ከስህተት እንወድቃለን ብለን
አንፈራም ። ማርክሲዝምን በዚህ አይነት ማኰላሸት
ወደ አድርባይነት ዝቅ ማድረግ ነው ፥ ምክንያቱም የዚህ
አይነት «አተረጓጎም» የእመርታንና ማእበልን ፥ አለመ
ኖር የአብዮቱን አለመኖር ዝግታን ፥ ቀስበቀስ የመሄድን
ጭፍን አስተሳሰብ ያመለክታልና ። በአሁኑ ጊዜ ፥ በጣ
ም የተስፋፋው የመንግስት «መንምኖ መጥፋት»
የሚለው አስተሳሰብ ፥ አብዮትን ካልተቃወመ
ያለጥርጥር አብዮትን ማደብዘዝ ነው ።

የዚህ አይነት « ትርጉም » ለቡርዧው ብቻ የሚያ
መች ፥ ቅጥ የሌለው ማርክሲዝምን ማጣመም ነው ፤
በቲዎሪ መስክ ፥ በሙሉ በጠቀስነው በኤንግልስ «ማጠ
ቃለያ » ውስጥ የተጠቆሙትን አስፈላጊ ሁኔታዎችና
ሚዛኖች ካለመገንዘብ ላይ የተመሰረተ ነው ።

በመጀመሪያ ደረጃ ፥ ኤንግልስ ገና ሀተታውን ሲ
ጀምር ፥ ወዛደሩ መንግስትን በመያዝ « መንግስት



እንደ መንግስት መሆኑን ያጠፋዋል » ይላል ። የዚህ
ትርጉም ምን እንደሆነ ማሰቡ «የተለመደ አይደለም።»
በአጠቃላይ ፥ ሙሉ በሙሉ ተዘንግቷል ፥ ወይንም
ደግሞ በኤንግልስ በኩል የተደረገ እንደ « ሄጌላዊ
ደካማነት » ተቆጥሯል ። ነገር ግን ፥ በእርግ
ጥም ፥ እነዚህ ቃላት ፥ በተገቢው ቦታ በዝርዝር
ስለምናወሳው ፥ ከትልልቅ ወዛደር አብዮቶቹ አንዱ
ስለሆነው ፥ ስለ 1871ዱ የፓሪስ ከሚዩን ልምድ በአ
ጭሩ ይገልፃሉ ። እንደ እውነቱ ከሆነ ኤንግልስ የወ
ዛደሩ አብዮት የቡርዧውን መንግስት « ስለመደም
ሰሱ » ይናገራል ፤ ነገር ግን ስለመንግስት መመንመ
ንና መጥፋት የሚያወሱት ቃላት የተነገሩት ከሶሺያ
ሊስት አብዮት በኋላ ስለሚቀረው የወዛደር መንግስት
ነው ። እንደ ኤንግልስ አባባል የቡርዧው መንግስት
« በመመንመን » አይጠፋም ። ነገር ግን አብዮቱ ሲካ
ሄድ በወዛደሩ « ይደመሰሳል » ። ከዚህ አብዮት በኋላ
በመመንመን የሚጠፋው የወዛደሩ መንግስት ወይም
ከፊል መንግስት ነው ።

ሁለተኛ ፥ መንግስት «ልዩ መጨቆኛ ሃይል » ነው።
ኤንግልስ ይህን አስደናቂና ጥልቀት ያለውን ገለፃ በጣም
ግልፅ በሆነ አኳኋን ይሰጣል ። ከዚህም የሚከተለው
ቡርዧው ወዛደሩን ፥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ለፍቶ አደ
ሮችን እፍኝ ብቻ በሚመሉ ሃብታሞች ለመጨቆን
የሚያገለግለው «ልዩ መጨቆኛ ሃይል» ፥ ቡርዧውን በወ
ዛደሩ ለመጨቆን በሚያገለግል «ልዩ መጨቆኛ ሃይል» ፥
በወዛደሩ የበላይ ገዥነት መተካት አለበት ። «መንግ
ስት እንደ መንግስት መሆኑን መደምሰስ» ማለት ትክ
ክለኛ ትርጉም ይህ ነው ። በህብረተሰብ ስም የምርት
መገልገያዎችን የመውሰድ « ድርጊትም » ይኸው

ነው ። እንዲህ አይነቱ የአንድ (ቡርዧ) « ልዩ ኃይል » በሌላ (ወዛደር) «ልዩ ሃይል » መተካት እንዲያው « በመመንመን መጥፋት» እንደማይሆን ሳይታለም የተፈታ ነው ።

ሶስተኛ ፣ ስለ መንግስት «መመንመንና መጥፋት » እና ከዚህም በበለጠ ስእላዊና ደማቅ የሆነው « መንግስት እራሱ መንግስት መሆን ስለማቆሙ» ጉዳይ ሲናገር ለኤንግልስ ግልፅና ቁርጥ ባለ አኳኋን የሚያመለክተው ጊዜ « መንግስት በህብረተሰብ ስም የምርት መገልገያዎችን ከወሰደ» በኋላ ይህም ከሶሺያሊስት አብዮት በኋላ ነው ። ሁላችንም በዚያን ጊዜ «የመንግስት» የፖለቲካ ፎርም ሙሉ የሆነ ዲሞክራሲ እንደሆነ እናውቃለን ። ነገር ግን ማርክሲዝምን ካለሀፍረት በሚበርዙት አድርባዮች ጭንቅላት ውስጥ በጭራሽ የማይገባው፤ኤንግልስ ከዚህ ላይ ስለመንግስት «መመንመንና መጥፋት» ሲናገር ስለ ዲሞክራሲ መናገሩ ነው ።ነገር ግን ይህ «የማይገባው» ዲሞክራሲ ጭምር መንግሥት መሆኑና መንግስትም ሲጠፋ ዲሞክራሲም ጭምር እንደሚጠፋ ያልተመራመረ ብቻ ነው ። ይህም ሲታይ እንግዳ ነገር ይመስላል ። እንዲሁም ዲሞክራሲ እራሱ መንግስት መሆኑ የማይገባቸው ስለዚህም መንግስት ሲጠፋ ዲሞክራሲም እንደሚጠፋ ያልተመራመሩ ብቻ ናቸው ። አብዮት ብቻ ነው የቡርዧውን መንግስት « የሚደመስሰው » በአጠቃላይ መንግስት ፤ይህም በጣም ሙሉ የሆነው ዲሞክራሲ ብቻ ነው « በመመንመን መጥፋት » የሚችለው ።

አራተኛ « መንግስት በመመንመን ይጠፋል » የሚለውን ሀሳብ ኤንግልስ ሲያቀርብ ፣ ይህ አሳብ በቀጥታ



የሚያመለክተው ወደ አድርባዮችና አናርኪስቶቹ እንደሆነ በተጨባጭ ወዲያውኑ ገልጧል ። ኤንግልስ ይህን በማድረጉ በአድርባዮቹ ላይ ያተኮረውንና « መንግስት በመመንመን ይጠፋል» ከሚለው ሃሳብ የተወሰደውን መደምደሚያ በመጀመሪያ ቦታ አስቀምጧል ።

« ስለመንግስት መመንመንና መጥፋት » ካነበቡት ወይም ከሰሙት 10,000 ሰዎች መሃል 9,900 ኤንግልስ ከርሱ ሃሳብ ያወጣቸውን መደምደሚያ ዎችየጠቀመው በአናርኪስቶች ላይ ብቻ እንዳልሆነ እንደማያውቁ ወይም እንደማያስታውሱ ለማረጋገጥ ይቻላል ።ከሚቀሩት አስሩ ደግሞ ምናልባት ዘጠኙ «ነፃ የህዝብ መንግስት» ትርጉም ወይም ይህን መፈክር መዝለፍ አድርባዮችን መዝለፍ እንደሆነ አያውቁም ። ታሪክ የተፃፈው እንደዚህ ነው ! ትልቅ አብዮታዊ ትምህርት በውሸት የተበከለውና ለሰፈነው አድርባይነት እንዲስማማ የተደረገውም እንደዚህ ነው ! በአናርኪስቶቹ ላይ የተጠቆመው መደምደሚያሺህ ጊዜ ተደጋግሞአል ፣ ተበርዞ በመደጋገሙ ብቻ በሰዎች አንጎል ውስጥ ተቀርፆ በዝንባሌ ብቻ ተቀባይነትን የማግኘት ጥንካሬ ተቀዳጅቷል ። ነገር ግን በአድርባዩ ላይ የተጠቆመው መደምደሚያ ተድበስብሶ « ተረስቷል » !

«የነፃ ህዝብ መንግስት» በ1870ኛው አመታት የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቶች የፕሮግራም ጥያቄና በጊዜው በሰፊው የነበረ መፈክር ነበር ። ይህ መፈክር በጩኸት በተመላ ርካሽ መንገድ ዲሞክራሲን ከመግለፁ በስተቀር ምንም የፖለቲካ ይዘት የለውም ። በህግ በተፈቀደው መሰረት ለ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ እስከጠቀመ ድረስ ከቅስቀሳ አቅጣጫ በመመልከት ኤንግልስ «ለተወሰነ

ጊዜ» በጥቅም ላይ እንዲውል «ምክንያት» ለማቅረብ
ዝግጁ ነበር ። ነገር ግን የቡርዧ ዲሞክራሲን የሚያወ
ድስ ከመሆኑም በላይ በጠቅላላው በመንግስት ላይ
የተሰነዘረውን የሶሻሊስት ትችት ሊቀበል ባለመቻሉ
አድርባይ መፈክር ነው ። በካፒታሊዝም ስር ላለው
ወዛደር የዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ በጣም የተሻለው የመ
ንግሥት ቅርስ ስለሆነ እንመርጠዋለን ። ነገር ግን በጣም
ዲሞክራቲክ በሆነው ቡርዧ እንደሆነ የመርሳት መብት
የለንም ። በተጨማሪም ፣ ማንኛውም መንግስት
ለተጨቋኙ መደብ መግቻ «የተለየ ጨቋኝ ሀይል ነው»
ስለዚህም አንዳ አንዱ መንግስት «ነፃ» ወይም "የህዝብ
መንግስት አይደለም"።በሰባኛው አመት ማርክስና ኤንግ
ልስ ይህን ለፓርቲ ጓዶቻቸው በመደጋገም ገልፀው ነበር።

አምስተኛ ፣ ስለ መንግስት መመንመንና መጥፋት
ማንኛውም ሰው የሚያስታውሰውን ሀተታ የያዘው ይ
ኸው የኤንግልስ ስራ በአመፅ ላይ የተመሰረተን አብ
ዮት አስፈላጊነት ያዘለ ሀተታን ይዟል ። ኤንግልስ
ይህ ስለአለው ሚና የአቀረበው ታሪካዊ ትንታኔ እው
ነተኛ የአመፅ አብዮት ሙገሳ ሆኖአል ። ይህንን « ማንም
አያስታውስም ፣ » በዘመናዊ የሶሺያሊስት ፓርቲዎች
ዘንድ ስለዚህ ሃሳብ አስፈላጊነት ማውራትም ሆነ እን
ዲያውም ማሰብ ጥሩ አይደለም ፤ ስለዚህም በሰፊው
ህዝብ መሃል ከሚያካሂዱት እለታዊ ፕሮፓጋንዳና
ቅስቀሳ ውስጥ ምንም ክፍል አይጫወትም ። ነገር ግን
ከመንግስት « መመንመንና መጥፋት » ጋር በማይለ
ያይና በተቀነባበረ ሙሉ አካል ውስጥ ተዋህዷል ።
የኤንግልስ ሀተታ እንደሚከተለው ነው ፤

«. . . ያ ሀይል » (ከሰይጣን ሀይል የተለየ የሆነው)»
በታሪክ ውስጥ ሌላ ሚና ፤ ሌላ አብዮታዊ ሚና



አለው ፤ እንደ ማርክስ አባባል ፤ የማንኛውም
አዲስ ነገር የአረገዘ አሮጌ ህብረተሰብ አዋላጅ
ነው ማህበራዊ እንቅስቃሴ መንገዱን የሚጠርግ
በት የሞቱትንና በድን የሆኑትን የፖለቲካ ቅርፆች
እንዲሰባብር የሚረዳ መሳሪያ ነው ። ስለዚህ በሄር
ዱሪንግ ምንም ቃል አልተጠቀሰም ። ሃይል የኤኮ
ኖሚን የብዝበዛ ስርአት ለመገልበጥ ምናልባት
ያስፈልጋል ቢልም በማመንታትና በማኩረፍ ነው ፣
በመጥፎ አጋጣሚ ፤ ማንኛውም ሀይልን የመጠ
ቀም ክስተት የተጠቃሚውን ሰው ሞራል ያዳክ
ማል ። ይህም የተባለው እያንዳንዱ ድልን የተ
ቀዳጀ አብዮት ከፍተኛ የሞራልና የመንፈስ ግፊ
ትን እንዳስከተለ ስለሚታወቅ ነው! በጀርመን ይህ
የሃይል ግጭት — ያውም በግድ በህዝቡ ላይ ሊ
መጣ የሚችለው ቢያንስ ቢያንስ የሰላሳ አመቱ
ጦርነት ውርደት ምክንያት በብሄራዊው ንቃተ
ህሊና ላይ ሰፍኖ የሚገኘውን ደካማነት ድም
ጥማጡን ሊያጠፋ ይችላል። ይህ ህይወት አልባ
ልበቢስነትና የተኮላሸ የደብተራ አስተሳሰብ
በታሪክ በታወቀውና በጣም አብዮታዊ በሆ
ነው ፓርቲ ላይ እራሱን እንዳስቀመጠ አድርጎ
ያሳያል !» ። (ገፅ 193 3ኛው የጀርመን እትም
ክፍል ሁለት ምዕራፍ 4 መጨረሻ)

ታዲያ እንዴት ኤንግልስ ለጀርመን ሶሻል ዲሞክራ
ቶች በ1878ና በ1894 መሃል ማለትም እስከሞተ
በት ጊዜ ድረስ በመደጋገም ያሳሰበው ፣ ይህ ስለአብ
ዮት አመፅ የተደረገው የምስጋና ንግግር ከመንግስት
« መመንመንና መጥፋት » ቲዎሪ ጋር ተደባልቆ እንደ
ዶክትሪን ሊሆን ይችላል ?

አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱ በኤክሌክቲሲዝም አማካ ኝነት ይገናኛሉ ። አላማ ቢስ ወይም ሶፌስቲክ በሆኑና (ወይም በስልጣን ላይ ያሉትን ለማስደሰት) በዘፈቀደ አንዴ አንዱን ሀተታ ፥ እንዴ ደግሞ ሌላውን ሀተታ ፥ በመውሰድ ከመቶ ዘጠና ዘጠኙ ጊዜ ፥ ወይም ያውም ከዚህ በላይ ባይሆን ፥ ግንባር ቀደም አድርጎ የሚያስ ቀምጠው « የመመንመንና መጥፋትን » ጉዳይ ነው ። ዲያሌክቲክስ በኤክሌክቲሲዝም ተተክቷል ፡ ይህም ስለ ማርክሲዝም ሶሻል—ዲሞክራቶች በአሁኑ ጊዜ በይፋ የሚያወጡት ስነ ፅሁፎች ውስጥ የሚያጋጥመው በጣም የተለመደውና በጣም የተስፋፋው ከስተት ነው ። ይህ አይነት አተካክ አዲስ ነገር አይደለም ፥ በጥንታዊ ግሪክ ፍልስፍና እንኳን ታይቶ ነበር ። ማርክሲዝምን አድር ባይ በሆነ ዘዴ በሀሰት መበከል ፥ በዲያሌክቲክስ ቦታ ኤክሌክቲሲዝምን መተካት ፥ ህዝቡን ለማታለል ቀላል የሆነ መንገድ ነው ፤ አታላይ የሆነ ማርኪያ ይሰጣል ፤ የሂደቱን አንፃሮች ሁሉ ፥ የልማቱን ዝንባሌ ሁሉ ፥ የማይጣጣሙትን ተፅእኖዎች ሁሉና ፥ ሌሎችንም ቢመስልም ፥ በእርግጥ ግን ምንም ስለማህበራዊ ልማት ሂደት የተያያዘና አብዮታዊ የሆነ ፅንስ ሃሳብ አያቀር ብም ።

የማርክስና የኤንግልስ ትምህርቶች ፥ የአመፅ አብ ዮት የማይቀር መሆኑን የሚያመለክቱት ስለቡርዧው መንግስት መሆኑን ከላይ ብለናል ፥ በኋላም በይበልጥ እናሳያለን ። በማንኛውም ጊዜ በአመፅ ትግል እንጂ በመንግስት « መመንመንና መጥፋት » የቡ ዧው መንግስት በወዛደሩ መንግስት (የወዛደሩ የበላይ ገዥነት) ሊተካ አይችልም ። ከማርክስ የተደጋገመ ገለፃ ጋር የሚመሳሰለው በኤንግልስ ስለክብሩ የተዘ



መረው የምስጋና መዝሙር (ስለማይቀረው የአመፅ አብዮት ኩሩና ግልፅ ከሆነው መግለጫቸው ጋር ይመሳሰ ላል የፍልስፍና ድህነት[5] የኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ[6] የመዝጊያ ፅሁፎችን አስታውስ ፤ የ1875ትን የጐታ ፕሮግራም [7] ከሰላሳ አመታት በኋላ ሂስ ባደረገበት ጊዜ ማርክስ የዚህኑ ፕሮግራም የአድርባይ ጠባይ ያለም ህረት የወቀሰበትን አስታውስ) ይህ የምስጋና ንግግር ስሜ ታዊ ፥ ያነጋገር ዘይቤ ወይም የብልጣብልጥ ክርክር አይደለም ። በህዝቡ መሀከል የአመፅ አብዮት አስተሳ ሰብ ስርአት ባለው መንገድ ማስፋፋት አስፈላጊ መሆኑ ፤ ይህ ትክክለኛ አስተሳሰብ የማርክስና የኤንግልስ ትምህርቶች ሁሉ መሰረት ነው ። አሁን በብዛት አይ ለው ባሉት በሶሻል ትምክህተኞችና በካውትስካይት አዝማሚያዎች የዚህ ፕሮፖጋንዳና ቅስቀሳ መዘን ጋት የማርክስንና የኤንግልስን ትምህርቶች ሁለቱም መካዳቸውን ያረጋግጣል ።

የቡርዧውን መንግስት በወዛደሩ መንግስት መጨ ቆን ያለአብዮታዊ አመፅ የማይቻል ነው ። የወዛደሩን መንግስት መደምሰስ (ይህም ጠቅላላውን መንግስትን መደምሰስ ማለት ነው ፥) « ከመመንመንና መጥፋት » ሂደት ውጭ ሊጠፋ አይችልም ።

የነዚህን አስተያየቶች ዝርዝርና መሰረታዊ ትንተና በማርክስና በኤንግልስ የተሰጠው እያንዳንዱን የተለ ያዩ አብዮታዊ ሁኔታ በአጠኑበት ጊዜ ፥ የእያንዳንዱን ነጠላ አብዮት ልምድ ትምህርት በመረመሩበት ወቅት ነው ። አሁን ወደዚህ ፥ ከሁሉም ያለጥርጥር ከፍተኛ ወደሆነው የትምህርታቸው ክፍል እናልፋለን ።

* * *

ምዕራፍ 2

# መንግሥትና አብዮት

## የ1848 — 51 ልምድ ፤

### 1. የአብዮቱ ዋዜማ

የበሰሉ የማርክሲዝም የመጀመሪያ ስራዎች — የፍልስፍና ድህነትና የኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ ፤ ልክ በ1848 አብዮት ዋዜማ ብቅ አሉ ። በዚህም የተነሳ ፣ የማርክሲዝምን ጠቅላላ መርህ ከማቅረባቸውም በላይ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የጊዜውን ተጨባጭ አብዮታዊ ሁኔታ ያንፀባርቃሉ ። ስለዚህም ፣ የ1848—51 አመታት ልምድ መደምደሚያዎች ላይ ከመድረሳቸው በፊት የእነዚህ ፅሁፎች ደራሲያን ስለ መንግስት ያሉትን መመርመር ምናልባት እጅግ በጣም ጠቃሚ ይሆናል ።

የፍልስፍና ድህነት :— ውስጥ ማርክስ እንዲህ ሲል ፅፏል ።

« የወዝ አደሩ መደብ በእድገት ወቅቱ መደቦችንና ተፃራሪነታቸውን የሚያስወግድ ማህበር ባረጀው የቡርዧ ህብረተሰብ እግር ይተካል ፣ በሚገባ የፖለቲካ ስልጣን ተብሎ የሚጠራ ነገር ከቶ አይኖርም ፤ ምክንያቱም የፖለቲካ ስልጣን በቡርዧው ህብረተሰብ ውስጥ ላለው ለመደብ ተጻራ ሪነት ትክክለኛና ይፋዊ መግለጫ ነውና ። የጀርመን እትም ገፅ 182,1885)[8]

ከመደቦች መደምሰስ በኋላ መንግስት ይጠፋል በሚለው ሃሳብ ላይ ያለውን ይህን ጠቅላላ ገለጣ ፣ ከጥቂት ወራት በኋላ—በትክክል ፣ በህዳር 1847 ማርክስና



ኤንግልስ ከፃፉት ከኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ ውስጥ ካለው ገለፃ ጋር ማነፃፀሩ ትምህርታዊ ነው ።

«በጣም አጠቃላይ የሆኑትን የወዝ አደሩን የእድገት ደረጃዎች በምናቀርብበት ጊዜ ፣ በነበረው ህብረተሰብ መሀል ከሞላ ጐደል በስውር የሚካሄደው የርስ በርስ ጦርነትና ያም ጦርነት ግልፅ ወደሆነ አብዮት እስከ ተለወጠበትና እንዲሁም የቡርዧው በሃይል መገልበጥ ለወዛደሩ ስልጣን መሰረት የሚጥል እስከሆነበት ደረጃ ድረስ ተከታትለናል ። »

« የወዛደሩ መደብ በሚያካሄደው አብዮት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ወዝ አደሩን ወደ ገዥው መደብ ደረጃ ከፍ ማድረግና ዲሞክራሲን ማረጋገጥ መሆኑን ከዚህ በላይተመልክተናል » ።

«ወዛደሩ ፣ ደረጃ በደረጃ፣ ከቡርዧው ሁሉንም ካፒታል ለመንጠቅ ፣ ሁሉንም የምርት መሳሪያዎች በመንግስት እጅ፣ ይኸውም እንደገዥው መደብ በተደራጀው ወዛደሩ እጅ ለማድረግ ፣ እንዲሁም የምርት ሃይሎችን ጠቅላላ ድምር በተቻለ መጠን በፍጥነት ለማሳደግ በፖለቲካ የበላይነቱን ይጠቀማል» (ገፅ 31 እና 37 ሰባተኛ የጀርመን እትም ፣ 1906 )[9]

እዚህ ላይ መንግስት በተባለው ርዕስ ላይ ፣ ማለት « የወዛደሩ የበላይ ገዥነት » (ማርክስና ኤንግልስ ከፓሪስ ኰሚዮን በኋላ መጥራት እንደጀመሩት ) ከማርክሲዝም እጅግ የላቁና እጅግ ከፍተኛ ከሆኑት ሃሳቦች ውስጥ አንዱ የሆነውን እናገኛለን ፤ እንዲሁም ከማርክሲዝም «የተረሱት ቃላት» አንደኛው የሆነውን የመንግስትን፣

ይኸውም ወዛደሩ እንደገዥው መደብ የተደራጀበትን
የሚለውን በጣም የሚስብ ትርጉም እናገኛለን ።

ይህ የመንግስት ትርጉም በኦፊሲያል በታወቁት
የሶሺያል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች በጊዜው በነበረው
የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ፅሁፎች ውስጥ ተገልፆ አያ
ውቅም ። ይህም ብቻ ሳይሆን ከጥገናዊ ለውጥ ጋር
ፈፅሞ የማይታረቅና እንዲሁም የአድርባዩችን « የዲ
ሞክራሲ ሰላማዊ እድገት » ግብዝ ቅዠቶች የሚ
ያጋልጥ በመሆኑ ሆን ተብሎ ተረስቶአል ። ወዛ
ደሩ መንግስት ያሻዋል ። ይህ አባባል ማርክስ ያስተማ
ረው ይህንኑ ነው በማለት በሚያረጋግጡልን በሁሉም
አድርባዮች፣ሶሻል ትምክህተኞችና ካውትስካይቶች ተደ
ጋግሞ ይነገራል ። ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ እንደ
ካርል ማርክስ ከሆነ ወዝአደሩ የሚያስፈልገው የሚ
መነምንና የሚጠፋ አይነት መንግስት ብቻ መሆኑን፣
ይህም ማለት በልዩ አይነት መስረት የተቋቋመ ከመ
ሆኑ የተነሳ መንግስቱ በቶሎ መመንመንና መጥፋት
የሚጀምርና መንምኖ ከመጥፋቱም በቀር መቆየት የማይ
ችል መሆኑን ለመጨመር «ይዘነጋሉ» ። ሁለተኛ ደግሞ
ወዛደሮቹ ፤ « ወዛደሩ እንደገዥው መደብ የተደራ
ጀበት መንግስት » ይፈልጋሉ ።

መንግስት ልዩ የሃይል ድርጅት ነው ፤ መንግስት
የተወሰነ መደብ መጨቆኛ የአመፅ ድርጅት ነው ።
ወዛደሩ ምን መደብ መጨቆን ይኖርበታል ? በእርግጥ፣
በዝባዡን መደብ ፣ ይኸውም ቡርዧውን ብቻ መጨ
ቆን ይኖርበታል ። ለፍቶ አደሮች መንግስት የሚያሻ
ቸው የበዝባዡን ተቃውሞ ለመደምሰስ ብቻ ነው ፣ እን
ዲሁም ይኸን ጭቆና ለመምራትና ከፍፃሜ ለማድረስ
የሚያስችል አቋም ያለው ወዛደሩ ብቻ ነው ፤ ምክንያ



ቱም ያለማቋረጥ አብዮታዊ የሆነ መደብ ወዛደሩ ብቻ
ስለሆነ ፣ ከቡርዧው ጋር በሚደረገው ትግልም ሁሉ
ንም ለፍቶ አደሮችንና ተበዝባዦችን አንድ ለማድረ
ግና ፣ ቡርዧውንም በጠቅላላ ለማስወገድ የሚችል
መደብ እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው ።

በዝባዥ መደቦች ብዝበዛ እንዳለ እንዲቀጥል ለማ
ድረግ ሲሉ ፣ ይኸውም ፣ የአብዛኛውን ብዙሃን ህዝብ
ጥቅም በመፃረር ከቁጥር ለማይገቡ ንኡሳን ክፍሎች
ራስ ወዳድ ፍላጎት ሲባል የፖለቲካ አገዛዝ ያስፈል
ጋቸዋል ። ተበዝባዥ መደቦች ሁሉንም ብዝበዛን ሙሉ
በሙሉ ለመደምሰስ ፣ ማለት ፣ ዘመናዊ የባሪያ ባለንብ
ረቶች ማለትም የመሬት ከበርቴዎችንና ካፒታሊስቶችን
የሚይዘውን ከቁጥር የማይገባ ንኡስ ክፍል በመፃረር ለብ
ዙሃኑ ህዝብ ጥቅም ሲባል የፖለቲካ አገዛዝ ያስፈል
ጋቸዋል ።

የንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች ፣ የመደብ ትግልን በመ
ደብ ስምምነት ህልም የለወጡ ፣ እነዚያ አስመሳይ ሶሻ
ሊስቶች ፣ የሶሺያሊስት ለውጥን እንኳን የተመለከቱት
በህልም መልክ — ይኸውም የበዝባዡን መደብ አገ
ዛዝ እንደ መገልበጥ ሳይሆን ግን የብዙሃኑን ክፍል
አላማ የተረዱት ንኡሳን በሰላም እጃቸውን እንደሚ
ሰጡ አድርገው ነበር ። መንግስት ከመደብ በላይ ነው
ከሚል ሃሳብ ጋር በጥብቅ የተያያዘው ይህን የንኡስ
ከበርቴ ተምኔት ፣ ለምሳሌ በ1848 እና 1871 የፈ
ረንሳይ አብዮቶች ታሪክ እና በ19ኛው ምእተ አመት
መጨረሻና በ20ኛው ምእተ አመት መጀመሪያ
ላይ በእንግሊዝ ፤ በፈረንሳይ ፣ በጣሊያን ፣ እንዲ
ሁም በሌሎች አገሮች ውስጥ በቡርዧ ካቢኔዎች «የሶ
ሻሊስት» ተሳትፎ ልምድ እንደታየው ፣ በተግባር

የለፍቶአደር መደቦችን ፍላጐቶች ወደ መካድ አም
ርቷል ።

አሁን በሩሲያ ውስጥ ፣ በሶሺያሊስት አብዮተኞችና
በሜንሼቪኮች ፓርቲዎች በኩል ትንሳኤ ያገኘውን
ይህን የንኡስ ከበርቴ ሶሺያሊዝም በመቃወም ማርክስ
ህይወቱን በሙሉ ታግሎአል ። የመደብ ትግል ትንተና
ውን በትክክል እስከ የፖለቲካ ስልጣን መርህ እስከ
የመንግስት መርህ አድርሶታል ።

የኑሮው የኤኮኖሚ ሁኔታዎች ለዚህ ተግባር ስለሚ
ያዘጋጁትና ፣ እንዲሁም ይህን ለማከናወን አመቺ ሁኔ
ታዎችና ሀይል የሚሰጡት መደብ እንደመሆኑ የቡ
ርዧውን አገዛዝ መገልበጥ ሊከናወን የሚችለው በወዛ
ደሩ ብቻ ነው ። ቡርዧው ገበሬውንና የንኡስ ከበርቴ
ውን ክፍል በሙሉ ሲሰባብርና ሲያፈራርስ ወዛደ
ሩን ግን አንድ ላይ ይበይደዋል ፣ በአንድነት
ያደራጀዋል ። ቡርዧው ከወዛደሮች ይልቅ ብዙውን
ጊዜ በይበልጥ እንጂ በማያንስ ለሚበዘብዛቸው ፣
ለሚጨቁናቸውና ለሚያደቃቸው ሆኖም ለነፃነታ
ቸው እራሱን የቻለ ትግል ለማካሄድ ለሚሳናቸው
ለፍቶ አደርና ተበዝባዦች ሁሉ ወዛደሩ ብቻ በከፍተኛ
ደረጃ የማምረት ተግባር በሚጫወተው ሚና የተነሳ
ነው መሪ ለመሆን የሚችለው ።

የመደብ ትግል ትምህርት ፣ በመንግስትና በሶሻሊ
ስት አብዮት ጥያቄ ላይ በማርክስ ሲተረጐም
የወዛደሩን የፖለቲካ አገዛዝ ፣ የርሱን የበላይ ገዢነት
ይኸውም ከማንም ጋር የማይካፈለውና በሰፊው ህዝብ
የጦር ሃይል ላይ በቀጥታ የተመሰረተ የፖለቲካ ስል
ጣንን ወደ መቀበል በግድ ያመራል። የቡርዧውን መደብ



መገልበጥ ሊሳካ የሚችለው የቡርዧውን የማይቀርና
ተስፋቢስ ተቃውሞ ለመደምሰስ ሁሉንም ለፍቶ አደር
ተበዝባዥ ሰፊ ህዝብ ለአዲሱ የኤኮኖሚ ስርአት ለማ
ደራጀት የሚችለው ወዛደሩ እራሱን ወደ ገዢው መደብ
ሲለውጥ ብቻ ነው ።

ወዛደሩ የበዝባዦችን ጉልበት ለመስበርም ሆነ አብ
ዛኛውን ህዝብ ፣ ማለት ገበሬውን ፣ ንኡስከበርቴውን ፣
ከፊል ወዛደሮችን — የሶሻሊስት ኤኮኖሚን በማደራ
ጀት ስራ ላይ ለመምራት ፣ የመንግስት ስልጣን ፣ ማእ
ከላዊ የሆነ የሃይል ድርጅትና የአመፅ ድርጅት ያስ
ፈልገዋል ።

ማርክሲዝም የወዛደሩን ፓርቲ በማስተማር ፣ ስል
ጣን በእጅ ማድረግና መላውን ህዝብ ወደ ሶሻሊዝም
ለመምራት ፣ አዲሱን ስርአት ለመምራትና ለማደራ
ጀት ያለ ቡርዧውና ቡርዧውንም በመቃወም ማህ
በራዊ ኑሮአቸውን በመገንባት ተግባር ላይ የሁሉም
ለፍቶ አደሮችና ተበዝባዦች መምህር ፣ መንገዱን የሚ
ያሳይና መሪ ሊሆን የሚችለውን የወዛደሩን ግንባር
ቀደም ያስተምራል ። ከዚህ በተቃራኒ አሁን
ትልቅ ተፅእኖ ያለው አድርባይነት ፣ ጥሩ ደመወዝ
ላላቸው ፣ ከተራ አባሎች ጋር ግንኙነት ለአጡ
በካፒታሊዝም ስር ደህና አድርገው « ለሚኖሩ » እን
ዲሁም የልደት መብታቸውን ለቅንጣት ድንች ለሚ
ሸጡ ፣ ማለትም ቡርዧውንም በመቃወም የህዝቡ
አብዮታዊ መሪነት ሚናቸውን ለከዱ ወዛደሮች ወኪሎ
ችን በወዛደሩ ፓርቲ ውስጥ እያፈራ ነው ።

« መንግስቱ ፣ ማለት እንደገዢ መደብ የተደራጀው
ወዛደር » የሚለው ይህ የማርክስ ቲዎሪ ወዛደሩ

በታሪክ ውስጥ ስለሚኖረው አብዮታዊ ሚና ፣ ካስተማረው ትምህርት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው ። የዚህ ሚና የመጨረሻ ግብ የወዛደሩ የበላይ ገዢነት ፣ የወዛደሩ የፖለቲካ አገዛዝ ነው ።

ነገር ግን ወዛደሩ መንግስት የሚፈልገው ቡርዧውን በመቃወም እንደ የአመፅ ድርጅት ልዩ ቅርፅ ከሆነ ፣ የሚከተለው መደምደሚያ ራሱን ያቀርባል ። ቡርዧው ለራሱ ሲል የፈጠረውን የመንግስት መሳሪያ በመጀመሪያ ሳያስወግድና ሳይደመስስ እንዲሁ ያለውን ድርጅት ለመፍጠር መቻሉ የሚመስል ነውን ? የኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ ወደዚህ መደምደሚያ በቀጥታ ያመራል ፣ ማርክስም የ1848—51 አብዮት ልምድ በሚያጠቃልልበት ጊዜ የተናገረው ስለዚህ መደምደሚያ ነው ።

## 2. አብዮት ሲጠቃለል ።

እኛን ስላሳሰበን የመንግስት ጥያቄ ላይ ማርክስ ከ 1848-51 የተካሄደውን አብዮት በመመልከት የደረሰበትን መደምደሚያ በሉዊ ቦናፓርት 18ኛው ብሩሜየር ውስጥ እንደሚከተለው ያጠቃልላል ።

«. . . ነገር ግን አብዮቱ የጠራ ነው ። አሁንም ቢሆን በገሀነም ውስጥ እየተጓዘ ነው ። ስራውንም የሚያከናውነው በዘዴ ነው ። በታህሳስ 2 ፣ 1851 (የሉዊ ቦናፓርት መፈንቅለ አገዛዝ በተደረገበት ቀን) ግማሽ የመሰናዶ ስራን አጠናቆ ነበር ፣ አሁን የቀረውን ግማሽ በማጠናቀቅ ላይ ነው ። በመጀመሪያ ለመገልበጥ እንዲችል ያመቸው ዘንድ የፓርላማ ስልጣንን አጠና



ከረ ። አሁን ይህን በመቀዳጀቱ የመንግስቱን መወሰኛ ስልጣን በሚገባ ያሻሽለዋል ፣ ፍፁም ወደሆነ ምንነቱ ድረስ ያጋልጠዋል ፣ ያገልለዋል ። መላ የመደምሰሻ ሀይሉን ለማከማቸት ሲል (ስርዝ ያዘጋጅ) ራሱን በራሱ ላይ በተቃውሞ በማስነሳት የጥላቻ ኢላማ ያደርገዋል ። ይህንንም የመሰናዶ ስራውን ሁለተኛ ክፍል ካጠናቀቀ በኋላ፣ አውሮፓ ከመቀመጫዋ ተነስታ በደስታ በመፈንደቅ ፣ ደህና ተይዘሻል አሮጌ ፍልፈል ! ብላ ትጮሃለች ።

«ይህ ከአያሌ ቢሮክራሲያዊና ወታደራዊ ድርጅቶች ጋር ፣ ከሰፊና ሰው ሰራሽ የመንግስቱ መሳሪያ ጋር ፣ ከግማሽ ሚሊዮን ወታደሮች ሌላ ግማሽ ሚልዮን ከሚሆኑ ባለ ስልጣኖች ጋር ይህ አሰቃቂ ተውሣካዊ አካል ፣ የፈረንሳይን ብረተሰብ አካል እንደመረብ ተብትቦ መተንፈሻዎቹን ሁሉ እንቆ የዘጋው የመንግስት መወሰኛ ስልጣን የፈለቀው የፊውዳሉ ስርአት በበሰበሰበትና ይህም መበስበስ እንዲፋጠን በረዳው በፈላጭ ቆራጭ የዘውድ አገዛዝ ጊዜ ነበር። ...» የመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት ማእከላዊነትን አዳበረ፣ « ነገር ግን በዚሁ ጊዜ የአገዛዙን ስልጣን ፣ መጠን ዓይነቱና የወኪሎችን ቁጥር አበዛ ። ናፖሊዮን ይህንን የመንግስት መሳሪያ አሻሻለው ። ህጋዊው የዘውድ አገዛዝና የሀምሌው የዘውድ አገዛዝ የበለጠ የስራ መከፋፈልን እንጂ ሌላ የጨመሩት ነገር አልነበረም ። . . .
በመጨረሻም ፣ ከአብዮቱ ጋር ለሚያደርገው ትግል ፣ ፓርላሜንታዊው ሪፐብሊክ ከመጨቆኛ

እርምጃዎቹ ጋር ፤ የአገዛዙን ይህልና
ማእከላዊነት እንዲያጠናክር ተገዶ ነበር ።
ሁሉም አብዮቶች ይህንን መሣሪያ በማ
ድቀቅ ፋንታ ፍፁም አደረጉት (ሠረዝ
ያዘጋጁ) ። በተራቸው ሥልጣን ላይ መውጣት
የሚሻሙት ፓርቲዎች ይህንን ትልቅ መንግስ
ታዊ መዋቅር መያዝ እንደ አሸናፊው ፓርቲ
ዋነኛ ምርኮ ይቆጥሩት ነበር ። (የሉዊቦናፓርት
18ኛ ብሩመር ገፅ 98—99 4ኛ እትም ሐም
ቡርግ 1907. )[10]

በዚህ ወደር የለሽ አንቀፅ ከኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ
ጋር ሲነፃፀር ማርክሲዝም ትልቅ እርምጃ ወደ ፊት
ወስድዋል ። በኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ የመንግስት ጥያቄ
የተወሰደው አሁንም ቢሆን በጣም ረቂቅ በሆነ መንገድ
እጅግ ስጣም አጠቃላይ አነጋገርና አገላለፅ ነው ። ከፍ
ብሎ በተጠቀሰው ምንባብ ጥያቄው የተወሰደው በተ
ጨባጭ ሁኔታ ነው ፣ እና መደምደሚያው በጣም ትክ
ክል ፣ ተግባራዊና ተጨባጭ ነው ። እስከ አሁን የተ
ደረጉት አብዮቶች ሁሉ የመግስቱን መሳሪያ ፍፁም አስ
ተካከሉት ፤ ዳሩ ግን መሰባበርና መደምሰስ ይኖርበታል ።

ይህ መደምደሚያ በማርክሲስት የመንግስት
ቲዎሪ ውስጥ ዋናውና መሰረታዊው ነጥብ ነው ። ባለ
ፋትና በይፋ በታወቁት የሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች
በሙሉ የተዘነጋ ብቻ ሳይሆን በታወቀው የሁለተኛው
አለም አቀፍ ቲዮሪቲሸያን ካውትስኪ (በኋላ እንደም
ናየው)የተበረዘው በትክክል ይህ መሰረታዊ ነጥብ ነበር ።

በኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ ውስጥ አጠቃላይ የታሪክ
ትምህርቶች ተጠቃለዋል ፣ ይኸውም መንግስት የመ



ደብ አገዛዝ መሆኑንና ወዛደሩም በመጀመሪያ የፖለ
ቲካ ሀይል ካልጨበጠ ፣ የፖለቲካ ገዥነቱን ካላገኘ
መንግስቱን «ወደ ተደራጀ የወዛደር ገዥ መደብ» ካልለ
ወጠ በስተቀር ወዛደሩ ቡርዧውን ለመደምሰስ የማይችል
መሆኑን እንድንገነዘብ ያስገድደናል ፤ ይህም የወዛደር
መንግስት ድልን እንደተቀዳጀ ወዲያውኑ መመንመን
ይጀምራል ፣ ምክንያቱም መንግስት አስፈላጊ ስለማይ
ሆንና የመደብ ተፃራሪዎች በሌሉበት ህብረተሰብ
ሊኖር ስለማይችል ነው ። ከታሪክ እድገት አንፃር የቡ
ርዧው መንግስት እንዴት አድርጎ በወዛደሩ መንግስት
ሊተካ እንደሚችል እዚህ ላይ አልተነሳም ።

ማርክስ በ1852 ያነሳውና መልስ የሰጠበት ጥያቄ
ይህ ነው ። የዲያሌክቲካዊ ማቴሪያሊዝም ፍልስፍ
ናውን በእርግጥ በመከተል ከ1848 እስከ 1851
ታላቅ የአብዮት አመታት ታሪካዊ ልምድን ማርክስ
መነሻ አድርጎ ወስድዋል ። ከዚህም ላይ እንደማንኛውም
ቦታ ሁሉ ፤ ትምህርቱ በአለም የጠለቀ የፍልስፍና አስተ
ሳሰብና በታሪክ የዳበረ እውቀት የተብራራበት የልምድ
ማጠቃለያ ነው ።

የመንግስት ችግር በተጨባጭ ሁኔታ ቀርቧል ፣ የቡ
ርዧው መንግስት ፣ ለቡርዧው አገዛዝ አስፈላጊ የሆ
ነው የመንግስቱ መሳሪያ ፣ ታሪካዊ አመጣጡ እንዴት
ነው ? በምን አይነት ለውጦች ስር ተካሄደ ? በቡርዧው
አብዮቶች ጊዜና የተጨቆኑት መደቦች ከወሰዱት እር
ምጃዎች ምን አይነት አዝጋሚ ለውጥ መጣ ? የመን
ግስቱን መሳሪያ በሚመለከተው ጉዳይ የወዛደሩ ተግ
ባራት ምን ምን ናቸው ?

የቡርዧው ህብረተሰብ የተለየ ጠባይ የሆነው ማእ
ከላዊ የመንግስት ስልጣን በተግባር የታየው ፍፁማ
ዊነት በወደቀበት ጊዜ ነበር ። ለዚህ አይነቱ የመንግስት
መሳሪያ ሁለት የታወቁ ዋና ዋና ተቋሞች አሉ ፣ እነ
ዚህም ቢሮክራሲውና ቋሚ ጦር ናቸው ። በስራዎቻ
ቸው ፣ ማርክስና ኤንግልስ ደጋግመው ያሳዩት እነዚህ
ሁለት ተቋሞች ከቡርዧው ጋር በሺ ክሮች እንደተ
ሳሰሩ ነው ። ይህንን ግንኙነት የማንኛውም ወዛደር
ልምድ አጉልቶ ያሳያል።የወዛደሩ መደብ ከዚህ መራራ
ልምድ ይህንን ግንኙነት ይገነዘበዋል ፣ ለዚህ ነው
የወዛደሩ መደብ የዚህን ግልፅ የሆነ የግንኙነት ትም
ህርት በቀላሉ ሊይዘውና ሊያጠፋው የሚችለው ።
የንኡስ ከበርቴው ዲሞክራቶች ግን ባለማወቅና
በግዴለሽነት መርሁን ይክዳሉ ወይም በዚህ አንፃር
ያለውን ተግባራዊ መደምደሚያ በመርሳት በግዴለሽ
ነት « በአጠቃላይ » ይቀበሉታል ።

ቢሮክራሲውና ቋሚው ጦር በቡርዧው ህብረተሰብ
አካል ላይ ያሉ «ተውሳክ ናቸው ።» ይህም ተውሳክ ህብ
ረተ ሰቡን በሚከፋፍለው ውስጣዊ ተፃርሮ የተፈጠረ፣
ሆኖም የህብረተሰቡን ዋና እስትንፋስ ሰጭ ቀዳዳዎች
የሚያንቅ ተውሳክ ነው ። ይፋዊ (በይፋ የታወ
ቀው)ሶሻል ዲሞክራሲ አሁን ጐልቶ የሚታየው የካ
ውስትካይቶች አድርባይነት ፤ መንግስት የተውሳካዊ
ነፍሳት (ፍጡር) ነው የሚለውን አስተያየት እንደ
የተለየና የግል የስርአት አልባነት ጠባይ ያየዋል (ይወ
ስደዋል) ። ሶሻሊዝምን ተሰምቶ ወደማይታወቅ ውር
ደት ያመጡትና የኢምፔሪያሊስትን ወረራ «የአባት
አገርን መከላከል» በሚለው ፅንሰ ሀሳብ አሳበው



ለሚደግፉና ለሚያፋፍሙ ባለጌዎች የዚህ ዓይነቱን
የማርክሲዝም መጣመም ለየጥቅማቸው እንደሚያው
ሉት ሳይታለም የተፈታ ነው ፤ ዞሮ ዞሮ ማወናበድ
መሆኑ ግልፅ ነው ።

ፊውዳሊዝም ከወደቀ ጀምሮ በአውሮፓ ውስጥ እን
ደታየው የቢሮክራሲውና የወታደሩ ተቋም የደረጁት ፣
የተጠናከሩትና የረቀቁት በቡርዧው አብዮቶች ጊዜ
ነበር። ለከፍተኛው ገበሬ፣ ባለ እጅ ፣ ነጋዴና ለመሳሰሉት
መደብ ከሌላው ህዝብ በላይ ምቾትና ክብር ያለው ስራ
ስለሚያስገኝላቸው በዚህ መሳሪያ አማካኝነት በተለይ
ወደ ትላልቅ ቡርዧዎች የተሳሰቡና ከእነሱም ጥገኛ የሆ
ኑት ንኡስ ከበርቴዎች ናቸው ። ከየካቲት 27 ፣ 1917 በኋላ
በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በሩሲያ የሆነውን እንይ ።
ለድል መቺዎች (ብላክ ሀንድረድስ) አባላት ይሰጡ
የነበሩት ከፍተኛ ስራዎች አሁን ለካዴቶች፣ ለሚንሺቪ
ኮችና ለሶሻሊስት አብዮተኞች ይሰጡ ጀመር ። ማንም
የጥገና ለውጥ ለማምጣት አጥብቆ ያሰበ አልነበረም ፤
የተደረገው ሙከራ ሁሉ « የህገ መንግስት ጉባኤ
እስኪሰበሰብ» ድረስ ለማስተላለፍና ፣ ጦርነቱም እስ
ኪያልቅ ድረስ ጉባኤ እንዳይሰበሰብ ነበር! ነገር ግን
የሚኒስትሮችን ፣ የምክትል ሚኒስትሮችን ፣ የክፍለ ሀገር
ሀገረ ገዢዎችን ወ. ዘ. ተ. ቦታዎች ለመከፋፈል የህገ
መንግስቱ ጉባኤ እስኪደረግ አልጠበቀም ! መንግስ
ቱን ለመመስረት የነበረው ጨዋታ ሁሉ በጠቅላላ በሀገ
ራቱ ውስጥ ከማዕከላዊው መንግስት እስከ እያንዳንዱ
መምሪያ ድረስ «የቀረውን ርዝራዥ» መከፋፈል ነበር ።

የካቲት 27 እና ነሐሴ 27,1917 መካከል የነበረው
የስድስት ወራት በሚከተለው ተጨባጭ ሁኔታ ሊጠ
ቃለል ይችላል ። የጥገና ለውጥ ተዘንጋ ፣ የስልጣን

ክፍልፍል ተፈፀመ ፣ በስልጣን ክፍፍሉ የተሰሩት «ስህተቶች» ጥቂቶችን እንደገና በማከፋፈል ታረሙ ።

ቢሮክራሲው እያደር በቡርዧውና በንኡስ ከበርቴው ፓርቲዎች(በሩሲያ ውስጥ እንደተደረገው በካዴቶች ፣ በሶሺያሊስት አብዮተኞችና በሜንሸቪኮች) መካከል «እየተከፋፈለ» ሲሄድ የጭቁን መደቦችና የሚመራቸው የወዛደሩ መደብ ከመላው ቡርዧ ህብረተሰብ ጋር የማይታረቅ ጥላቻ እንዳላቸው አወቁ ። ለዚህ ነው ሁሉም የቡርዧ ፓርቲዎች ዲሞክራቲክና «አብዮተኛ ዲሞክራቲክ» የሆኑት እንኳን ሳይቀሩ የወዛደሩን አብዮት ለመግታት የጭቆና እርምጃቸውን የሚያጐሉትና የጭቆና መሳሪያቸውን፤ ይህም ያው የታወቀውን የመንግስት መሳሪያ የሚያጠነክሩት ። እነዚህም ድርጊቶች አብዮቱ ያለውን የመደምሰስ ሃይል ሁሉ አጠናክሮ ፣ የመንግስቱን መሳሪያ ማስተካከል ሳይሆን ፣ እንዲሰባብረውና እንዲደመሰሰው ያስገድዱታል ።

ችግሩ በዚህ አይነት እንዲቀርብ ያደረገው በሎጂካዊ አስተሳሰብ ሳይሆን ከ1848-51 ከተገኘው ህያው ልምድ የተነሳ ነው ። በ1852 ማርክስ የሚደመሰሰው የመንግስት መሳሪያ በምን መተካት አለበት የሚለውን ጥያቄ በተጨበጠ መልክ ገና ያላነሳው ፣ መነሻ የሚሆን የታሪካዊ ልምድ ስላልነበረው ነበር ። በ1871 አይነተኛ የሆነው የጊዜው ጥያቄ ከዚያ በፊት ምንም ልምድ ስላልነበረ ችግሩ መፍትሄ ሳያገኝ ቀይቶ ነበር ። በ1852 በሳይንሳዊ ምርምር ትክክለኛነት መሰረት ለማድረግ የቻለው የወዛደሩ አብዮት «ያለውን ሃይል ሁሉ በማጠናከር» የመንግስቱን ሃይል



«ለመደምሰስና» የአገዛዙን መሳሪያ «ለመሰባበር» መቃረቡን ነበር ።

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የማርክስን ልምድ ፣ ጥናቶችና መደምደሚያዎች ከ1848—51 የሶስት አመታት የፈረንሣይ ታሪክ ይበልጥ ስፋት ባለው መስክ በስራ ላይ ለማዋል ይቻላል ብሎ ማጠቃለል ትክክል ነውን? ይህን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት እስቲ መጀመሪያ የኤንግልስን አስተያየት እናስታውስ ፣ ከዚያ በኋላ ጭብጥ እውነቶችን እንመርምር ። በአስራ ስምንተኛው ብሩሜየር በሶስተኛው እትም መግቢያ ላይ ኤንግልስ እንደፃፈው ፤

« ፈረንሳይ ከማንኛውም አገር የበለጠ ፣ ታሪካዊ የመደብ ትግሎች በየጊዜው እስከ ውሳኔ ደረጃ ድረስ ውጊያ የተደረገባት ምድር ናት ፣ በዚህም የተነሳ በውስጡ የሚንቀሳቀሱትና ውጤቶቻቸውም የሚጠቃለሉበት ተለዋዋጭ ፖለቲካዊ ቅርፆች እጅግ በጣም ግልፅ በሆኑ መዋቅሮች ታትመዋል ። በመካከለኛው ዘመናት የፊውዳሊዝም እምብርት በመሆን ከሬናይስንስ ጀምሮ ለጠንካራና አንድ ለሆነ የዘውድ አገዛዝ ሞዴል የሆነችው ፈረንሳይ ፣ በታላቁ አብዮት ፊውዳሊዝምን አጠፋችና በሌላ የአውሮፓ ምድር ወደር የሌለውና የአንደኛ ደረጃ ጥራት ያለው ጠንካራ የቡርዧ አስተዳደር መሰረተች ። ታዳጊው ወዛደር ገዢውን በመቃወም ያደረገው ትግል በሌላ ቦታ ታይቶ የማይታወቅ የከረረ ፎርም ይዞ ብቅ አለ ። » (ገፅ 4 ፣ 1907 እትም)

የመጨረሻው አረፍተ ነገር ያረጀ ነው ፣ ለምን ቢባል ከ1871 ጀምሮ የፈረንሳይ ወዛደር አብዮታዊ ትግል

በመቀዝቀዝ ላይ ነው ፣ የአብዮቱ መቀዝቀዝ ቢረዝምም በመጪው የወዛደሩ አብዮት ፈረንሳይ እንደገና እስከመጨረሻው የመደብ ትግል ማካሄድ የምትችል አገር ለመሆን የመቻልዋን እድል ፈፅሞ አያግድም ።

እስቲ ፣ የሆኖ ሆኖ ፣ በአስራ ዘጠነኛው ምእት አመት መጨረሻና በሃያኛው ምእት አመት መጀመሪያ ላይ ወደፊት የገፉ አገሮችን ታሪክ በአጭሩ እንቃኝ ። ያው ሂደት ፣ በዛ ባሉ የተለያዩ ቅርፆች ፣ ሰፋ ባለ መስክ በይበልጥ እያዘገመ በመጓዝ ላይ መሆኑን እናያለን በአንድ በኩል የሪፑብሊካዊ አገሮችም ሆነ (ፈረንሳይ ፣ አሜሪካ ፣ ሲዊዘርላንድ) የዘውድ አገዛዝ አገሮች (እንግሊዝ፤ በመጠኑም ጀርመን ፣ ኢጣሊያ ፣ የእስካንድኔቢያ አገሮች ወዘተ ) የ « ፓርላሜንታዊ ስልጣን » እድገት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቡርዧ ህብረተሰብ መሰረቶች ሳይለወጥ የቢሮ ስልጣኑን በመከፋፈልና እንደገና መልሶ በመከፋፈል እና በመጨረሻም « የማስፈፀሚያ ስልጣንን » ቢሮክራቲክና ወታደራዊ አቋሙን ፍፁም በማድረግና በተለያየ ንኡስ ከበርቴዎች የሚካሄደው የስልጣን ሽሚያ ነበር ።

እነዚህ ፀባዮች በአጠቃላይ ለመላ ካፒታሊስት መንግስታት ዘመናዊ አዝጋሚ ለውጥ በሙሉ ተመሳሳይ ለመሆናቸው ጭራሽ ጥርጥር የለውም ። ከ1848—51 ባሉት ሶስት አመታት ውስጥ ፈረንሳይ በመላ ካፒታሊስት አለም የተለመዱትን የእድገት ሂደቶች በፈጣን፣ ግልፅና በተከማቸ መልክ አሳይታለች ።

ኢምፔሪያሊዝም በተለይ የባንክ ካፒታል ዘመን፣የታላላቅ ካፒታሊስትች ሞኖፖሎች ዘመን፣ የሞኖፖል ካፒታሊዝም ወደ መንግስታዊ ሞኖፖል የሚያድግበት ዘመን በዘውድ አገዛዝና በመጨረሻም ነፃ ሪፐብሊካዊ አገ



ርም በወዛደሩ ላይ የጭቆና እርምጃዎችን ከማጠንከር ጋር የተያያዘ የቢሮክራሲያዊና የወታደራዊ አቋም ከመቼም ይበልጥ ያደገበት « የመንግስት መሳሪያ » መጠንከር በሀይል አሳይቷል ።

ከ1852 ይበልጥ አሁን የአለም ታሪክ ያለጥርጥር የመንግስት መሳሪያን «ለማጥፋት» የወዛደሩን አብዮት « መላሃይሎች ክምችት» ወደር በሌለው ስፋት እየመራ ነው ።

ወዛደሩ በእርሱ (የመንግስት መሳሪያ) ምትክ ምን እንደሚተካ ከፓሪሱ ኮሚዮን የተገኘው ጠቃሚ የሆነው ትምህርታዊ ሀሳብ (ማቴሪያል) ታይቷል ።

### 3. የጥያቄው አቀራረብ ፣ በማርክስ በ-1852 *

በ1907፣ሜሪንግ ፣ «በኖየ ሣይት[11]» መፅሔት (ቅፅ 25 ፤ 2 ፤ ገፅ ፤ 164) ማርክስ መጋቢት 5, ፣ 1852 ለቫይዴሜየር ከፃፈው ደብዳቤ አስተዋፅኦ አሳትሞ ነበር ይህ ደብዳቤ ፣ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ሌላ የሚከተለውን የታወቀ ጥናት ይዟል ።

> « እንደ እኔ ከሆነ ፣ በዘመናዊ ህብረተሰብ የመደቦች መኖርም ሆነ በመካከላቸው ያለውንም ትግል በማሳየት በኩል ምንም ድርሻ የለኝም ። ከእኔም በፊት የቡርዧ ታሪክ ፃፊዎች የዚህን የመደቦች ትግል ታሪካዊ እድገትና የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች ደግሞ የመደቦችን የኤኮኖሚ አቋም አብራርተዋል፣ እኔ ለማረጋገጥ ያደረግሁት አዲስ ነገር (1) የመደቦች መኖር በምርት እድገት ውስጥ ከተለየ ታሪካዊ ደረጃዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን (2) የመደብ ትግል የግድ ወደ ወዛደሩ የበላይ ገዢነት እንደሚያመራ፤

* ሁለተኛው እትም ላይ የተጨመረ

(3) ወደ መደቦች መጥፋትና ወደ መደብ አልባ ህብረተሰብ የሚያሸጋግረው ይኸው የበላይ ገዢነት ብቻ መሆኑን ነው . . . . »[12]

በነዚህ ቃላት ማርክስ ፣ በመጀመሪያ በአስገራሚ ጥራት በርሱና በታወቁት አዋቂ የቡርዧ ተመራማሪዎች መካከል ያለውን ዋናና ስር ነቀል ልዩነት ፤ ሁለተኛ ፣ ስለመንግስት እርሱ ያስተማረውን ቁም ነገር ለመግለፅ ችሏል ።

ከማርክስ ትምህርቶች ዋናው ነጥብ የመደብ ትግል ነው እየተባለ ብዙ ጊዜ ተነግሯል ፣ ተፅፏልም ፤ ነገር ግን ይህ እውነት አይደለም ። ስለሆነም ብዙ ጊዜ ከዚህ እውነት ካልሆነ ነጥብ አድርባይ የማርክሲዝም ብረዛ ፣ ይመጣል ። ብረዛውም የሚደረገው በቡርዧው ተቀባይነት እንዲያገኝ ተደርጐ ነው ። የመደብ ትግል ቲዎሪ የተፈጠረው በማርክስ ሳይሆን ከማርክስ በፊት በቡርዧው ነበር ፣ ባጠቃላይ አነጋገርም በቡርዧው ተቀባይነት አለው ። የመደብ ትግልን ብቻ የሚቀበሉት ማርክሲስቶች ሆነዋል ማለት አይደለም ፤ ገና በቡርዧው አስተሳሰብና ፖለቲካ ድንበሮች ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ ። ማርክሲዝምን በመደብ ትግል ትምህርት መወሰን ማርክሲዝምን መግታት ፣ ማምታታት ፣ ለቡርዧው ተቀባይነት ወደሚኖረው ደረጃ ዝቅ ማድረግ ነው ። የመደብ ትግልን እስከወዛደሩ የበላይ ገዢነት የሚቀበል ብቻ ነው ማርክሲስት ። በማርክሲስትና በተራ ንኡስ (እንዲሁም ትልቅ) ቡርዧ መካከል ያለው እጅግ በጣም ጥልቅ ልዩነት መሰረቱ ይህ ነው ። ማርክሲዝምን በእርግጥ መረዳትና መቀበል የሚፈተንበት መለኪያ ይህ ነው ፤ የአውሮፓ ታሪክ ይህን ጥያቄ በተግባራዊ



መንገድ በወዛደሩ ፊት ሲያስቀምጥ አድርባዮችና ጠጋኞች ብቻ ሳይሆኑ መላ « ካውትስካይቶች » (በጥገናዊነትና በማርክሲዝም መካከል የሚያወላውሉ ሰዎች) የወዛደሩን የበላይ ገዢነት የማይቀበሉ አሳዛኝ ከዳተኞችና የንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች መሆናቸው አያስደንቅም ። በነሐሴ 1918 ማለትም ከዚህ መፅሀፍ የመጀመሪያ እትም ከብዙ ጊዜ በኋላ የታተመው ፣ የወዛደሩ የበላይ ገዢነት የተሰኘው የካውትስኪ መፅሄት ንኡስ ከበርቴዎች ማርክስዝምን በቃላት እንዴት እንደሚቀበሉና በተግባር ከመሰረቱ እንዴት እንደሚያጣምሙትና እንደሚያወግዙት የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው ። (የወዛደሩ አብዮትና ከሃዲው ካውትስኪ ፔትሮግራድና ሞስኮ ፣ 1918 ፓምፍሌቱን ይመልከቱ) ።

የአሁኑ ጊዜ አድርባይነት ዋንኛው ወኪል ፣ የሆነው የቀድሞ ማርክሲስት ፣ ካውትስኪ እላይ በተጠቀሰው በማርክስ ከተመደበው የቡርዧ አቋም ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማል ፣ ይህም አድርባይነት የመደብ ትግል ማወቁን በቡርዧ ግንኙነቶች ክልል ይወስነዋል ። (በዚህ ክልል ውስጥ ፣ ከራሱ ወሰን ውስጥ « በመርህ » አንድም የተማረ ሊብራል እንኳን የመደብ ትግሉን አልቀበልም አይልም !) አድርባይነት የመደብ ትግልን መቀበል አቢይ ነጥብ እስከሆነው ፣ ከካፒታሊዝም እስከ ኮሚዩኒዝም የሽግግር ጊዜ ድረስ ፣ እስከ ቡርዧ መውደቅና ጭራሽ መደምሰስ ድረስ አያስፋውም ። እንደ እውነቱ ፣ ይህ ክፍለ ጊዜ ታይቶ የማይታወቅ አስቸጋሪ ቅርፆች ያሉት ሀይለኛ ደም መፋሰስ ያለበት የመደብ ትግል ክፍለ ጊዜ ነው ፣ በዚህ ምክንያት በዚህ ክፍለ ጊዜ መንግስቱ

የግድ በአዲስ መንገድ ዴሞክራሲያዊ ( ለወዛደሩና ንብረት አልባ ለሆኑት በአጠቃላይ) የሆነና በአዲስ መንገድ የበላይ ገዥ (በቡርዧው ላይ) መሆን አለበት ።

ለመቀጠል ። በመንግስት ላይ በማርክስ ትምህርት ይዘት ተክነዋል የሚባሉት የአንድ መደብ ፈላጭ ቆራጭነት አስፈላጊነት ፤ በአጠቃላይ ለማንኛውም የመደብ ህብረተሰብ ብቻ ሳይሆን፤ ቡርዧውን ለገለበጠ ወዛደር ብቻ ሳይሆን ፤ ነገር ግን ካፒታሊዝምን ከ « መደብ አልባ ህብረተሰብ » ከኮሚዩኒዝም ለሚለየው መላው ታሪካዊ ክፍለ ጊዜም አስፈላጊነቱን የሚረዱትብቻ ናቸው ። የቡርዧ መንግስታት ቅርፆች እጅግበጣም ይለያያሉ ፤ ነገር ግን ይዘታቸው አንድ ነው ፤ የነዚህ ሁሉ መንግስታት ፤ ምንም አይነት ቅርፅ ቢኖራቸው ፤ ዞሮ ዞሮ የማይቀር የቡርዧ የበላይ ገዢነት ናቸው ። ከካፒታሊዝም ወደ ኰሚዩኒዝም ሽግግር በርግጥ በጣም ብዙና የተለያዩ ፖለቲካዊ ቅርፃች ከመያዙ በስተቀር ሌላ ሊሆን አይችልም ፤ ነገር ግን ይዘቱ የግድ አንድ ይሆናል ፤ የወዛደሩ የበላይ ገዢነት ።

* * *



ምዕራፍ 3

# የ1871 የፓሪስ ኰሚዩን ልምድ ፡ የማርክስ ትንተና

## 1. የኰሚዩናርዶች ሙከራ ጀግንነቱ ከምን ላይ ነው ያለው ?

በ1870 በልግ ውስጥ ፤ ከኮሚዩን ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ፤ መንግስቱን ለመገልበጥ የሚደረገው ማንኛውም ሙከራ ተስፋ የመቁረጥ ሞኝነት እንደሚሆን ማርክስ የፓሪሱን ወዛደሮች ማስጠንቀቁ በሚገባ የታወቀ ነው። ሆኖም በመጋቢት 1871 ፤ በወዛደሮች ላይ የሞትና የሽረት ጦርነት የግዴታ ሲመጣባቸውና እነሱም ከተቀበሉት በኋላ የህዝብ መነሳሳት እውነት ከሆነ በኋላ ፤ መጥፎ ትንቢቶች ቢኖሩም እንኳን ፤ ማርክስ የወዛደሩን አብዮት በከፍተኛ ስሜት ተቀበለው ። ስለ ወዛደሮቹና ማርክስ እንደፕሌካኖብ «ያለ ጊዜው» የመጠን ንቅናቄ በግትርነትና በጭፍን የማወገዝ ዝንባሌ አልወሰደም መጥፎ ዝና ያለው ሩሲያዊው የማርክሲዝም ከሀዲ ፤ ፕሌካኖብ ፤ በህዳር 1905 የወዛደሮችንና ገበሬዎችን ትግል በማበረታታት ፃፈ ፤ ግን ከታህሳስ 1905 በኋላ በሊብራልሁኔታ «መሳሪያ ማንሳት አልነበራቸውም» ብሎ ጮኸ ።

ማርክስ ግን «መንግስተ ሰማያትን» በማጥቃት መድረሻ ስላሳጡት ኰሚዩናርዶች ጀግንነትና ስሜት፤እርሱ እንደገለፀው ከፍተኛ ብቻ አልነበረም።ምንም እንኳን ህዝባዊ አብዮታዊ ንቅናቄው ግቡን ባይመታም፤በውስጡ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ታሪካዊ ልምድን ፤ ለአለም ወዛደሮች አብዮት መጠነኛ እድገትን እንደያዘና በመቶ ከሚቆጠሩ

ፕሮግራሞችና ውይይቶች የበለጠ ዋጋ ያለው ተግባራዊ
እርምጃ እንደሆነ ማርክስ አይቷል ።
ይህን ልምድ ለመተንተን ፣ ከእሱም ታክቲካዊ ትምህርቶ
ችን ለመውሰድ የርሱን ቲዎሪ በዚህ አንፃር እንደገና
ለመመርመር ፣ ማርክስ የገጠመው ችግር ይህነበር ።

በኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ
ያሰበውን አንድ « እርማት » ብቻ ማርክስ በፓሪስ ኮሚ
ዩናርዶች አብዮታዊ ልምድ መሰረት አደረገ ።

በሁለቱም ደራሲዎች የተፈረመው የኰሚዩኒስት
ማኒፌስቶ አዲሱ የጀርመን እትም የመጨረሻው መቅ
ድም ቀኑ ሰኔ 24 ቀን 1872 የሚል ነው ። በዚህ
መቅድም ውስጥ ደራሲያኑ ማርክስና ኤንግልስ የኰ
ሚዩኒስት ማኒፌስቶ ፕሮግራም «በአንዳንድ ነጥቦች»
ጊዜው ያለፈበት ሆኗል ፣ ይላሉ ። ከዚያም በመቀጠል ፣
« በኰሚዩኑ በተለይ የተረጋገጠ አንድ ነገር አለ
ይኸውም « የወዛደሩ መደብ የተዘጋጀውን የመ
ንግስት መሳሪያ በቀላሉ ጨብጦ ለእራሱ አላማ
ዎች ሊያውለው አይችልም »[13]

ፀሀፊዎቹ በነጠላ ጥቅስ ውስጥ ያለውን ሀረግ የወ
ሰዱት በፈረንሳይ የእርስ በርስ ጦርነት ከተባለው የማ
ርክስ መፅሀፍ ነው ።

ስለዚህ ማርክስና ኤንግልስ የፓሪስ ኰሚዩንን እንደ
አንድ ዋናና መሰረታዊ ትምህርት ፣ ታላቅ ጠቃሚነት
እንዳለው በመቁጠር ከኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ ውስጥ
እንደ ከፍተኛ እርማት አስገቡት ።

በእርግጥም በአድርባዮች የተጣመመውና ፣ ከኰሚ
ኒስት ማኒፌስቶ አንባቢዎች በዘጠኝ አስረኛ ቀርቶ



በዘጠና ዘጠኝ መቶኛው ምናልባት ያልታወቀው ይኸው
ከፍተኛ እርማት መሆኑ በጣምግልፅ ነው ። ስለዚህ መጣ
መም በተለይ ስለመጣመም በተመደበው ምእራፍ ውስጥ
ወደፊት በይበልጥ እንመለከተዋ ለን ። ከላይ ስለተጠ
ቀሰው የማርክስ ዝነኛ አባባል አሁን ያለው ፣ ስድ
«ትርጉም» እንደ ከሳሾቹ አባባል የመንግስት ስልጣንን
ከመያዝ በተቃራኒ ማርክስ በዝግተኛ እድገት ሀሳብ
ወዘተ ፣ . . ላይ ያተኩራል የሚለውን እዚሁ ላይ መመ
ልከቱ በቂ ነው ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ጉዳዩ በትክክል የዚህ ተቃ
ራኒ ነው ። የማርክስ አስተሳሰብ የወዛደሩ መደብ « የተ
ዘጋጀውን የመንግስት መሳሪያ » መስበር ፣ ማንኰታኰት
አለበት እንጂ እሱን በመያዝ ብቻ ራሱን መወሰን የለ
በትም የሚል ነው ።

በሚያዝያ 12 ፤ 1871 ማለትም ልክ በኰሚዩኑ ጊዜ
ማርክስ ለኩግልማን የሚከተለውን ፃፈ ፤
« የኔን አስራ ስምንተኛው ብሩሜየር የመጨረሻ
ምእራፍ ብትመለከቱ የፈረንሳይ አብዮት የሚቀጥ
ለው ሙከራ ፣ ወታደራዊ ቢሮክራቲክ መሳሪያውን
እንደቀድሞው ከአንድ እጅ ወደ ሌላ ማዛወር ሳይ
ሆን መሰባበር ነው ማለቴን ታገኛላችሁ (ሰረዝ የማ
ርክስ) ። ይህም በአህጉሩ ላይ ለእውነተኛ ህዝባዊ
አብዮት የመጀመሪያው ተፈላጊ ሁኔታ ነው ።
ጀግኖች የፓርቲ ጓደኞቻችንም በፓሪስ የሞከሩት
ይህንኑ ነው ። »

(ኖየ ሳይት ቅፅ 20, 1 ፡ 1901—2 ፣ ገፅ 709)[14] (ማር
ክስ ለኩግማን የፃፋቸው ደብዳቤዎች ከሁለት ባላ
ነሱ እትሞች በሩሲያ ቋንቋ ወጥተዋል ፣ ከነሱም አን

ደኛውን እኔ አርሜና አስተካክዬ መቅድም ሰጥቼዋ ለሁ ። 15)

"ወታደራዊ ቢሮክራቲክ መሳሪያውን ለመሰባበር" የሚሉት ቃላት በአብዮት ወቅት ከመንግስት ጋር በሚ ኖረው ዝምድና ስለወዛደሩ ተግባር የማርክሲዝምን ዋነኛ ትምህርት በአጭሩ ይገልፃሉ ። አሁን መረሳት ብቻሳይሆን ፥ ባለው የካውትስካይት የማርክሲዝም «ትርጉም» በግልፅ የተጣመመው ይኸው ትምህርት ነው ።

ማርክስ አስራ ስምንተኛውን ብሩሜዬር ስለመጥቀሱ ተፈላጊውን ምንባብ በሙሉ ከዚህ በላይ ጠቅሰናል ።

ከላይ በተጠቀሰው የማርክስ ምንባብ ውስጥ ፥ በተ ለይ ሁለት ነጥቦችን ማስተዋሉ ጥሩ ነው ። አንደኛ የር ሱን መደምደሚያ በአህጉሩ ይወስናል ። በ1871 እንግሊዝ ወታደራዊ መሳሪያና በከፍተኛ ደረጃም ቢሮክራሲ ያልነ በረባት ገና ንፁህ የካፒታሊስት አገር ሞዴል በነበረች በት ጊዜ ይህ የሚገባት ጉዳይ ነበር። ስለዚህ «ማርክስ የተ ዘጋጀውን የመንግስት መሳሪያ » ማጥፋት የመጀመሪያ ተፈላጊ ሁኔታ ሳይሆን አንድ አብዮት እንዲያውም ህዝባዊ አብዮት እንኳን ሊመጣ የሚችል የመሰለባትን በእርግጥም ይቻል ነበር ፥ እንግሊዝን አልጨመረም ።

ዛሬ በ1917 ፥ በመጀመሪያው ታላቅ የኢምፔሪያሊስት ጦርነት ዘመን ፥ ይህ ከማርክስ የተደረገው ልዩ መግለጫ ከእንግዲህ ዋጋ ያለው አይደለም ። ሚሊቴሪዝምና ቢሮ ክራሲ ካለመኖሩ አንፃር ለአንግሎ ሳክሰን «አርነት» ታላላቆቹና የመጨረሻ ተወካዮች የነበሩት አሜሪካና እንግሊዝ ሁለቱም አሁን ማንኛውንም ነገር በስራ ቸው በሚያደርጉትና ማንኛውንም ነገር ረግጠው በሚ



ይዙት የጠቅላላው የአውሮፓ አስቀያሚ የወታደራዊ ቢሮክራቲክ ድርጅቶች ማጥ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ሰምጠ ዋል። ዛሬ በእንግሊዝና በአሜሪካን «ለማንኛውም ህዝባዊ እውነተኛ አብዮት የመጀመሪያው ተፈላጊ ሁኔታ» ያለ ውን የመንግስት መሳሪያ (በ1914 እና 1917 መሀከል በእነዚህ አገሮች ውስጥ ወደ አጠቃላይ « የአውሮፓ ውያን » ኢምፔሪያሊስት ደረጃ የተሻሻለውን) ማን ኰታኰትና ማውደም ነው—።

ሁለተኛ «ለማንኛውም እውነተኛ ህዝባዊ አብዮት የመ ጀመሪያው ተፈላጊ ሁኔታ የወታደራዊ ቢሮክራቲክ የመንግስት መሳሪያ መውደም ነው የሚለውን የማር ክስ እጅግ መሰረታዊ የሆነ አስተያየት በተለይ አተ ኩሮ መመልከት ያስፈልጋል ። ይህ « የህዝባዊ » አብ ዮት የሚለው ሃሳብ ከማርክስ ሲመጣ እንግዳ ይመስላል፥ ስለዚህም የሩሲያ ፕሌካኖቫይቶችና ሜንሸቪካውያን እንደ ማርክሲስት ለመቆጠር የሚፈልጉት የስትሩቭ ተከታዮች የዚህ አይነቱን አባባል ከማርክስ በኩል «የብ እር ማዳለጥ » ነው በማለት ምናልባት ይገልፁት ይሆናል ። ማርክሲዝምን ወደ የደኸዩ «ሊብራል» በብ ረዛ ዝቅ ስላ አደረጉት ለእነሱ በቡርዧውና በወዛደሩ አብዮት መካከል ካለው ልዩነት በላይ ምንም ነገር የለም ለዚያውም ያንን ልዩነት የሚረዱት ፈፅሞ ህይወት የለሽበሆነ መንገድ ነው ።

የሃያኛውን ምእተ አመት አብዮትቶች እንደ ምሳሌ አድርገን ከወሰድናቸው ፥ የፖርቹጋልና የቱርክ አብዮ ቶች የቡርዧ አብዮቶች መሆናቸውን በእርግጥ መቀ በል ይኖርብናል ። ሆኖም ፥ ከሁለቱ በአንዱም ውስጥ እንኳን ሰፊው ህዝብ ፥ ብዙሃኑ ክፍል ፥ በንቁ ተሳትፎ ራሱን ችሎ የራሱን የኤኮኖሚና የፖለቲካ ጥያቄዎች

ጉልቶ በሚታይ ደረጃ [illegible]
ቸውም ቢሆን « ህዝባዊ » አብዮት አይደሉም ። በተቃራኒው የፖርቹጋልና የቱርክ አብዮቶች አንዳንዴ እንዳጋጠማቸው ምንም እንኳ የ1905 እስከ 1907 የሩሲያ ቡርዧ አብዮት እስከዚህ « ጉልህ » ድሎችን ባያሳይም ሰፊው ህዝብ ፥ ብዙሃኑ ክፍል ፥ በብዝበዛና በጭቆና የተረገጠው በጣም ዝቅተኛው የህብረተሰቡ ክፍል በአብዮቱ ወቅት ሁሉ የራሳቸውን ጥያቄና በሚያፈራርሰው አሮጌው ህብረተሰብ ምትክ በራሳቸው መንገድ አዲስ ህብረተሰብን ለመገንባት በሚያደርጉት በራሳቸው ሙከራ ስለአሳወቁ ። ያለ ምንም ጥርጥር « እውነተኛ ህዝባዊ » አብዮት ነበር ።

በአውሮፓ በ1871፥ ወዛደሩ ከህዝቡ ብዙሃኑ ክፍል የሆነበት በአህጉሩ ውስጥ አንድም አገር አልነበረም ። አንድ «ህዝባዊ» አብዮት ፥ ማለት በእርግጥ ብዙሃኑን ወደ ራሱ ስቦ በሰፊው የያዘ ፥ እንደዚህ ሊሆን የሚችለው ሁለቱንም ወዛደሩንና ገበሬውን ሲያጠቃልል ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ «ህዝብ» የሚባሉት እነዚህ ሁለት መደቦች ናቸው። «ወታደራዊ ቢሮክራቲክ የመንግስት መሳሪያ» ስለሚጨቁናቸው፥ስለሚረጋግጣቸው፥ስለሚበዘብዛቸው እነዚህ ሁለት መደቦች አንድነት አላቸው። ይህን መሳሪያ <u>መሰባበር</u> ፥ <u>ማንኰታኰት</u> በእርግጥ «የህዝቡን» የብዙሃኑን ፥ ህብረት የወዛደሩንና የአብዛኛውን ገበሬ ጥቅም የሚጠብቅ ነው ። በደሀ ገበሬውና በወዛደሩ መካከል ነፃ የሆነ ህብረት እንዲኖር ይህ «የመጀመሪያ ሁኔታ» ነው ፤ ያለዚህ ህብረት ዲሞክራሲ ያልፀና ነው ፥ ሶሻሊስት ለውጥም ሊኖር አይችልም ።

በሚገባ እንደሚታወቀው በተለያዩ የውስጥና የውጭ ምክንያቶች የተነሳ ከግቡ ባይደረስም ፥ የፓሪሱ ኰሚ



ዩን በእርግጥ ወደዚህ አይነቱ ህብረት እያመራ ነበር ።

በዚህም የተነሳ ፥ ማርክስ ስለ « እውነተኛ ህዝባዊ አብዮት » ሲናገር የንኡስ ከበርቴውን ልዩ ጠባይ ፍፁም ሳይረሳ (ስለእነሱ ብዙ ጊዜያት በጣም ብዙ ተናግሯል) በ1871 ከእንግሊዝ በስተቀር በአውሮፓ አህጉር በአብዛኞቹ ሀገሮች ውስጥ የነበሩትን የመደብ ሃይሎች አሰላለፍ በሚገባ ተመልክቷል ። በሌላ በኩል የመንግስት መሳሪያውን « መሰባበር» ለሁለቱም ፥ ለወዛደሮቹና ለገበሬዎች ጥቅም ተፈላጊ ስለሆነ ፥ ያስተባብራቸዋል ፥ « ተውሳኩን » የማስወገዱንና በአዲስ ነገር የመተካቱን የጋራ ተግባር ከፊታቸው ያስቀምጣል ብሏል ።

የሚተካው በእርግጥ በምንድን ነው ?

## 2. <u>የተንኰታኰተው የመንግስት መሣሪያ በምንድን ነው የሚተካው ?</u>

በ1847 <u>በኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ</u> ውስጥ ለዚህ ጥያቄ የማርክስ መልስ ገና ፍፁም ረቂቅ ነበር ፥ ወይም በይበልጥ በትክክል ለመናገር ችግሮችን የሚያመለክት እንጂ ሊከናወኑ የሚችሉበትን መንገዶች የሚጠቁም አልነበረም ። <u>በኰሚዩኒስት ማኒፌስቶ</u> ውስጥ የተሰጠውን መልስ ይህ መሳሪያ የሚተካው «ዲሞክራሲ በመመስረት» «እንደ ገዢ መደብ በተደራጀ ወዛደር » ነው የሚል ነበር ።

ማርክስ በተምኔት ውስጥ አልዘቀጠም ፥ ይህ የወዛደሩ እንደገዥ መደብ መደራጀት ምን አይነት ልዩ ቅርፆች ይይዛል፥ በምን አይነት መንገድ በፍፁም ከማያወላውል « ለዲሞክራሲ መመስረት » ንቅናቄ

ጋር ይህ ድርጅት ይዋሀዳል ለሚለው ጥያቄ የሰፈው ልምድ መልሱን እንዲሰጥ ነው የጠበቀው ።

ማርክስ የፈረንሳይ የእርስ በርስ ጦርነት በተባለው መፅሀፍ ውስጥ የኰሚዮን ልምድ ፣ የመነመነ ቢሆንም በጣም ጥንቁቅ የሆነ ትንታኔ አድርጐበታል ።

ከዚህ ስራ ውስጥ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ምን ባቦች እስኪ እንጥቀስ ፣ « በመሀከለኛው ክፍለ ዘመን በመፍለቅ ፣ የትም ፡ ቦታ ቋሚ ጦር ሰራዊት ፣ ፖሊስ ፣ ቢሮክራሲ ካህናት ፣ ፍርድ ቤቶች ያሉት ማእከላዊው የመንግስት ስል ጣን » በአስራ ዘጠነኛው ምእተ አመት ውስጥ አደገ ። በካፒታልና በወዝ መካከል ካለው የመደብ ተፃራሪነት እድገት ጋር ፣ የመንግ ስቱ ስልጣን እያደረ በይበልጥ የካፒታልን በወዝ ላይ ብሄራዊ ሃይል የመሆንን ፣ ለሶሻል ባርነት የተደራጀ ህጋዊ ሃይል የመሆንን የመደብ ፈላጭ ቆራጭነት ሞተር የመሆንን ጠባይ ያዘ ። የመደብ ትግሉን ወደፊት ካራመደ ከማንኛውም አብዮት በኋላ የመንግስት ሃይል ፍፁም የጨቋኝነት ጠባይ በጣም እየጐላ ይታያል ። « ከ1848-49 አብዮት በኋላ የመንግስቱ ስልጣን ወዝን የሚቃወም የካፒታል ብሄራዊ የጦርነት ሞተር ሆነ ። ሁለተኛው ኤምፓየር ( የንጉስ ነገስት መንግስት) ይሽንኑ አጠናከረ ። « የኤምፓየሩ (የንጉስ ነገስት አገዛዝ)ቀጥተኛ ተቃራኒ ኰሚዮኑ ነበር ።» « የዘውድ አገዛዝን ፎርም ሳይሆን ፣ ራሱን የመደብ አገዛዝን የሚተካ የሪፐብሊክ ጥሩ ቅርፅ ነበር ።



ይህ የወዛደሩ ፣ የሶሻሊስት ሪፑብሊክ ፣ « ጥሩ » ቅርፅ ምን ነበር ? ሊፈጥር የጀመረው መንግስት ምን ነበር ?

«...የመጀመሪያ የኮሚዩኒስት አዋጅ....ቋሚውን ጦር ሰራዊት መበተንና እሱን በታጠቀ ህዝብ መተካት ነበር ።»

በማንኛውም ሶሺያሊስት ነኝ በሚል ፓርቲ ፕሮግ ራም ውስጥ ይህ ጥያቄ ጐልቶ ይታያል ። ነገር ግን የፕ ሮግራሞቻቸው እውነተኛ ቁምነገር ልክ ከየካቲት 27 አብ ዮት በኋላ ይህንን ጥያቄ ለማሟላት እንቢ ባሉት በእኛ ሶሺያሊስት አብዮተኞችና ሜንሸቪኮች ሁኔታ በሚገባ ታይቷል ! ።

« ኰሚዩኑ የተመሰረተው ከየከተማው ክፍሎች በግልፅ በህዝብ በተመረጡ ፣ ተጠያቂነት ባላቸው በአጭር ጊዜያት ውስጥ ሊሻሩ በሚችሉ የማዘጋጃ ቤት መማክርት ነበር ። ከአባላቱ ብዙሃኑ በርግ ጥም ወዛደሮች ወይም የታወቁ የወዛደሩ መደብ ተወካዮች . . . ነበሩ ። የማእከላዊው አገዛዝ ወኪል መሆኑን በመቀጠል ፈንታ ፣ የፖሊስ ሰራ ዊቱ የፖለቲካ ስልጣኑን ባንድ ጊዜ ተገፎ በማ ንኛውም ጊዜ ሊሻር የሚችልና ሃላፊነት ያለበት የኰሚዮኑ ወኪል እንዲሆን ተደረገ ። ሌሎቹ የአስተዳደር ቅርንጫፎች ሹማምንትም ሁሉ እንደዚሁም ተቀየሩ ። ከኰሚዮኑ አባላት ጀምሮ ወደታች ፣ የህዝብ አገልግሎት በሙሉ በወዛደሮች ደመወዝ መሰራት ነበረበት ። የመንግስቱ ታላላቅ ሹማምንት ቋሚ ጥቅምና የተወካይነት አበል ከራሳቸው፣ ከታላላቁ ሹማምንት ጋር አብሮ ጠፋ ። »...

« ያሮጌው መንግስት ግዙፍ የሃይል ክፍሎች ፣
ቋሚ ጦር ሰራዊቱንና ፖሊሱን አንዴ ከአስ
ወገደ በኋላ ፣ መንፈሳዊ የመጨቆኛ ሃይሉን
« የካህናቱን ሃይል . . . » ለመሰባበር ኮሚዩኑ
ጓጉቶ ነበር ። . . .»

«ዳኞችም ከዚያ ከአስመሳይ ነፃነታቸው . . . ሊገፈ
ፉና የሚመረጡ ፣ ሃላፊነት ያለባቸውና ፣ በማን
ኛውም ጊዜ የሚሻሩ ሊሆኑ ነበር ። »[16]

ስለዚህም ኮሚዩኑ የተንኰታኰተውን የመንግስት
መሳሪያ በሙሉ ዲሞክራሲ « ብቻ » የተካ ይመ
ስላል ፣ ቋሚ ጦር ሰራዊቱን ማጥፋት ፣ ሁሉም
ባለስልጣኖች የሚመረጡና ካስፈለገ የሚሻሩ መሆን።
ሆኖም እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የሚያመለክተው
አንዳንድ ተቋሞች በመሰረቱ ልዩ አቋም ባላቸው
ሌሎች ተቋሞች መተካታቸውን « ብቻ » ነው ። ይህ
በትክክል « የመጠን ወደ ዓይነት የመለወጥ » ሁኔታ
ነው ። ለማሰብ የሚቻለውን ያህል ሰፋ ብሎና በማያወ
ላውል መንገድ እንዲኖር የተደረገ ዲሞክራሲ ፣ ከቡ
ርዧ ዲሞክራሲ ወደ የወዛደሩ ዲሞክራሲ ይለወጣል ፣
ከመንግስት (አንድ የተወሰነ መደብ የመጨቆኛ ልዩ
ሃይል ) በእርግጥ መንግስት ወደ አልሆነ አንድ ነገር
ይለወጣል ።

ቡርዧውን መጨቆንና ተቃዋሚነቱንም ማንኰታ
ኮት አሁንም አስፈላጊ ነው ። ይህም ለኰሚዩኑ በተ
ለይ አስፈላጊ ነበር ፣ ለመሸነፉም አንዱ ምክንያት
ይህንን በሙሉ ቆራጥነት አለማድረግ ነው ። ሆኖም
የመጨቆኛው መሳሪያ በባርነት ፣ በገባርነትና በቅጥር
ጉልበት ስር ሁል ጊዜ እንደነበረው ንኡሳኑ ክፍል
ሳይሆን አሁን ብዙሃኑ ህዝብ ነው ። ከህዝቡ ብዙሀኑ



ክፍል ጨቋኞቹን ራሱ ስለሚጨቁን ለመጨቆኛ « ልዩ
ሃይል » አስፈላጊ አይሆንም ! በዚህ መንፈስ መንግስቱ
መመንመንና መጥፋት ይጀምራል ። በጥቂቶች ተጠ
ቃሚዎች (ባለስልጣኖች የቋሚ ጦር ሰራዊቱ አለ
ቆችም) ልዩ ተቋሞች ምትክ ብዙሀኑ ራሱ በቀጥታ
እነዚህን ተግባሮች ሁሉ ለማሟላት ይችላል ። እንዲ
ሁም የመንግስቱ ስልጣንና ተግባሮች በይበልጥ በአ
ጠቃላይ በህዝቡ ላይ ሲወድቁ የስልጣኑ መኖር ተፈላጊ
ነት ያነሰ ይሆናል ።

ከዚህ ጋር በማያያዝ በማርክስ በተለይ የታዩት በኮ
ሚዩኑ የተወሰዱት የሚከተሉት እርምጃዎች በተለይ
ጠቃሚ ናቸው ። ባለስልጣኖችን በሚመለከት ረገድ
የተወካይነት አበልን በሙሉና የገንዘብ ጥቅምን ማስ
ወገድ፣ለመንግስቱ አገልጋዮች ሁሉ ይከፈል የነበረውን
ደመወዝ በሙሉ ወደ « ወዛደር ደመወዝ » ደረጃ ማው
ረድ ። ይህ ከማንኛው ነገር ይልቅ ከቡርዧ ዲሞክራሲ
ተላቆ ወደ ወዛደር ዲሞክራሲ፣ ከጨቋኝ መደቦች ዲሞክ
ራሲ ወደ ተጨቋኝ መደቦች ዲሞክራሲ ፣ መንግስቱ አን
ድን የተወሰነ መደብ ከመጨቆኛ «ልዩ ሃይል» በብዙሀኑ
ህዝብ ፣ ወዛደሮችና ገበሬዎች ሞላ ሃይል ጨቋ
ኞችን ወደ የሚጨቁን መለወጡን ይበልጥ በግልፅ ያሳ
ያል ። በዚሁ በተለይ ዋና በሆነው ፣ ምናልባት መንግስ
ትን በሚመለከት ጉዳይ በጣም ጠቃሚ በሆነው ነጥ
ብላይ ነው ፣ የማርክስ ትምህርት ሙሉ በሙሉ የተዘነ
ጋው ! ቁጥራቸው እጅግ ብዙ በሆኑ ታዋቂ ትችቶች
ውስጥ አይነሳም ። ክርስቲያኖች ፣ ሃይማኖታቸው የመ
ንግስት ሃይማኖት የመሆን ማእረግ ከተሰጠው በኋላ ፣
ዲሞክራቲክ አብዮታዊ መንፈስ የነበረውን የጥንቱን

ክርስቲያንነት « የዋህነት » « እንደደረሱት » ሁሉ ፥
ልክ ይህንንም ያረጀ አይነት « የየዋህነት » ቁራጭ የሆነ
ይመስል ዝም ማለቱ ነው ።

የከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች ደመወዝ መቀ
ነስ « እንዲያው » የየዋህ ፥ ጥንታዊ ዲሞክራሲ ጥያቄ
ይመስላል ። የዘመናዊ አድርባይነት « መስራች » ከሆ
ኑት መካከል አንዱ የቀድሞው ሶሻል ዲሞክራት ፥ ኤድ
ዋርድ በርንስታይን ፥ በ «ጥንታዊ » ዲሞክራሲ ላይ የቡ
ርዧውን ስንኩል ቀልድ ከአንድ ጊዜ በላይ በመደጋገም
ተናግሯል ። እንደማንኛውም አድርባይ እንዲሁም
እንደ ዛሬ ጊዜ ካውስትካይቶች ፥ ከሁሉ አስቀድሞ ወደ
« ጥንታዊ» ዲሞክራሲ « መለስ » ሳይባል ( ያለበለ
ዚያ ብዙሀኑ ፥ ከዚያም ያለምንም ልዩነት ጠቅላላ ህዝቡ
የመንግስቱን ተግባሮች ለማከናወን እንዴት ይችላል ?)
ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የማይቻል
መሆኑን ፥ ሁለተኛም ፥ በካፒታሊስት ባህልና በካፒታ
ሊዝም ላይ የተመሰረተው « ጥንታዊ ዲሞክራሲ » በቅ
ድመ ታሪክና በቅድመ ካፒታሊስት ጊዜያት ከነበረው
ጥንታዊ ዲሞክራሲ ጋር እንደማይመሳሰል መረዳት
ፈፅሞ ተስኖታል ። የካፒታሊስት ባህል በብዛት ማም
ረትን ፥ ፋብሪካዎችን ፥ የባቡር ሀዲዶችን ፥ የፖስታ
አገልግሎትን ፥ ቴሌፎኖችን ወዘተ . . ፈጥሯል ፥
በዚህም መሠረት የአሮጌው « የመንግስት ስልጣን »
ተግባሮች አብዛኞቹ በጣም የተቃለሉ ስለሆን ቀላል ወደ
ሆኑት ፥ የመዝገብ አያያዝና የመፈተሽ የመቆጣጠር ስራ
ዎች ሊወርዱ ስለሚችሉ በማንኛውም መፃፍና ማንበብ
በሚችል ሰው በቀላል ለመስራት እንደሚችሉ ፥ በተራ
« የወዛደር ደሞዝ » ለመሰራት እንደሚችሉ ፥ እነዚህም
ተግባሮች ከማንኛውም የመጠቀሚያ ሽፋናቸው ፥ ከማ



ንኛውም የ« ባለስልጣን ክብር » ካባቸው መገፈፍ
ይችላሉ (ይኖርባቸዋልም) ።

ሁሉም ባለስልጣኖች ፥ ያለምንም ልዩነት ፥ የተመረ
ጡና በማንኛውም ጊዜ የሚሻሩ ሆነው ደመወዛቸው
ወደ ተራ « የወዛደር ደመወዝ » ደረጃ ተቀንሶ እነዚህ
ቀላልና « በራሳቸው ግልፅ የሆኑ » ዲሞክራሲያዊ እር
ምጃዎች ፥ የወዛደሮቹንና ከገበሬዎቹ የብዙሀኑን ፍላ
ጐቶች ሙሉ በሙሉ ሲያስተሳስሩ በዚሁ ጊዜም ከካፒ
ታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም እንደሚያሸጋግር ድልድይም
ያገለግላሉ ። እነዚህ እርምጃዎች የመንግስቱን እንደገና
መገንባት የህብረተሰቡን እንደገና በፖለቲካ ብቻ መገ
ንባት ያመለክታሉ ። ሆኖም በእርግጥ ሙሉ ትርጉማ
ቸውንና ቁም ነገራቸውን ሊያገኙ የሚችሉት « የበ
ዝባዦችን ንብረት የመውረስ » ተግባር በመጠናቀቅ
ላይ ወይም በዝግጅት ላይ ከመሆን ጋር ሲያያዝ ብቻ ነው፤
ይህም ማለት የምርት መገልገያዎች ከካፒታሊስት የግል
ባለቤትነት ወደ ሶሻል (የጋራ) ባለቤትነት መለወጥ
ጋር ሲያያዝ ብቻ ነው ።

«ኰሚዩኑ » ይላል ማርክስ «የቡርዧ አብዮቶችን
መመሪያ ፥ ርካሽ አገዛዝን ፥ ሁለቱንም ዋና ዋና
የወጪ ምንጮች ፥ ቋሚ የጦር ሰራዊትንና የመንግ
ስቱን አካላት በማፈራረስ እውነት አደረገው ። »

ከገበሬው፤ከንኡስ ከበርቴው የተለያዩ ክፍሎች ሁሉ
«ወደ ከፍተኛው ደረጃ የሚደርሱት በቡርዧ መንፈስ
ኑሮአቸው የተቃናላቸው » ይህም ማለት ፥ የተደላደለ
«ኑሮ የሚኖሩ» ቡርዧ የሚሆኑ ወይም ጥቅም
ባለውና በሚያስተማምን ቦታ ባለስልጣን የሚ
ሆኑት ከቁጥር የማይገቡ ጥቂቶች ብቻ ናቸው ። በማን
ኛውም ገበሬ በሚገኝበት ካፒታሊስት አገር (በብዙዎቹ

የካፒታሊስት አገሮች እንዳለው ሁሉ ) ከገበሬዎቹ ብዙዎቹ በአገዛዙ የተጨቆኑ ናቸው ። ስለዚህም መውደቁን ይመኛሉ ፣ « ወጪው አነስተኛ የሆነ » አገዛዝን ይመኛሉ ። ይህም ሊገኝ የሚችለው በወዛደሩ ብቻ ነው ፣ እሱንም እንዳከናወነ ወዛደሩ በዚሁ ጊዜ መንግስቱን በሶሻሊስት አቅጣጫ ለመገንባት እርምጃ ይወስዳል ።

3. ፓርላሜንታዊነትን ማስወገድ

« ኮሚዮኑ » ይላል ማርክስ ፣ ፓርላሜንታዊ ሳይሆን ፤ የሚሰራ ፣ በአንድ ጊዜ ህግ አውጭና ህግ አስፈፃሚ አካል ሊሆን ነበር »

የበሶስት ወይም በስድስት አመታት አንድ ጊዜ የትኛው የገዢ መደብ አባል በፓርላሜንት ውስጥ ህዝቡን እንደሚወክልና እንደሚጨቁን ከመወሰን ይልቅ ወዛደሮችን ፣ ፎርማኖችንና ሂሳብ ሰራተኞችን ለንግዱ ለመፈለግ የግለሰብ ምርጫ እያንዳንዱን ቀጣሪ እንደሚያገለግለው ሁሉ ፣ አጠቃላይ ምርጫ በኰሚዮኖች የተደራጀውን ህዝብ እንዲያገለግል ተደረገ ። »[17]

በሶሻል ትምክህተኝነትና በአድርባይነት መኖር የተነሳ ፣ ይህ በ1871 በፓርላሜንታዊነት ላይ የተደረገው ሂስ አሁን ከማርክሲዝም ውስጥ « ተረስተው ከቀሩት ቃላት » ውስጥ ነው ። ፕሮፌሽናሎቹ የካቢኒ ሚኒስቴሮችና ፓርላሜንታውያኖች የጊዜያችን የወዛደሩ ከሀዲዎችና « አታላይ » ሶሻሊስቶችም ፣ ስለፓርላሜንታዊነት የሚደረገውን ሂስ ሁሉ « ስርአተ አልበኛነት» በማለት ያወግዛሉ ። « በአደጉት » ፓርላሜንታዊ አገሮች ወዛደሮች ፣ እንደ ሺድማን ፣ ዴቪድ ፣ ሌጅዮን ፤ ሴምባት ፣ ሬኖድል ፣ ሂንደርስን ፣ ቫንደርቬል



ግስት መዋቅር መሀከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ፤ ሶስተኛም ፣ የአካባቢ አገዛዝን በሚመለከት ።

ኤንግልስ በኤርፋርት ፕሮግራም ረቂቅ ሂስ ውስጥ አቢይ ርእስ አድርጎ ያቀረበው የሬፑብሊክን ጉዳይ ነው ። የኤርፋርት ፕሮግራም ረቂቅ የአለም አቀፍ ሶሻል ዲሞክራቶች ያስገኙላቸውን ጠቃሚ ነገሮች በምናስታውስበት ጊዜ ፣ ፕሮግራሙ በጠቅላላው ለሁለተኛው አለም አቀፍ የወዛደሮች ማህበር ጥሩ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡን እንገነዘባለን ፣ እንዲያውም ያላንዳች ማጋነን ኤንግልስ በዚህ ሂስ አማካይነት በሁለተኛው አለም አቀፍ የወዛደሮች ማኅበር ውስጥ የታየውን አድርባይነት ነቅፏል ለማለት እንችላለን ።

« የረቂቁ የፖለቲካ ጥያቄዎች ፣ » ይላል ኤንግልስ «አንድ ትልቅ ስህተት አለባቸው ። መባል የነበረበት ነገር እዚያ ውስጥ የለም » (መስመር የኤንግልስ)

በኋላ ፣ የጀርመን ህገ መንግስት በጣም አድሃሪ የሆነው የ1850 ህገ መንግስት ትክክል ግልባጭ መሆኑን ይገልፃል ፤ ቪልሄልም ሊብክኔሽት እንደፃፈው ይሽታግ (የጀርመን ሸንጎ) « የፍፁም ፈላጭ ቆራጭነትን መሸፈኛ የበለስ ቅጠል » ነው ። ስለሆነም የትንንሽ መንግስታትን ህልውና ፣ የትንሽዋን ጀርመን ፌዴሬሽን ህልውና በሚያረጋግጥ ህገ መንግስት መሰረት « ሁሉም የማምረቻ መገልገያዎች ወደ ህዝብ ይዞታ ይዙሩ »ብሎ መመኘት «ቅልጥ ያለ ጅልነት»ነው ይላል

ጀርመን ሬፑብሊክ ትሁን የሚለውን ጥያቄ በፕሮግራሙ ማስገባት በህጋዊ መንገድ የማይቻል መሆኑን ጠንቅቆ በማወቁ ኤንግልስ

« ነገሩን መንካት አደገኛ ነው » ይላል ። ነገር ግን
ኤንግልስ በዚህ « ሁሉንም » በሚያረካ ግልፅ
ሃሳብ አልረካም ። በመቀጠል « ስለዚህም ነገሩ በሆ
ነው ዘዴ ሁሉ ለማጥቃት መሞከር አለበት ። ይህም
የቱን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በአሁኑ ጊዜ በሶሻል
ዲሞክራቶች ፅሁፎች ውስጥ በሰፊው በመስፋፋት
ላይ ባለው አድርባይነት ታይቷል ። ፀረ ሶሻሊስት
የሆኑትን ህጎች እንደገና መታደስ በመፍራት
እና በዚያ በህግ ጊዜ የተደረጉትን ችኩል ንግግሮች
በማስታወስ ፣ ፓርቲው ጥያቄዎቹን ሁሉ በሰ
ላም እንዲያገኝ አሁን ያለው የጀርመን ህግ በቂ
ሆኖ እንዲገኝ ይፈልጋሉ ፤ ..»

ኤንግልስ በመሰረቱ የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቶች
ፀረ ሶሻሊስት ህግ ይታደሳል ብለው የሚፈሩ መሆናቸ
ውን ገልፆ ፣ ይህም ያለጥርጥር አድርባይነት ጠባይ
መሆኑን በተለይ ያስረዳል ፤ እርሱም በጀርመን ውስጥ
ሪፑብሊክና ነፃነት ባለመኖራቸው ፓርቲው ስራውን
« በሰላም » መንገድ የማካሄዱ ጉዳይ በፍፁም ዘበት
መሆኑን አመለከተ ። ኤንግልስ እዚህ ላይ ስህተት
እንዳይሰራ በጣም ተጠንቅቆ ነበር ። ምክንያቱም
በሬፑብሊካን ወይም በጣም ነፃ በሆኑት አገሮች ወደ
ሶሻሊዝም በሰላም የመሸጋገሩን ጉዳይ « ማሰብ የሚ
ቻል መሆኑን (ማሰብ ብቻ !) ያምናል ፣ ሆኖም
« . . . በጀርመን ውስጥ ፣ መንግስቱ ሁሉን ለማድረግ
የሚችል በሆነበት ራይሽታግና ሌሎች ተወካይ
አካሎች የተጨበጠ ሥልጣን በሌላቸው ስፍራ ፣
የዚህ አይነቱን ነገር በጀርመን ውስጥ ማወጅ —
በተለይም ማድረጉ አስፈላጊ ባልሆነበት ስፍራ —
የበለስን ቅጠል ማንሳትና ለእርቃን ስጋነቱም
ራስን መጋረጃ ማድረግ ነው ። » ይላል



ይህንን ምክር የደበቁ ብዙ የጀርመን ሶሻል ዲሞ
ክራት መሪዎች ፣ ለዚህ ፍፁምነት መጋረጃ ሆነው
ቀርተዋል ።

« በመጨረሻም የዚህ አይነቱ ፖሊሲ የራ
ስን ፓርቲ ከመስመሩ ውጭ ብቻ ነው ሊመራ
የሚችለው ። እነርሱም በፕሮግራሙ ውስጥ
በመጀመሪያው ከፍተኛ ድርጊት ፣ በመጀ
መሪያው የፖለቲካ ቀውስ ራሳቸውን ከአጀንዳ
የሚያስቀምጡትን ፣ ጥያቄዎች በመደበቅ ፣ አጠ
ቃላይ ፣ ረቂቅ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ብቻ ያቀር
ባሉ ። በዚህ በቀውጢ ጊዜ ፓርቲው በድንገት
ያለ መሪ ከመቅረቱ በስተቀር ፣ በጣም ጠቃሚ
ጉዳዮች ላይ ውይይት ስላልተደረገባቸው ሳይገ
ልፁ ከመቆየታቸውና ስምምነት ከመጥፋቱ በስ
ተቀር ከዚህ ሁኔታ ምን ሊገኝ ይችላል ? . . .

« ለጊዜያዊ ፍላጎት ሲባል ይህን አቢይ ነጥብ
መርሳት ፣ ወደፊት የሚያስከትለውንም ጉዳትና
ጥቅም ሳያመዛዝኑ ለጊዜያዊ አሸናፊነት መታገ
ልና ጥረት ማድረግ ፣ የንቅናቄውን የወደፊት
እድል ለጊዜያዊው የሚደረግ መስዋእት ከቅንነት
ሊሆን ይችላል ፣ ሆኖም አሁንም ሆነ ወደፊት
የአድርባይነት ጠባይ ነው ። « የቅንነት » አድርባይ
ነት ምናልባትም ከሁሉም የበለጠ አደገኛ ነው ።
« አንድ የታመነ ነገር ቢኖር ፣ ፓርቲያችንና ወዛ
ደሩ በስልጣን ላይ መውጣት የሚችሉት በዲሞ
ክራሲያዊ ሬፑብሊክ ስር ብቻ ነው ። ቀደም ብሎ
ታላቁ የፈረንሳይ አብዮት እንዳስተማረን ሁሉ ፣
ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ልዩ አይነት የወዛደሮች
የበላይ ገዥነት ነው ። . . . »

ኤንግልስ እዚህ ላይ በማርክስ ቃላት ውስጥ ደመቅ
ብሎ የሚታየውን መስረተ ሃሳብ በተለይ በሚያስደንቅ
ሁኔታ ይደግማል ፡ ይኸውም ፡ ዲሞክራሲያዊ
ሪፑብሊክ ለወዛደሮች የበላይ ገዥነት የሚቀርበው
መንገድ መሆኑን ነው ። የዚህ አይነቱ ሪፑብሊክ የካ
ፒታልን አገዛዝ ፤ ከዚህም ጋር የሰፊው ህዝብና የመ
ደብ ትግል ጭቆና ሳይደመሰስ ፡ የጭቁኑ ሰፊ ህዝብ
መሠረታዊ ፍላጐት ለማርካት የሚያስችል ሁኔታም
እንደተፈጠረ ያለጥርጥር ወደዚህ ትግል መስፋፋት ፡
ማደግና መፋፋም ያመራል ። ይህም ሁኔታ በስራ የሚ
ታየው በወዛደሩ የበላይ ገዥነት ፡ ማለትም ፡ ሰፊው
ህዝብ በወዛደሩ ሲመራ ነው ። እነዚህ በሁለተኛው
አለም አቀፍ የወዛደሮች ማህበር « የተዘነጉ » የማር
ክሲዝም « ቁም ነገሮች » ናቸው ፡ መዘንጋታቸውም
በ1917 በሩሲያ አብዮት በመጀመሪያው አጋማሽ ፡ በሜ
ንሼቪክ ፓርቲ ታሪክ ውስጥ በግልፅ ታይቷል ።

ኤንግልስ ስለፌዴራል ሪፑብሊክ ፡ ከህዝቡ ብሄ
ራዊ ይዘት ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው ይፅፋል ።
« የዛሬው ጀርመን መተካት ያለበት በምንድ
ነው ? » ( በአድሃሪ የዘውድ ህገ መንግስትና እንዲ
ሁም ጨርሶ በመጥፋት ፋንታ በጀርመን ውስጥ
የ « ፕሩሺያኒዝም » ልዩ ጠባዮች ከሚያራዝመው
ጀርመንን በጥቃቅን መንግስታት ከሚከፍለው
አድሃሪ መመሪያ ጋር) ። « በኔ አስተያየት ፡ ወዛ
ደሩ አንድ እና የማይከፈል ሪፑብሊክን መጠቀም
ይችላል ። በሰፊው የአሜሪካን ግዛት ፡ በምስራቁ
በኩል መሰናከል ቢሆንም ፡ በጠቅላላው ፌዴራል
ሪፑብሊክ አስፈላጊ ነው ። ሁለቱ ደሴቶች በአ
ራት ብሄሮች በታያዙበትና ዛሬም ቢሆን ባንድ



ፓርላሜንት ውስጥ ቢሆንም እንኳ ሶስት ልዩ
ልዩ ህጉች ገ‹ን ለገ‹ን ባሉበት በእንግሊዝ አገ
ርም ቢሆን ሪፑብሊክን መመስረት አንድ እርምጃ
ወደፊት መራመድ ይሆናል ። በትንሿ ስዊዘር
ላንድ ፡ የረጅም ጊዜ መሰናከል ቢሆንም ፡ ስዊ
ዘርላንድ ከአውሮፓ የመንግስት ስርአት ውስጥ
በፍፁም ንቁ ያልሆነች አባል መሆኗ ስላልከፋት
መታገስ ይቻላል ። ለጀርመን ግን ፡ በስዊዝ አይ
ነት ፍዴሬት ማድረግ ከፍተኛ እርምጃ ወደኋላ መው
ሰድ ይሆናል ። የህብረት መንግስት (Union State)
ሙሉ በሙሉ ከተዋሃደ መንግስት (Unified State)
በሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ይለያል ። አንደኛ ፡ ከህ
ብረቱ መንግስት ውስጥ እያንዳንዱ መንግስት ፡
የራሱ የፍትሀብሄርና የወንጀለኛ ህጐች እና የህግ
መመሪያዎች ( Judicial System ) አሉት ፡
ሁለተኛ ፡ ከህዝባዊ ምክር ቤት (Popular
Chamber) ጐን ለጐን ትንሽ ወይም ትልቅ
ንኡስ ክፍል (Federal Chamber) የሚመ
ርጥበት ፌዴራል ምክር ቤት አለ ። » በጀርመን
የህብረት መንግስት ፡ ወደ ሙሉ በሙሉ የተዋ
ሃደ መንግስት መሸጋገሪያ ደረጃ ነው ። ከ1866
እስከ 1870 ድረስ «ከላይ የተደረገው አብዮት»
ወደ ኋላ መሄድ ወይም መቀልበስ የለበትም ፤
ነገር ግን « በበታች ንቅናቄ » መደገፍ አለበት ።

ኤንግልስ ስለ መንግስት አይነት በግድየለሽነት
ከማለፍ ይልቅ ፡ በተቃራኒ ፡ በያንዳንዱ ልዩ ተጨባጭ
ታሪካዊ ሁኔታ መሰረት ፡ ሽግግሩ ከምን ወደ ምን
መሆን እንደሚገባው ለማሳየት የሽግግሩን አይነቶች
በጥንቃቄ ለመተንተን ሞክሯል ።

ነገሩን ከወዛደሮችና ከወዛደሮች አብዮት አቅጣጫ
በመቅረብ ፣ ኤንግልስ ፣ እንደማርክስ ፣ ዲሞክራሲያዊ
ዋህድነትንና የሬፑብሊክን — የማይከፈል አንድነት
ይደግፋል ። እሱም ፌዴራል ሪፑብሊክን ለእድገት እን
ዳልተለመደ ሁኔታና እንቅፋት ፣ ወይም ከዘውድ አገ
ዛዝ ወደ ማእከላዊ ቁጥጥር ስር ወደሆነው ሪፑብሊክ
መሸጋገሪያና በአንድ አንድ ልዩ ልዩ ሁኔታዎችም እንደ
አንድ እርምጃ ወደፊት አድርጎ ይመለከተዋል ። ከነዚ
ህም ልዩ ሁኔታዎች ፣ የብሄሮች ጥያቄ ቅድሚያን ይይ
ዛል ።

የትንንሽ መንግስታትን አድሃሪ ተፈጥሮ ያለምህረት
ቢተችም እንኳን ፣ ይኸንንም አንድ አንድ ተጨባጭ ሁኔ
ታዎች በብሄር ጥያቄ ቢያበጥረውም ፣ የብሄርን ጥያቄ
ወደ ጎን የመተው ፍላጎት በፍፁም አልነበረውም ።
የሆላንድና የፖላንድ ማርክሲስቶች «የራሳቸውን»ትና
ንሽ መንግስታት ጠባብ ብሄረተኝነት ትክክለኛ ተቃ
ውሞ የተነሳ ይህን (የብሄርን ጥያቄ ወደ ጎን የመተው
ፍላጎት (ተርጓሚ) ስህተት ፈፅመዋል ።

የጂኦግራፊ ሁኔታ ፣ የጋራ ቋንቋና የረጅም ዘመናት
ታሪክ የብሄርን ጥያቄ በያንዳንዱ ትንንሽ ክፍል ያቃ
ለለ በሚመስልበት በእንግሊዝ ይህችን አገር በሚመ
ለከት እንኳ ፣ ኤንግልስ የብሄር ጥያቄ ያለፈ ታሪክ አለ
መሆኑን ገልፆ ፌዶራል ሪፑብሊክን መመስረት «አንድ
እርምጃ ወደፊት » መሆኑን አስረድቷል ። እርግጥ ፣
እዚህ ላይ ኤንግልስ በፕሮግራሙ ውስጥ የፌዶራል
ሪፑብሊክን ደካማ ጎን ከመንቀፍ ዞር ማለቱን ወይም
ለተዋሃደ በማእከላዊ ቁጥጥር ስር ለሆነ ዲሞክራሲያዊ
ሪፑብሊክ የሚያደርገውን ቆራጥ ትግልና ፕሮፓጋንዳ
መተውን የሚገልፅ ምንም ነገር የለም ።



ኤንግልስ ዲሞክራሲያዊ ዋህድነትን ቡርዧና ንኡስ
ከበርቴ አይዲዮሎጂስቶች ከነርሱም ውስጥ በተለይ
አናርኪስቶች በሚጠቀሙበት በቢሮክራሲያዊ መንፈስ
አልወሰደውም ። የሱም የዋህድነት አስተሳሰብ «ኰሚ
ዩኖችና » ወረዳዎች የአገርን አንድነት በፈቃደኝነት
ለመከላከል ፣ ቢሮክራሲንና « ከላይ » መታዘዝን ጨርሶ
ለመደምሰስ የሚያስችል ሰፊ የውስጥ አስተዳደር እን
ዲኖራቸው የሚደግፍ ነው ።

ማርክሲዝም ስለ መንግስት የሚያስተምረንን በመው
ሰድ ፣ ኤንግልስ የፕሮግራሙን አስተያየት እንደሚከተ
ለው ያስፋፋል ፡—

«እንግዲህ አንድነቱን ያጠነከረ ሪፑብሊክ ያስ
ፈልጋል — ነገር ግን በ1798 ያለንጉስ በተመ
ሰረተው በአሁኑ የፈረንሳይ ሪፑብሊክ አይነት
መሆን የለበትም ። ከ1792 እስከ 1798 እያንዳ
ንዱ የፈረንሳይ ክፍልና ኰሚዩን (Gemeinde) ፣ በአ
ሜሪካን ሞዴል ላይ የተመሰረተ ሆኖ ፣ ሙሉ
የራስ አገዛዝና ነፃነት ነበረው ፣ ዛሬም እኛ ሊኖረን
የሚገባን የዚህ አይነት ነፃነት ነው ። የራስ
አገዛዝ እንዴት እንደሚቋቋምና ያለቢሮክራሲም
እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል የአሜሪካና የመ
ጀመሪያው የፈረንሳይ ሪፑብሊክ ፣ አሳይተውናል።
ዛሬም ካናዳ ፣ አውስትራሊያና ሌሎች የእንግሊዝ
ቅኝ ግዛቶች ይህንኑ በማሳየት ላይ ይገኛሉ ። የዚህ
አይነቱ የክፍለ ሃገርና አካባቢ አገዛዝ ፣ ንኡስ
ክፍሉ ከህብረት መንግስት ፣ «( ማለትም ፣ ከጠ
ቅላላው ፌዴራል ከሆነ መንግስት ) « ከወረዳና
ከኰሚዩን ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ነፃነት ካለው
ከስዊስ ፌዴራሊዝም ይበልጥ ነፃ ነው ። የንኡስ

ክፍሉ መንግስታት የወረዳና የክፍል አስተዳደሮችን ይሾማሉ ፥ ይህም በእንግሊዝ ቋንቋ ተናጋሪ አገሮች ውስጥ የተለመደ ነገር አይደለም ፥ ቢሆንም ወደፊት በነዚህ አገሮች ኰሚሽነሮችን የወረዳ ፖሊስ አዛዦችን ፤ ገዢዎችንና እንዲሁም በጠቅላላው በመንግስት የተሾሙትን ባለስልጣኖች ሁሉ ፈፅሞ ማጥፋት ይኖርብን ይሆናል ። በፕሮግራሙ ውስጥ ስለተመለከተው የራስ አገዛዝ ሀረግ ፥ ኤንግልስ የሚከተለውን ሃሳብ ያቀርባል ። « ለክፍለ ሀገሮች ፥ ለአውራጃዎች ፥ ለወረዳዎችና ለኰሚዩኖች ፤ ለብሄረሰቦች ሙሉ የራስ አገዛዝ መብት በነፃ ምርጫ በተመረጡ ባለስልጣኖች ሊሰጣቸው ይገባል ። በመንግስት የተሾሙ ባለስልጣኖች ሁሉ መደምሰስ ይኖባቸዋል ።

በኬሬንስኪና በሌሎች « ሶሻሊስት » ሚኒስትሮች መንግስት በተከለከለው ፕራቭዳ (ቁ. 68 ግንቦት 28 ቀን 1917 [22]ላይ በዚህ ነጥብ ላይ (እርግጥ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ አይደለም) የአስመሳይ አብዮታዊ አስመሳይ ዲሞክራሲ አስመሳይ ሶሻሊስት ተወካዮች ከዲሞክራሲ በሚያሳፍር ሁኔታ ርቀው መሄዳቸውን ለማመልከት እድል አጋጥሞኝ ነበር ። እርግጥ ፥ ራሳቸውን ከኢምፔሪያሊስት ቡርዧ ጋር « በህብረት » ያሰሩት ሰዎች ለዚህ አይነቱ ወቀሳ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ እንደሚሉ አያጠራጥርም ።

ከማእከላዊ ሪፑብሊክ ይልቅ በፌዴራል ሪፑብሊክ የበለጠ ነፃነት ሊኖር ይችላል ብለው የሚያምኑትን ንኡስከበርቴ ዲሞክራቶችን ማስረጃ የሌለው መጥፎ አስተያየት ፥ ኤንግልስ ፥ በተጨባጭ ምሳሌዎችና ማስረጃዎች ፥ ሊያፈርስ መቻሉን መገንዘብ በጣም ጠቃሚ



ነው ። ይህ ትክክል አይደለም ። ልክ አለመሆኑንም ኤንግልስ ከ1792 - 1798 ከነበረው የፈረንሳይ ማእከላዊ ሪፑብሊክና ከስዊዝ ፌዴራል ሪፑብሊክ ማስረጃ በመጥቀስ ያስረዳል ። ዲሞክራቲክ ማእከላዊ ሪፑብሊክ ከፌዴራል ሪፑብሊክ ይበልጥ ነፃነት ሰጥቷል ። በሌላ አባባል የውስጥ ፥ የክፍለ ሀገርና በታሪክ የታወቀው ከፍተኛ ነፃነት የሚሰጠው በማእከላዊ ሪፑብሊክ እንጂ በፌዴራል ሪፑብሊክ አይደለም ።

በጠቅላላው ፥ ስለፌዴራል ፥ ስለ ማእከላዊ ሪፑብሊክና ስለ ውስጥ አገዛዝ በፓርቲያችን በኩል በቂ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ እንዳልተደረገ ሁሉ ስለዚ ህም እውነተኛ ጉዳይ በቂ ጥንቃቄ አልተደረገም ።

## 5. ለማርክስ የፈረንሳይ የርስ በርስ ጦርነት ። የ1891 መቅድም ፤

የፈረንሳይ የርስ በርስጦርነት ሶስተኛው እትም መቅድሙ ላይ ( ይህ መቅድም የወጣበት ቀን ማርች 18. 1891 ሲሆን በመጀመሪያም በኖዬላሳይት (Neue Zeit) ታትሞ ነበር) ኤንግል ስለመንግስት ካለው አስተሳሰብ ጋር በተያያዙ ጥያቄዎች ላይ የሚያስደስቱ አስተያየቶችን ከሰጠው ተጨማሪ ስለኰሚዩኑ[23] ትምህርቶች በጣም ግልፅ ማጠቃለያ ሰጥቷል ።

ይህ ማጠቃለያ ፥ ፀሀፊውን ከኰሚዮኑ በለዩት ሃያ አመታት ጠቅላላ ልምድ በይበልጥ የተረጋገጠ ፥ በተለይ ጀርመን ውስጥ እንደዚያ የተናኘው « መንግስት አምልኰአዊ እምነትን » የሚቃወም ሲሆን ፥ በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ የማርክሲዝም የመጨረሻው ቃል ተብሎ ቢጠራ ትክክል ይሆናል ።

ኤንግልስ እንደሚመለከተው ፣ በፈረንሳይ ውስጥ ወዛደሮቹ ከእያንዳንዱ አብዮት ውስጥ ታጥቀው ብቅ አሉ ፤

ስለዚህም ፣ ወዛደሮቹን ትጥቅ ማስፈታት የመንግስቱ ቁንጮ ለነበረው ቡርዧ ቀዳሚ ግዳጅ ነበር ። ስለዚህ ከእያንዳንዱ ወዛደሮች ካሸነፉት አብዮት በኋላ ፣ በወዛደሩ መሸነፍ የሚያልቅ አዲስ ትግል ይቀጥላል ። »

ይህ የቡርዧ አብዮቶች ልምድ ማጠቃለያ ፣ የተመጠነ እንደመሆኑ ገላጥም ነው ። የነገሩ ይዘት ፣ በተጨማሪ ፣ በመንግስት ጥያቄ ላይ ደግሞ ፣ (ጭቁን መደብ ትጥቅ አለው ወይ? እዚህ ጋ ባስገራሚ ሁኔታ በሚገባ ተጨብጧል ። ይህ ይዘቱ ነው ብዙ ጊዜ በሁለቱም ፣ በቡርዧ አብዮት ርእዮተ አለም ተፅእኖ ስር ባሉ ፕሮፌሰሮችና በንኡስ ከበርቴ ዲሞክራቶች ቸል የተባለው ። በ1917 የሩሲያ አብዮት ውስጥ የዚህን የቡርዧ አብዮት ምስጢር የመለፍለፍ ክብር (የካቬኛክ[24] ክብር) ለ«ሜንሸቪክ» «እሱም ማርክሲስት» ፀረ ቴሌ ወደቀ ። ሰኔ 11 « ታሪካዊ » ንግግሩ ላይ ፣ ፀረ ቴሊ ቡርዧው የፔትሮግራድ ወዛደሮችን ትጥቅ ለማስፈታት መቁረጡን እንደራሱ ውሳኔና ለመንግስቱም አስፈላጊ እንደሆነ አድርጐ ለፈፈ ።

የሰኔ 11ዱ የፀረቴሊ ታሪካዊ ንግግር ፣ በሚስተር ፀረቴሌ የሚመራው የሶሻል አብዮተኞችና የ ሜንሼቪኮች ግንባር ፣ የወዛደሩን አብዮት በመቃወም ወደ ቡርዧው እንደከዱ ለማሳየት ለ1917 አብዮቱ ታሪክ ፀሀፊዎች እንደ ጥሩ ማስረጃ ያገለግላል ።



ሌላው ከነገሩ አግባብ ኖሮት የተጠቀሰ ፣ ከመንግስት ጥያቄም ጋር የተቆራኘ የኤንግልስ አስተያየት ሃይማኖትን ይመለከታል ። የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ ፣ እየበሰበሰና በይበልጥ አድርባይ እየሆነ ሲሄድ ፣ « ሃይማኖት የግል ነገር ሆኖ መታወጅ ይኖርበታል » የሚለውን የተከበረ ፎርሙላ የተሳሳተ አድሃሪ ትርጉም ወደመስጠቱ በይበልጥ አሽቆልቁሎ መሄዱ በሚገባ የታወቀ ነው ። ፎርሙላው አብዮተኛ ለወዛደሩ ፓርቲ እንኳ ሃይማኖት የግል ጉዳይ ነበር የሚል ትርጉም እንዲኖረው ተጠምዝዟል . . ይህን የወዛደሩን አብዮታዊ ፕሮግራም ፍፁም መክዳትን ነበር ኤንግልስ አጥብቆ የተቃወመው ። እንዲያው በጣም ደካማውን የአድር ባይነት አጀማመር ብቻ ነበር በሱ ፓርቲ ውስጥ በ1891 ያየው ስለዚህም በከባድ ጥንቃቄ ሃሳቡን እንደሚከተለው ገለጠ ።

« . . በኮሚዮኑ ውስጥ የተቀመጡበት በብዛት ወዛደሮች ብቻ ፣ ወይም የታወቁ የወዛደሮች ተወካዮች ስለነበሩ ፣ ውሳኔዎቹ ከፍተኛ የወዛደር ጠባይ አዝለዋል ። እነዚህ ውሳኔዎች ሬፑብሊካዊው ቡርዧው ከፍርሃት የተነሳ ሳያሳልፍ የቀረውን ፣ ግን ለወዛደሩ መደብ ነፃ ንቅናቄ አስፈላጊ የሆነውን መሰረት የሰጡት ጥገናዎች ከመንግስት አንፃር ሲታይ ሃይማኖት ፍፁም የግል ጉዳይ መሆኑን እንደመገንዘብ የመሰሉትን አፅድቋል ፣ አለያም ኰሚዩኑ ለወዛደሩ መደብ ጥቅም ቀጥታ የቆሙና በከፊል ወደ ጥንቱ የኅብረተሰብ ስርአት የጠለቁ ትእዛዞች አውጅዋል ። »

ኤንግልስ « በመንግስት አንፃር » የሚሉትን ቃላት
ያስመረባቸው ፥ የአብዮተኛ ወዛደሩን ፓርቲ ወደ እጅግ
ስድ ወደ ሆነ « የነፃ አስተሳሰብ » አድርባይነት
ደረጃ ዝቅ በማድረግ ስም የለሹን አቋም ለመቀበል
የተዘጋጀውን ግን ህዝቡን የሚያደነዝዘውን የሃይማኖት
መርዝ በመቃወም ፓርቲው የሚያደርገውን ትግል የሚ
ያወግዘውን በፓርቲው አንፃር ሃይማኖት የግል ጉዳይ
ነው ብለው ያወጀውን የጀርመን አድርባይነት በቀጥታ
ለመውጋት ነው ።

የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቶች የወደፊት ታሪክ መር
ማሪዎች፥ ለ1914 አሳፋሪ ክስረታቸው ስረ መሰረቶቹን
ለማውጣት ሲቦረቡሩ ፥ ለአድርባይነት በሩን ቅልጥጥ
አድርገው በሚከፍቱ ፥ በፓርቲው ርእዮተ አለማዊ
መሪ በካውትስኪ የማምለጫ አዋጆች መጀመርያ
በ1913ቱ « ቤተክርስቲያንን ተውት » ንቅናቄ በሚ
ለው የፓርቲውን ዝንባሌ በመጨረስ ፥ በዛ ያሉ ቸል
የማይባሉ ጠቃሚ ማስረጃዎች ያገኛሉ ።

እስኪ ፥ ከኰሚዩኑ ሃያ አመታት በኋላ ፥ ኤንግልስ
ለተዋጊው ወዛደር ትምህርቱን እንዴት እንዳጠቃለለ
ለት እንመልከት ።

ኤንግልስ ከፍተኛ ግምት የጣለባቸው ትምህርቶች
እነዚሁና ፡—

«... የበፊቱን ማዕከላዊ አገዛዝ ፤ ጨቋኝ ኃይል ፥ የጦር
ኃይሎች፥የፖለቲካ ፖሊሲና ቢሮክራሲውን ነው
ናፖሊዮን በ1798 ፈጥሮት የነበረውና ከዚያ ጀምሮ
ማንኛውም አዲስ አገዛዝ እንደ ጥሩ መሣሪያ ወርሶ
በጠላቶቹ ላይ የተጠቀመበት - ይህ ኃይል ነበር
ልክ ፓሪስ ላይ እንደወደቀው በማንኛውም ቦታ



መውደቅ የነበረበት ። የወዛደሩ መደብ አንዴ ሃይ
ልክያዘ ፥ ባረጀው የመንግስት መሳሪያ መገልገል
ሊቀጥል እንደማይችል ኰሚዩኑ ፤ እንዲያውቅ
ከመጀመሪያው ተገዶ ነበር ፤ ያገኛትን የበላይነት
እንደገና ላለማጣት ፥ ይህ የወዛደር መደብ ፥ ባንድ
በኩል ፥ በፊት በእርሱ ላይ ይውል የነበረውን
ያረጀ የመጨቆኛ መሳሪያ በሙሉ ማውደም እና ፥
በሌላ በኩል ፥ ከራሱ ወኪሎችና ሹሞች ራሱን
መጠበቅ ማን ከማን ሳይባል ፥ ሁሉም በማናቸ
ውም ጊዜ ሊሻሩ እንደሚችሉ መሆናቸውን
በማስታወቅ ነበረበት ። »

በዘውድ አገዛዝ ስር ብቻ ሳይሆን ፥ በዲሞክራሲያዊ
ሬፑብሊክም መንግስት ያው መንግስት መሆኑን ፥
ማለትም ባለስልጣኖችን «የህብረተሰብ አገልጋዮቹን ፥»
ክፍሎቹን ወደ ህብረተሰቡ ጌቶች የመለወጥ መሰረ
ታዊ መለያ ጠባዮቹን እንደሚይዝ ፥ ኤንግልስ በመደ
ጋገም አበክሮ ያመለክታል ።

« የመንግስትንና የመንግስት ክፍሎች ከህብ
ረተሰብ አገልጋይነት ወደ የኅብረተሰብ ጌቶች
መሸጋገርን በሁሉም ባለፉት መንግስታት ውስጥ
የማይቀር የነበረውን ሽግግር፥ለመቃወም ኰሚ
ዩኑ በሁለት እንከን በሌላቸው ዘዴዎች ተጠቀመ ።
መጀመሪያ ፥ በሚመለከታቸው ሁሉ ሙሉ ተሳ
ትፎ በተመረጡና በተፈለገው ጊዜ በመራጮቹ
በሚሻሩ ሰዎች ሁሉንም የአስተዳደር ፥ ህግ የት
ምህርት ቦታዎች ሞላ ። ከዚያም ፥ በሁለተኛ
ደረጃ ፥ ለሁሉም ሹማምንት ለከፍተኞችም ሆነ
ለዝቅተኞች ለሌሎቹ ወዛደሮች የሚከፈለውን ደመ
ወዝ ብቻ ከፈለ ። በኰሚዩኑ የተከፈለው ከፍተ

ኛው ደመወዝ 6000 ፍራንክ* ነበር ። ለልኡካኖች
ለተወካይ አካሎች ተጠሪ ፡ እንደሆኑ ከወጡት
እገዳዎች ሌላ በዚህ መንገድ ለሹመትና ለጥቅም
ፍለጋ ሲሉ መስራትን ማገጃ ተዘጋጅቶ ነበር ።»

ኤንግልስ እዚህ ላይ የማያቋርጥ ዲሞክራሲ በአንድ
በኩል ፥ ወደሶሻሊዝም ከሚለወጥበት ፥ በሌላ በኩል ፥
ሶሻሊዝምን ከሚጠይቅበት አስደናቂ የአዋሳኝ መስመር
ላይ ይደርሳል ። ምክንያቱም መንግስትን ለመደምሰስ
እንዲያስችል ፡ የአብዛኛው ሰፊው ህዝብና እንዲሁም
የእያንዳንዱ ግለሰብ መጠንና ችሎታ በሚፈቅደው
ገደብ መሰረት የህዝቡ አገልግሎትና ተግባሮች ወደ
ቀላል የቁጥጥርና የሂሳብ ስራዎች መቀየር አለባቸው ።
እንዲሁም ጥቅም ፍለጋን ለመደምሰስ «የሚያስከብሩ»
ግን ጥቅም የሌላቸው የመንግስት ስራዎች በሁሉም
እጅግ በጣም ነፃ በሆኑ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ
ሁልጊዜ እንደሚሆነው ፥ ከፍተኛ ገንዘብ ወደ የሚ
ያስገኙ ባንኮችና አክሲዮን ማህበሮች ውስጥ ቦታዎች
መወጣጫ እንዳይሆኑ መደረግ አለበት ።

ሆኖም ፥ ለምሳሌ የብሄሮችን እድል በራስ መወሰን
በሚለው ጥያቄ ላይ አንዳንድ ማርክሲስቶች ይህ በካ
ፒታሊዝም የማይሆን ነገር ነው ፤ በሶሻሊዝም ውስጥም
የማያስፈልግ ነው በሚሉበት ጊዜ የሚያደርጉትን
ስህተት ኤንግልስ አላደረገም ። የዚህ አይነት ብልህ
መሳይ ግን የተሳሳተ መግለጫና ተቋም አንፃር ሊደረግ

* የደመወዝ ጣሪያ ለመላው መንግስት በቂ ከሆነው በ6000 ሩብል
ፋንታ ለምሳሌ ለማዘጋጃ ቤት መማክርት 9000 ሩብል ይሁን የሚሉት
እነዚያ ቦልሼቢኮች ይቅርታ የማይደረግለት ድርጊት እየፈፀሙ ነው።



ይቻል ይሆናል ፥ ከማናቸውም ዲሞክራሲያዊ መሀከለኛ
ደመወዝ ለሹማምንት ጨምሮ ፤ ምክንያቱም በካፒታ
ሊዝም ስር ሙሉ በሙሉ የማያወላውል ዲሞክራሲ የሚ
ቻል አይደለም ፥ በሶሻሊዝም ውስጥም ዲሞክራሲ ሁሉ
የሚቻል መምንምኖ ይጠፋል ።

ቀልድ!አንድ ሰው አንድ ጠጉር ቢነቀልበት በራ
ይሆናል ወይ እንደሚለው የጥንት ቀልድ እውነት አስ
መስሎ ማሾፍ ነው ።

ዲሞክራሲን እስከመጨረሻው ማሳደግ ፥ የእድገቱን
ቅርፆች ፈልጉ ማውጣት ፥ እነሱንም በተግባር መፈ
ተን እና የመሳሰሉት ይኸ ሁሉ ለህብረተሰብ አብዮት
ለሚደረግ ትግል ከስራ ዘርፎች አንዱ ነው ። ተለይቶ
ሲታይ ፥ አንድም አይነት ዲሞክራሲ ሶሻሊዝምን አያ
መጣም ። ሆኖም በእውነተኛው ኑሮ ውስጥ ዲሞክራሲ
በፍፁም « ተነጥሎ አይታይም » ፥ ከሌሎች ነገሮች ጋር
« አብሮ ይታያል » ፤ በኤኮኖሚ ህይወት ላይ ተፅእኖ
ያደርጋል ፥ አሸጋገሩን (አለዋወጡን) ያንቀሳቅሰዋል ፤
በተራውም በኤኮኖሚ እድገት ተፅእኖ ይደረግበታል ።
የኑሮ ታሪክ ዲያሌክቲክሱ እንደዚህ ነው ።
ኤንግልስ ይቀጥላል ፡—

«ይህ የፊተኛው መንግስት ሃይል መፈረካከስና
አዲስና እውነተኛ ዲሞክራቲካዊ በሆነ መተካቱ
በርስ በርስ ጦርነት ሶስተኛው ክፍል ላይ በዝር
ርዝር ተገልፅዋል ። ነገር ግን እዚህ ላይ በጥቂት
መለያ በሆኑ ጠባዮቹ ላይ እንደገና ባጭሩ ማተ
ኮሩ አስፈላጊ ነበር ፤ ምክንያቱም ጀርመን ውስጥ
በተለይ በመንግስት ላይ ያለው አምልኮአዊ እም
ነት ከፍልስፍና ወደ አጠቃላይ የቡርዧውና የብዙ

ወዛደሮችም ንቃተ ህሊናነት ተላልፏል ። እንደ
ፍልስፍናዊው አስተሳሰብ ፥ መንግስት « የሃ
ሳብ በስራ መገለፅ » ወይም በምድር ላይ የእግዚ
አብሔር ንጉሳዊ አገዛዝ ነው ፤ በፍልስፍና ቃላ
ቶች ሲተረጐም ፥ ዘለአለማዊ እውነትና ትክክ
ለኛ ፍርድ የሚፈፀምበትን ወይም መፈፀም ያለ
በት ነው ። የጠቅላላው ህብረተሰብ ተግባሮችንና
ፍላጐቶች ሁሉ እስከ ዛሬ ሲጠበቁበት ከቆዩበት
መንገድ ፥ ማለትም ፥ በመንግስት ጥቅም ባላቸው
ሹማምንት አማካኝነት በስተቀር ፥ በሌላ መንገድ
ሊጠበቁ አይችሉም በማለት ከህፃንነቱ ጀምሮ
ማሰብ በለመደው ህዝብ ዘንድ በቀላሉ ስር
የሚሰደው ለመንግስት ከሱ ጋር በተያያዘ ነገር
ሁሉ የሚሰጠው አምልኮአዊ ክብር ከዚሁ የመነጨ
ነው ። ሰዎች ከውርስ የዘውድ አገዛዝ እምነት
ራሳቸውን ሲያላቅቁና በዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ
ሲምሉ ፤ ፍፁም ባልተለመደ ጀግንነት አንድ
ትልቅ እርምጃ የተራመዱ ይመስላቸዋል ።
በእውነቱ ከሆነ ታዲያ ፥ መንግስት በዲሞክራ
ቲክ ሬፑብሊክ ውስጥም ቢሆን በዘውድ አገዛዝ
ውስጥ ባላነሰ ደረጃ አንዱ መደብ በሌላው የሚ
ጨቆንበት መሳሪያ እንጂ ፥ ሌላ ነገር አይደለም ፤
ግፋ ቢል ወዛደሩ የመደቡን የበላይነት ለመቀዳ
ጀት ድል አድራጊ ትግሉን ካካሄደ በኋላ የወረሰው
ጠንቅ ነው ። በአዲስና ነፃ በሆኑ የሶሻል ሁኔታዎች
ውስጥ የሚያድገው ትውልድ መንግስትን እንኰ
ታኰቶ ከቆሻሻ መጣያ ወርውሮ እስኪጥለው
ድረስ ፥ ድል አድራጊው ወዛደር ፥ ልክ እንደ
ኰሚዩኑ ፥ ጭራሽ ክፉ የሆኑትን ገፆችን በተቻለው



መጠን ባንዳፍታ ጐርዶ ከመጣል ሊቆጠብ
አይችልም ። »

የዘውድ አገዛዝን በሬፑብሊክ በመተካቱ ጉዳይ ላይ
ተያይዞ በጠቅላላው በመንግስት ጥያቄ ላይ የሶሻሊዝም
መሰረቶች እንዳይረሱ ኤንግልስ ጀርመኖቹን አስጠን
ቅቋቸዋል ። የሱ ማስጠንቀቂያዎች ፥ በ« ጥምር » ተግ
ባራቸው ለመንግስት ያላቸውን አምልኰአዊ እምነ
ትና አምልኰአዊ አክብሮት ለገለጡት ለነአቶ ፀረቴሌ
ዎችና ቼርኖቮች እንደትክክለኛ ትምህርት አሁን ይነ
በባል !

ሁለት ተጨማሪ አስተያየቶች ። 1. በዲሞክራቲክ
ሬፑብሊክ ውስጥ ከዘውድ አገዛዙ «ባላነሰ ደረጃ» መን
ግስት » አንዱ መደብ በሌላው የሚጨቆንበት መሳ
ሪያ » ሆኖ ይቆያል ብሎ ኤንግልስ የተናገረው ሃቅ ፥
ጥቂት ስርአት አልበኞች « እንደሚያስተምሩት » የጭ
ቆናው ቅርፅ ለወዛደሩ ልዩነት የለውም ብሎ በምንም
አይነት አያመለክትም ። በጠቅላላ መደቦችን ለማጥ
ፋት በሚያደርገው ትግል በጣም ሰፊ ፥ በጣም ነፃና
በጣም ግልፅ የሆነ የመደብ ትግሉ ቅርፅና የመደብ ጭቆ
ናው ወዛደሩን በሰፊው ያግዙታል ።

2. ለምን አዲሱ ትውልድ ብቻ መንግስትን ከነኰ
ቱቱ የቆሻሻ ክምር ላይ አሽቅንጥሮ ሊጥለው ይችላል ?
ይህ አሁን የምናተኲርበት ጥያቄ ዲሞክራሲን ከማስ
ወገድ ጋር የተሳሰረ ነው ።

## 6. ኤንግልስ ዲሞክራሲን ስለማስወገድ ፤

« ሶሻል ዲሞክራት » የሚለው ቃል በሳይንስ
ረገድ ስህተት ከመሆኑ ሃቅ ጋር በመገናኘት ኤንግልስ

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየቱን ለማስረዳት አመቺ ጊዜ
ነበረው ።

ጥር 3 ፥ 1894 ፤ ማለትም አንድ አመት ተኩል
ከመሞቱ በፊት በሰባኛዎቹ አመታት በተለያዩ ጉዳዮች
በይበልጥም « በአለም አቀፍ » ጥያቄዎች [25] ፅሁ
ፎቹ አንዱ እትም መቅድም ውስጥ ፥ የተጠቀመው
« ኰሚዩኒስት » እንጂ « ሶሻል ዲሞክራት »
እንዳልነበረ ፅፍዋል ፥ ምክንያቱም በዚያን ሰአት ፈረ
ንሳይ ውስጥ ፕሩዶንስቶችና ጀርመን ውስጥ ላሳልያ
ያኖች ራሳቸውን ሶሻል ዲሞክራት ብለው ይጠሩ
ስለነበረ ነው ።

« . . . ለማርክስና ለኔ » ይላል ኤንግልስ ፥ «እነሆ
የኛን ልዩ ቋም ነገር ለይቶ ለማሳየት ሰፊ
ትርጉም ያለው (ኢላስቲክ) ቃል ለመጠቀም
ፍፁም አልተቻለም ነበር ። ዛሬ ብዙ ነገሮች
ተለዋውጠዋል ፥ ቃሉም « ሶሻል ዲሞክራት »
የኤኮኖሚ ፕሮግራሙ በጠቅላላ ሶሻሊስት ብቻ
ሳልሆነ ፥ ግን በቀጥታ ኰሚዩኒስት ፥ የመጨረሻ
የፖለቲካ ግቡም መንግስትን እንዳለ ከዚያም
የተነሳ ዲሞክራሲንም ጭምር ማሸነፍ ለሆነ ፓርቲ
(ተስማሚ) ትክክል ባይሆንም እንኳን ምናልባት
በቂ ይሆን ይሆናል ። ሆኖም የእውነተኛ (የኤ
ንግልስ መስመር) የፖለቲካ ፓርቲዎች ስሞቹ
በፍፁም ሙሉ በሙሉ ተስማሚ ሆነው አያው
ቁም ፤ ስሙ ሲቆይ ፓርቲው ያድጋል ። » [26]

ዲያሌክቲክስን የተካነው ኤንግልስ እስከመጨረሻው
ቀኖች ድረስ ከዲያሌክቲክስ አልተዛባም ። ማርክስና
እኔ ይላል ኤንግልስ ፥ አስደናቂ ሳይንሳዊ የሆነ ትክክ
ለኛ ስም ለፓርቲው ነበረን ፤ ነገር ግን እውነተኛ ፓርቲ



አልነበረም ፤ ይኸውም የሰፊው የወዛደር ፓርቲ አልነ
በረም ። አሁን (በአስራዘጠነኛው ምእተ አመት መጨ
ረሻ ላይ ) እውነተኛ ፓርቲ አለ ፤ ግን ስሙ በሳይንስ
ትክክል አይደለም ። ግድየለም ፓርቲው እስካደገ ድረስ
ስሙ በሳይንስ ትክክል አለመሆኑን እስካልተደበቀበ
ትና በትክክለኛው አቅጣጫ እንዲያድግ እስካልተከለ
ከለው ድረስ ስሙ በቂ ሊሆን ይችላል ! ።

ምናልባት እኛን ቦልሼቪኮችን አንድ ጥበብ በኤን
ግልስ ሁናቴ ያፅናናን ይሆናል ። እውነተኛ ፓርቲ
አለን ፤ በአስደናቂ እድገት ላይ ነው ፤ እንደዚህ ትር
ጉምየለሽና አስቀያሚ የሆነው እንደ « ቦልሼቪክ »
ያለው ቃል ፤ ምንም እንኳ በ1903 በብረስልስ —
ሎንዶን በነበረው ኰንግሬስ እኛ ብዙሃን . .[27] ከመ
ሆናችን ሀቅ በስተቀር ሌላ ነገር ባይመለከትም ፥
በቂ ይሆናል ። ምናልባት ሀምሌና ነሐሴ በሬፑብ
ሊካውያኖችና በ « አብዮተኛ » ንኡስ ከበርቴ ዲሞክ
ራሲ የኛ ፓርቲ መሰደዱ « ቦልሸቪክ » ለሚለው ስም
እንደዚህ ያለ ሁለንተና አክብሮት አትርፍዋል ፤ በተ
ጨማሪም ፤ ይህ ስደት ፓርቲያችን በእውነተኛ እድ
ገቱ ላይ ላደረገው ሃያል የሆነውን ታሪካዊ እርምጃ ሳለ
አበሰረ ፥ ምናልባት አሁን የፓርቲያችንን ስም ለመ
ለወጥ በሚያዝያ ያቀረብኩት ሃሳብ ላይ እንኳ ለመፅ
ናት እጠራጠር ይሆናል ። ምናልባት ለጓዶች « አስ
ታሪቂ ሃሳብ » አቀርባለሁ ፥ ማለትም ፥ ራሳችንን ኰሚ
ዩኒስት ፓርቲ ብለን መጥራት ፤ ግን « ቦልሼቪክ »
የሚለውን ቃል በቅንፍ ማስገባት . . .

ነገር ግን የፓርቲው ስም ጥያቄ ከአብዮተኛ ወዛደሩ
ለመንግስት ያለው ዝንባሌ ጥያቄ ጋር የማይወዳደር
አነስተኛ ነገር ነው ።

ስለመንግስት በተለመዱት ክርክሮች ውስጥ ፥ ኤን
ግልስ ማስጠንቀቂያውን ከተናገረበትና እኛ እግረ መን
ገዳችንን ከላይ ካመለከትነው ውጪ ስህተት ባለማቋ
ረጥ ይደረጋል ፥ ይኸውም የመንግስት መደምሰስ ደግሞ
የዲሞክራሲ መደምሰስ ማለት መሆኑ ባለማቋረጥ ተረ
ስቷል ፤ የመንግስት መንምና መጥፋት የዲሞክራሲ
መንምና መጥፋት ማለት ነው ።

ይህ አባባል በመጀመሪያ ሲታይ ያለቅጥ እንግዳና
ፍፁም የማይገባ ይመስላል ፤ እንዲያውም ፥ አንዳንዱ
የህብረተሰቡ ስርአት ክፉኛ ተለውጦ የህዳጣን ለብዙ
ሃን የበታች መሆን መርህ የማይከበርበት ሁኔታን መም
ጣት የምንጠባበቅ መስሎት መፍራት ይጀምር ይሆ
ናል — ምክንያቱም ዲሞክራሲ ማለት ይህን ትክክ
ለኛ መርህ ማወቅ ማለት ነውና ።

አይደለም ፥ ዲሞክራሲ ህዳጣን ለብዙሃን የበታች
ከመሆን ጋር አንድ አይደለም ። ዲሞክራሲ የህዳጣን
ለብዙሃን የበታች መሆን የሚታወቅበት መንግስት
ነው ፤ ማለትም አንድ መደብ በሌላው ላይ ፥ አንዱ የህ
ዝብ ክፍል በሌላው ላይ አመፅን በስርአት የሚጠቀ
ምበት ድርጅት ነው ።

እኛ መንግስትን መደምሰስ ከፍተኛው ግባችን አድ
ርገን ወስደናል ፥ ይኸውም ማናቸውም የተደራጀና
ስርአት ያለው አመፅ በሙሉ ፥ በአጠቃላይ በሰው ላይ
አመፅን መጠቀምን በሙሉ ማለት ነው ። የህዳጣን
ለብዙሃን የበታችነት የማይከበርበት የህብረተሰብ ስር
አት ይመጣል ብለን አንጠብቅም ። ግን ለሶሻሊዝም
ስንጥር ወደኰሚዩኒዝም እንደሚያድግ እናምናለን ፥
ስለዚህ ፥ በአጠቃላይ በህዝብ ላይ አመፅ የማድረግ



አንድን ሰው ከሌላው በታች የማዋል ፥ አንድን የህዝብ
ክፍልም ከሌላው በታች የማድረግ ፍላጐት ፥ ህዝቡ
ሁሉ ሁኔታዎችን ያለሀይልና ያለትእዛዝ ለማክበር
ስለሚለማመድ ፥ በአጠቃላይ ይጠፋሉ ።

ይህን የልማድ ነጥብ አበክሮ ለማሳየት ፥ ኤንግልስ
« በአዲስና ነፃ በሆኑ የሶሻል ሁኔታዎች ውስጥ ስለ
ሚያድግ አዲስ ትውልድ « መንግስትን ከነኰተቱ
ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ወርውሮ እንደሚጥል » ማን
ኛውንም—አይነት መንግስት ፥ የዲሞክራቲክ ሪፑብ
ሊክ መንግስትንም ጭምር ይናገራል ።

ይህን መግለፅ እንዲያስችል የመንግስትን መንምና
መጥፋት የኤኮኖሚ መሰረቱን ጥያቄ መመራመር አስ
ፈላጊ ነው ።

* * *

## ምዕራፍ 5
## ለመንግስት መመንመን ኤኮኖሚ መሰረት

ማርክስ ይህንን ጉዳይ የጐታ ፕሮግራም ትችት
ሜይ 5,1875 ለብሬክ በፃፈውና እስከ 1891 ድረስ
ሳይታተም በኖዩ ሳይት ቅፅ 91 በሩሲያ ላይ እትም
የወጣ በሚለው ፅሁፍ በሚገባ ገልፆታል ። የሶሻሊዝ
ምን ነቀፌታ የሚያጠቃልለው የዚህ ድንቅ ስራ
ሃይለኛ ማስተባበያ ቃል በመያዙ እርግጠኛ ክፍሉን
በተለይም በኮሚዩኒዝም እድገትና በመንግስት መመ
ንመን መካከል ያለው ግንኙነት ትንተናን ሸፍኖታል ።

### 1. በማርክስ የጉዳዩ አቀራረብ

ቀደም ብለን የመረመርናቸውን ሜይ 5 ቀን 1875
ማርክስ ለብራኬ የፃፈውንና ማርች 28 ቀን 1875
ኤንግልስ ለቤቢል የፃፈውን ደብዳቤዎች ጥራዝነጠቅ

በሆነ መንገድ ማንፀፀር ማርክስ ከኤንግልስ ይልቅ « የመንግስት ዋና ደጋፊ » እንዲሁም በሁለቱ ፀሀፊ ዎች መካከል ስለመንግስት ጉዳይ ያለው የአስተያየት ልዩነት እጅግ የተራራቀ ሊመስል ይችላል ።

ስለ መንግስት የሚደረገው ልፍለፋ ጨርሶ እንዲ ቆም እንዲሁም « መንግስት » የሚለው ቃል ከፕሮ ግራሙ ከነጭራሹ ተሰርዞ በምትኩ « ህብረተሰብ » የሚለው ቃል እንዲገባ ኤንግልስ ለቤብል ሃሳብ አቅ ርቦ ነበር ። ኤንግልስ እንዲያውም በትክክለኛው የቃሉ ትርጉም ኮሚዩውኑ መንግስት መሆኑ መቅረቱን ገል ፅዋል ። ይሁን እንጂ ማርክስ በኮሚዩኒዝም ውስጥ የመንግስትን መኖር አስፈላጊነት የተቀበለ ይመስል «የወደፊቱ የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ መንግስት ጠባይ» ብሎ ተናግሯል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለው አስተያየት በመሰረቱ ስህተት ነው ። ጠለቅ አድርጐ ለተመራመረው ስለ መንግስትና እያደረም ስለመመንመኑ የማርክስና የኤ ንግልስ አስተያየቶች ፍፁም ተመሳሳይ ናቸው ። ከላይ የተጠቀሰው የማርክስ አባባልም የሚያመለክተው ስለ ዚሁ የመንግስት Nature of the state ጠባይ መንምና መጥፋት ሂደት ነው ።

በእርግጥ የወደፊት «መንምኖ መጥፊያው» ትክክለኛ ጊዜ መች እንደሆነ ለመግለፅ አይቻልም ፤ በተለያዩ ነጥቦች ላይ በተለይም የረጅም ጊዜ ሂደት መሆኑ ግልፅ ነውና ። በማርክስና በኤንግልስ መካከል የሚታየው ልዩነት ሁለቱ ስለፃፉና በተለያዩ አላማዎችም ላይ ስላ ተኮሩ ነው ። ኤንግልስ በተብራራና ዝርዝር ባለ ዘዴ በጊዜው ስለ መንግስት ያለው አስተሳሰብ ምን ያህል



የተጃጃለ እንደሆነ ለቤቢል ለመግለፅ ተነሳሳ ። ማርክስ ግን ይህን ጉዳይ የነካው እግረ መንገዱን ነው ፤ ፍላጐቱና አላማው ስለ ኮሚዩኒስት ህብረተሰብ እድገት ነበርና ።

መላው የማርክስ ቲዎሪ የእድገትን ቲዎሪ—በማ ያወላውል ፤ ፍፁም በሆነ ፣ ጥንቃቄ በተመላበትና ጥርት ባለ መልኩ በዘመናዊ ካፒታሊዝም ላይ ማዋል ነው ። በእርግጥ ማርክስ ይህንን ቲዎሪ ለመጪው የካፒታሊ ዝም መንኮታኮትና ለወደፊቱ የኮሚዩኒዝም የወደፊት እድገት እንዴት እንደሚያውለው ችግር ገጥሞት ነበር ።

እንግዲህ የወደፊቱ የኮሚዩኒዝም የወደፊት እድገት ጉዳይ ሊታይ የሚቻለው ምንን መነሻ በማድረግ ነው ? የወደፊቱ የኮሚዩኒዝም የወደፊት እድገት ጉዳይ መነ ሻው ምንጩ ካፒታሊዝም መሆኑ ፣ ታሪካዊ እድገቱ ከካፒታሊዝም መሆኑና ካፒታሊዝም የወለደው የሶ ሻል ሀይል ውጤት መሆኑ ነው ። ማርክስ ተምኔታዊ የሆነና ሊታወቅ ስለማይቻልም ነገር መላቢስ ግምት ለመስጠት ሙከራ ለማድረጉ ምንም ምልክት የለም ። ማርክስ የኮሚዩኒዝምን ጉዳይ የመረመረው የስነ ፍጥረት ተመራማሪ ስለእድገት ሲያጠና ፣ ለምሳሌ አዲስ የፍጡር አይነት ፣ ምንጩ ይህና ይህ ነው ፣ ይህና ይህ ደግሞ የለውጡ ትክክለኛ አቅጣጫ ነው እንደሚለው ነው ።

በመጀመርያ ማርክስ የጐታ ፕሮግራም በመንግስትና በህብረተሰብ መካከል ስላለው ግንኙነት ያስከተለውን ውዥንብር ወደጐን ገሸሽ ያደርገዋል ። እርሱም ሲፅፍ ፤

«… የዛሬው ኅብረተሰብ» በሰለጠኑት አገሮች ውስጥ ሁሉ የሚገኝ የካፒታሊስት ህብረተሰብ ነው ። ይህም ህብረተሰብ ከመካከለኛው ዘመን ምልክቱ ከሞላ ጐደል

ነፃ የሆነ ፤ በያንዳንዱ አገር የተለየ የታሪክ እድገት ከሞላ ጐደል የተሻሻለና ከሞላ ጐደል የዳበረ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ « ያሁኑ ጊዜ መንግስት » እንደ አገሩ ድንበር የለያያል ። በፕሩሶ ጀርመን ያለው የንጉስ ነገስት ግዛት በስዊዘርላንድ ካለው ልዩ ነው ፤ በአሜሪካ ያለው እንግሊዝ ካለው ልዩ ነው ። ስለዚህ « ያሁኑ ጊዜ መንግስት » ልብ ወለድ ነው ።

ይሁን እንጂ የተለ ያዩት የሰለጠኑ አገሮች የተለያዩት መንግስታት ምንም እንኳ በብዙ መንገዶች የቅርፅ ልዩነት ቢኖራቸውም ፣ የዘመናዊ ቡርዧ ህብረተሰብ ላይ መመስረታቸውና ሁሉም የበለፀጉት በካፒታሊስት ስርአት ላይ መሆኑ በጋራ ያመሳስላቸዋል ። ስለዚህም የሚመሳሰሉበት መሰረታዊ የጋራ ባህሪያት አላቸው ። በዚህ መልክ «የአሁኑን ጊዜ መንግስት» ሁኔታና ያሁኑ የቡርዧ ህብረተሰብ መሰረቱ የሆነው ከሞተ በኋላ ስለሚኖረው ስለወደፊቱ መንግስት በማነፃፀር ለመናገር ይቻላል ።

«ከዚህ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ፣ የመንግስት ሁኔታ በኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ውስጥ ምን አይነት ለውጥ ያደርጋል የሚል ነው ። በሌላ አባባል በኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ዛሬ መንግስት ከሚፈፅማቸው ተግባራት ጋር የሚመሳሰሉ ምን ማህበራዊ ተግባራት ይኖራሉ ? ይህ ጥያቄ መመለስ ያለበት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ነው ። እንደ ቁንጫ እንጣጥ እንጣጥ በማለት ሺ ጊዜ ህዝብና መንግስት የሚሉትን ቃላት በማጣመር ማንም ወደ ችግሩ መቅረብ አይችልም»[28] ።

ማርክስ « የህዝብ መንግስት » የሚለውን አባባል እንዲህ ከቀለደበት በኋላ ጉዳዩን አቀነባብሮ ለጉዳዩ



ሳይንሳዊ መልስ ለማግኘት የሚቻለው በሳይንሳዊ መረጃዎች በመጠቀም መሆኑን ያስገነዝበናል ።

በቴምኔታውያንና የሶሻሊስት አብዮትን በሚፈሩ የዛሬ ዘመን አድር ባዮች የተዘነጋው በማያወላውል መንገድ በመላው የእድገት ቲዎሪ ፣ በጠቅላላው በሳይንስ የተረጋገጠው ከካፒታሊዝም ወደኮሚኒዝም መሸጋገሪያ የሚሆን ልዩ ድርሻ ወይም ልዩ የመሸጋገሪያ ወቅት ያለጥርጥር መኖር እንዳለበት ነው ።

## 2. ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚኒዝም ሽግግር ፤ ማርክስ በመቀጠል ፡

«በካፒታሊስትና በኮሚዩኒስት ህብረተሰብ መካከል አንዱ ወደ ሌላው አብዮታዊ ለውጥ የሚያደርግበት ዘመን አለ ። ከዚህም ጋር አብሮ መንግስት የወዛደሩ አብዮታዊ የበላይ ገዥነት የሚሆንበት የፖለቲካ ሽግግር ዘመን ይኖራል ።» ማርክስ እዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቻለው በዘመናዊ የካፒታሊስት ህብረተሰብ ውስጥ የወዛደሩ ሚና ምን እንደሆነ በመተንተን ፤ የዚህን ህብረተሰብ እድገት መረጃ በመመርመርና የወዛደሩና የቡርዧው ጥቅም ሊታረቁ የማይችሉ ተፃራሪዎች መሆናቸውን በመገንዘብ ነው ።

ቀደም ሲል ጉዳዩ እንደሚከተለው ሆኖ ቀርቦ ነበር፤ ወዛደሩ ነፃነቱን ለማግኘት ቡርዧውን ገልብጦ የፖለቲካ ስልጣንን ጨብጦ አብዮታዊ የበላይ ገዥነቱን መመስረት አለበት ። አሁን ደግሞ ጉዳዩ ወደኮሚዩኒዝም በማደግ ላይ ካለው የካፒታሊስት ህብረተሰብ ወደ ኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ለመሸጋገር « ያለ ፖለቲካ መሸጋገሪያ ዘመን » አይቻልም ፣ በዚህም የመሸጋገሪያ ጊዜ መንግስት የወዛደሩ የበላይ ገዥነት መሆን ይገባዋል ።

እንግዲህ ይህ የበላይ ገዥነት ከዲሞክራሲ ጋር ያለው
ግንኙነት ምንድነው ?

<u>የኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ</u> ሁለቱን ፅንስ ሃሳቦች ጐን
ለጐን እንዳስቀመጣቸው ተመልክተናል ። ይኸውም
«ወዛደሩን ወደ ገዥ መደብ ከፍ ማድረግ» እና «ለዲ
ሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ማሸነፍ » ። ከላይ የተ
ዘረዘሩትን ሁሉ መሰረት በማድረግ ከካፒታሊዝም
ወደ ኮሚዩኒዝም በሚደረገው ሽግግር ዲሞክራሲ እን
ዴት እንደሚለወጥ በትክክል መረዳት ይቻላል ።

የካፒታሊስት ህብረተሰብ እጅግ አመቺ በሆነ
ሁኔታ ካደገ ከሞላ ጐደል በዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ
ውስጥ የተሟላ ዲሞክራሲ ይኖራል ። ነገር ግን ይህ
ዲሞክራሲ በካፒታሊስት ብዝበዛ ሳቢያ ሁል ጊዜ
ጠባብ ገደብ ይሰጠዋል ። ስለዚህም በትክክለኛው
ሁኔታው ከተረዳነው ዲሞክራሲው ሁል ጊዜ ለጥቂቱ
ብቻ ፥ ለባለንብረቱ መደብ ብቻ ፥ ለሀብታሙ ብቻ ሆኖ
ይቀራል ። በካፒታሊስት ህብረተሰብ ውስጥ ነፃነት
ሁልጊዜ ከጥንታዊ ግሪክ ሪፑብሊኮች ውስጥ ከነበረው
ነፃነት ተመሳሳይ ነው ፥ ነፃነት ለባሪያ ባለቤቶች ።
በካፒታሊስት ብዝበዛ ሳቢያ ዘመናዊ የደመወዝ ባሮች
በችግርና በድህነት እጅግ የደቀቁ በመሆናቸው «ለዲሞ
ክራሲ ሊጨነቁ አይችሉም » «ለፖለቲካ ሊጨነቁ አይ
ችሉም» ፤ በአጠቃላይ ሁኔታ ብዙሃኑ ህዝብ በአገሪቱ
ፖለቲካ እንዳይሳተፍ ይታገዳል ። የዚህን አባባል ትክ
ለኝነት በጀርመን ሁኔታ በትክክል ለማረጋገጥ ይቻ
ላል ። በጀርመን አገር የህገ መንግስት ህጋዊነት
በጣም ረዘም ላለ ጊዜ ፥ ግማሽ ምእተ አመት (1871-1914)
ያህል ፅኑ ሆኖ ቆይቷል ። በዚህ ዘመን ውስጥም ከሌ
ሎች አገሮች ይበልጥ ሶሻል ዲሞክራሲ « ህጋዊነትን



በመጠቀም » በርከት ያሉ ሰራተኞችን በፖለቲካ
ፓርቲ ለማደራጀት ችሏል ።

እንግዲህ እስካሁን በካፒታሊስት ህብረተሰብ ውስጥ
የታየው በፖለቲካ የነቃውና ንቁ የደመወዝ ባሪያ የሆ
ነው መጠኑ የቱን ያህል ነው ? ከአስራ አምስት ሚሊ
ዮን የደመወዝ ሰራተኞች አንድ ሚሊዮን የሶሻል ዲሞ
ክራሲ ፓርቲ አባሎች ናቸው ። ከአስራ አምስቱ ሚሊ
ዮን ሰራተኞች መካከል ሶስት ሚሊዮን በሰራተኛ
ማህበራት ተደራጅተዋል ።

የካፒታሊስት ህብረተሰብ ዲሞክራሲ እጅግ ጥቂት
የሆኑ የህብረተሰቡ ክፍል ፥ የሃብታሞች ዲሞክራሲ
ነው ። በጣም ጠጋ ብለን ፥ የካፒታሊስት ዲሞክራሲን
የአሰራር ሁኔታ ብንመለከት በሁሉም ቦታ «ጥቃቅን የሚ
ባሉ»የምርጫ መብት ዝርዝሮች(ሴቶችን ማግለል፤ወዘተ)
በህዝብ ተቋሞች የአሰራር ሁኔታ ፥ በመሰብሰብ መብት
ላይ ባሉት ጉልህ እንቅፋቶች ( የህዝብ ህንጻዎች «ለለ
ማኞች » አይደሉም ) የእለቱ ዜና አቀነባበር ጥርት ባለ
የካፒታሊስት መንገድ መሆን ፥ ወዘተ ፥ ዲሞክራሲ
ገደብ በገደብ ላይ ተጭኖበት እናያለን ። እነዚህ ገደቦች
ግልልቶች ፥ ለድሃው የተደቀኑ እንቅፋቶች ቀላል ይመ
ስላሉ ። በተለይም ችግርን ላልቀመሰና የጭቁን መደ
ቦችን ኑሮ በቅርብ ላላየ ሰው (ዘጠኝ አስረኛው እንዲ
ያውም ዘጠና ዘጠኝ መቶኛ ሊሆኑ የሚችሉ የቡርዧ
ህዝባዊ ድርጅት ጉዳይ አዋቂዎችና የፖለቲካ ሰዎች
ከዚህ ክፍል ናቸው ፤ በዲሞክራሲ ላይ በተጣለው
ገደብ ቀላል ሊመስል ይችላል ። ነገር ግን በድምሩ እነ
ዚህ ገደቦች ደሀውን ከፖለቲካና ከዲሞክራሲም ንቁ
ተሳትፎ ጨምቀው ይተፉታል ። ማርክስ የካፒታሊስ
ትን ዲሞክራሲ <u>ይዘት</u> ድንቅ በሆነ መንገድ በመረ

ዳቱ የፓሪስን ኮሚዩን ልምድ ሲተነትን ጭቁኖች
የትኛው የጨቋኝ መደብ ወኪል በፓርላማ እንደሚወ
ከልና እንደሚጨቁናቸው እንዲወስኑ በየጥቂቱ አመ
ታት ይፈቀድላቸዋል ብሏል ።

ነገር ግን ከዚህ የካፒታሊስት ዲሞክራሲ — ጠባ
ብና በስውር መንገድ ደሃውን የሚያገል በመሆኑ ሁለ
ንተናው አስመሳይና ውሸታም ከሆነው — ሊበራል
ፕሮፌሰሮችና አድርባይ ንኡስ ከበርቴዎች ሊያሳም
ኑን እንደሚፈልጉት-የወደፊት እድገት በቀላል ፣ በቀ
ጥታና ያለ እንቅፋት ወደ « ከፍተኛና እጅግ ከፍተኛ
ዲሞክራሲ » የሚጓዝ አይደለም ። የወደፊት ግስጋሴ
ማለትም ወደ ኮሚዩኒዝም የሚካሄደው በወዛደሩ የበላይ
ገዥነት እንጂ በሌላው አቅጣጫ አይቻልም ። ምክንያ
ቱም የካፒታሊስት በዝባዦች ተቃውሞ የሚሰበረው
በሌላ በማንም ወይንም በሌላ በምንም መንገድ ስላይ
ደለ ነው ። የወዛደሩ የበላይ ገዥነት ማለትም ጨቋ
ኞችን ለመጫን እንደ ገዥ መደብ የሚደራጀው የጭ
ቁኖች ግንባር ቀደም ድርጅት ዲሞክራሲን የማስፋፋት
ውጤት ብቻ አይኖረውም ። በአንድ ጊዜ ዲሞክራሲን
በጣም በማስፋፋት ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሞክራሲ ለደ
ሃው ፣ ዲሞክራሲ ለህዝቡ እንጂ ዲሞክራሲን ለሃብታም
ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ የወዛደሩ የበላይ ገዥነት
በጨቋኞች በበዝባዦችና በካፒታሊስቶች ነፃነት ላይ
በርከት ያሉ ገደቦች ያደርጋል ። የሰውን ልጅ ከደ
መወዝ ባርነት ነፃ ለማውጣት ስንል እነሱን መጨ
ቆን አለብን ። ተቃውሟቸውም በሃይል መደምሰስ
ይኖርበታል ። አመፅና ጭቆና ባለበት ሁሉ ነፃነትና
ዲሞክራሲ አለመኖሩ ግልፅ ነው ።



እንባቢ እንደሚያስታውሰው ሁሉ ኤንግልስ ለቤ
ቤል በፃፈው ደብዳቤ « ወዛደሩ መንግስትን የሚጠቀ
ምበት ለነፃነት ሲል ሳይሆን ባላንጣዎቹን ለመጫን
ነው ። ስለነፃነት መናገር እንደተቻለም የመንግስት
ህልውና ይቋረጣል » በማለት ድንቅ አድርጉ ገልፆ
ታል ።

እንግዲህ ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚዩኒዝም በሚደረ
ገው ሽግግር ዲሞክራሲ የሚያደርገው ለውጥ ዲሞክ
ራሲን ለብዙሀኑ ህዝብ አድርጎ የህዝብን በዝባዦ
ችና ጨቋኞች በሀይል መጨቆን ማለት ከዲሞክራሲ
ማግለል ነው ።

« ስለ ነፃነት መናገር የሚቻለው » የካፒታሊስቶች
ተቃውሞ ፍፁም ሲደመሰስ ፣ ካፒታሊስቶች ሲጠፉ ፣
መደቦች ሲጠፉ ፤ (ማለትም የህብረተሰቡ አባሎች ከም
ርት መገልገያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ሳይለያዩ)
« መንግስት . . . ህልውናው ሲቋረጥ» በኮሚኒስት
ህብረተሰብ ብቻ ነው ። ያን ጊዜ ብቻ ነው እውነተኛ
ውንና ሙሉውን ዲሞክራሲ እገሌ ከእገሌ የማይለ
ውንም ዲሞክራሲ መገንዘብ የሚቻለው ።ከካፒታሊስት
ባርነት ፣ መጠን ከሌለው ጭካኔ ነፃ በመሆን ፣ አስከፊ
የሆነ የካፒታሊስት ብዝበዛ ሲቀር ብቻ ነው ዲሞክራሲ
መመንመን የሚጀምረው ።

ህዝቡም እያደረ ለዘመናት የታወቁትንና ለብዙ ሺ አመ
ታት መሰረታዊ መርህ ሆነው የተቆጠሩትን የህብረተ
ሰብ መተዳደሪያ መደበኛ ደንቦች ማክበር ሲለምድ
ዲሞክራሲም ይመነምናል ። ህዝቡም ያለ ሃይል ፣ ያለ
ማስገደድ ፣ ያለበታችነትና ማስገዳጃ የሆነው መንግስት

የተባለው መሳሪያ ሳይኖር መተዳደሪያ ደንቦችን
ያከብራል ።

« መንግስት ይመነምናል » የሚለው አባባል የተ
መረጠው በትክክል ነው ። ምክንያቱም ዝግተኛና
ግብታዊ የሂደት ጠባዩ ይህንኑ ስለሚገልፅ ነው ። ልማ
ድ ብቻ ነው እንዲህ ያለ ውጤት የሚኖረው ። ብዝበዛ፣
ቁጣን የሚቀሰቅስ ምንም ነገር ከሌለ ፣ ቅሬታንና አመ
ፅን የሚቀሰቅስ ምንም ነገር ከሌለ ፣ በሃይል የሚጨቆን
ሁኔታ ሳይፈጠር ባካባቢያችን ሰዎች አስፈላጊውን
የህብረተሰብ ደንብ የማክበር ልማድ እንዳላቸው
በሚሊዩን በሚቆጠሩ ሁኔታዎች ለማረጋገጥ እን
ችላለን ።

ስለዚህ በካፒታሊስት ህብረተሰብ ውስጥ ያለው ለጥ
ቂቶችና ለሀብታሞች ብቻ ከመሆኑም በላይ የተመጠነ፣
ጐስቋላና ሀሰት ዲሞክራሲ ነው ። ወደ ኮሚዩኒዝም መሸ
ጋገሪያ ዘመን የሆነው የወዛደሩ የበላይ ገዥነት ለመ
ጀመሪያ ጊዜ ለብዙሃኑ ህዝብ ዲሞክራሲ ከመፍጠሩም
በላይ በዝባዥ የሆኑትንና አነስተኛ ወገኖች ይጨቁናል።
እውነተኛውንና የተሟላውን ዲሞክራሲ የሚሰጠው
ኮሚዩኒዝም ብቻ ነው ። በይበልጥ የተሟላ እየሆነ በሄደ
መጠን ደግሞ አስፈላጊ መሆኑ ይቀርና በገዛ ራሱ መን
ምኖ ይጠፋል ።

በሌላ አባባል በዘመነ ካፒታሊዝም አንዱ መደብ
ሌላውን የሚጨቁንበት ፣ በተለይም ጥቂቱ ብዙሃኑን
የሚጨቁንበት ግብሩ ከባህርዩ የሰመረ መንግስት አለ ።
በርግጥም እንዲህ አይነቱ ጥቂቶች በዝባዦች በብዙሃኑ
ተበዝባዦች መጨቆን እንዲሰፍን ከተፈለገ ከፍተኛ
ጭካኔና አረመኔነት አስፈላጊ ይሆናል ። የሰውም ልጅ



በባርነት ፣ በጭሰኝነትና በደመወዝተኝነት ለመዳከር
የደምባህር አፍስሷል ።
ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚኒዝም በሚደረገው ሽግግ
ርም ቢሆን አሁንም ጭቆና አስፈላጊ ነው ። ነገር ግን
አሁን ጭቆናው ብዙሃን ተበዝባዦች በጥቂት በ
ዝባዦች ላይ የሚፈፅሙት ነው ። « መንግስት » የተ
ባለው ልዩ መሳሪያ ፣ ልዩ የመጨቆኛ መሳሪያ አሁንም
አስፈላጊ ነው ። ነገር ግን የሽግግር መንግስት ነው ።
ሆኖም ትርጉሙ በተለምዶ የያዘው ትርጉሙ አይደ
ለም ፤ ምክንያቱም የጥቂቶቹ በዝባዦች
ትናንት የደመወዝ ባሮች በነበሩት በብዙሀኑ መጨቆን
ብዙሀኑ ይደርስባቸው ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ቀላል ፣
አነስተኛና እንግዳ ያልሆነው ነገር በመሆኑ ነው ።
የባሮችን ፣ የገባሮችንና የደመወዝተኞችን አመፅ ለማ
ፈን ከሚፈሰው ደም እጅግ አነስተኛ ይሆናል ። ከዚ
ህም ሌላ ለብዙሃኑ ህዝብ ዲሞክራሲን ከማስፋፋቱ
ጋር ለመጨቆኛ የሚያስፈልገው ልዩ መሳሪያ መጥፋት
የሚጀምር መሆኑ ተስማሚ ነው ። እርግጥ በዝባዦች
ያለ እንዲህ ያለ የረቀቀ መሳሪያ ህዝቡን ለመጨቆን አይ
ችሉም ። ነገር ግን ህዝቡ ጨቋኞችን በቀላል « መሳ
ሪያ » እንዲያውም ያለ « መሳሪያ » ያለ ልዩ መሳሪያ
ቀላል በሆነ የሰፊው ህዝብ የትጥቅ ድርጅት (ለምሳሌ
በወዛደር ሶብዬቶች ተመራጮችና የወታደሮች ወኪሎች)
ለመጫን ይችላል ።

ምክንያቱም ማንም የሚጨቆን ስለሌለ ። « ማንም »
ስንል በመደብና ፣ በተወሰነ የህዝብ ክፍል ላይ
ደንበኛ ትግል ስለማይካሄድ ከሚለው አንፃርነው ።
የመንግስትን አስፈላጊነት ፈፅሞ የሚሽረው ኮሚዩ

ኒዝም ብቻ ነው ። ሀሳባዊያን አይደለንም ። ስለዚህም አንዳንድ ግለሰቦች ከልክ ያለፈ ተግባር ሊፈፅሙ መቻላቸውንና እንደሚፈፅሙም አሌ አንልም ፤ ወይም ደግሞ ይህንን ከልክ ያለፈ ተግባር መግታት አስፈላጊ መሆኑን አንክድም ። ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ ምንም ልዩ መሳሪያ ፣ ምንም አይነት የጭቆና መሳሪያ ለዚህ አያስፈልግም ። ይህን ልክ በዘመናዊው ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች አምባጓሮን እንደሚያቆሙ ወይም ሴትን ከመደፈር እንደሚያስጥሉ በቀላል ዘዴና በአፋጣኝ ሊቋቋመው ይችላል ።

ሁለተኛም የማህበራዊ ኑሮ መደበኛ ደንቦች መጣስን የሚያስከትለው ከልክ የማለፍ ተግባር መሰረታዊ መንስኤ የሰፊው ህዝብ መበዝበዝ ፣ መቸገርና መደህየት መሆኑን እናውቃለን ። የዚህ ዋነኛ መንስኤ ከተወገደ ከልክ ያለፈ ተግባሮችም በግድ «መመንመን» ይጀምራሉ ። በምን ያህል ፍጥነትና በምን አይነት ቅደም ተከተል መሆኑን አናውቅ እንጂ እንደሚመነምኑ እናውቃለን ። ከነርሱ መመንመን ጋር ፣ መንግስት ይመነምናል ።

በምኞት አለም ውስጥ ሳይገባ ማርክስ በተሟላ ሁኔታ አሁን ስለወደፊቱ ሊገለፅ የሚቻለውን ማለትም የኮሚኒስት ህብረተሰብ ዝቅተኛና ከፍተኛ ደረጃዎች ልዩነት ገልጿል ።

### 3. የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ የመጀመሪያው ደረጃ

የጐታ ፕሮግራም ሂስ በተሰኘው ፅሁፍ ውስጥ ማርክስ በሶሻሊዝም ወዛደሩ « ምንም ያልተቀነሰበት» ወይም «የወዙን ሙሉ ውጤት» ያገኛል የሚለው የላሳል ሀሳብ ልክ አለ መሆኑን በዝርዝር አስረድቷል።



ግስት መዋቅር መሀከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ፤ ሶስተኛም ፣ የአካባቢ አገዛዝን በሚመለከት ።

ኤንግልስ በኤርፉርት ፕሮግራም ረቂቅ ሂስ ውስጥ አቢይ ርእስ አድርጐ ያቀረበው የሬፑብሊክን ጉዳይ ነው ። የኤርፉርት ፕሮግራም ረቂቅ የአለም አቀፍ ሶሻል ዲሞክራቶች ያስገኘላቸውን ጠቃሚ ነገሮች በምናስታውስበት ጊዜ ፣ ፕሮግራሙ በጠቅላላው ለሁለተኛው አለም አቀፍ የወዛደሮች ማህበር ጥሩ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡን እንገነዘባለን ፣ እንዲያውም ያላንዳች ማጋነን ኤንግልስ በዚህ ሂስ አማካይነት በሁለተኛው አለም አቀፍ የወዛደሮች ማኅበር ውስጥ የታየውን አድርባይነት ነቀፏል ለማለት እንችላለን ።

« የረቂቁ የፖለቲካ ጥያቄዎች ፣ » ይላል ኤንግልስ «አንድ ትልቅ ስህተት አለባቸው ። መባል የነበረበት ነገር እዚያ ውስጥ የለም » (መስመር የኤንግልስ)

በኋላ ፣ የጀርመን ህገ መንግስት በጣም አድሃሪ የሆነው የ1850 ህገ መንግስት ትክክል ግልባጭ መሆኑን ይገልፃል ፤ ቪልሄልም ሊብክኔሽት እንደፃፈው ይሽታግ (የጀርመን ሸንጐ) « የፍፁም ፈላጭ ቆራጭነትን መሸፈኛ የበለስ ቅጠል » ነው ። ስለሆነም የትንንሽ መንግስታትን ህልውና ፣ የትንንሽዋን ጀርመን ፌዴሬሽን ህልውና በሚያረጋግጥ ህገ መንግስት መሰረት « ሁሉም የማምረቻ መገልገያዎች ወደ ህዝብ ይዞታ ይዙሩ »ብሎ መመኘት «ቅልጥ ያለ ጅልነት»ነው ይላል ጀርመን ሬፑብሊክ ትሁን የሚለውን ጥያቄ በፕሮግራሙ ማስገባት በህጋዊ መንገድ የማይቻል መሆኑን ጠንቅቆ በማወቁ ኤንግልስ

ሀብረተሰብ ናቸው ። እያንዳንዱ የሀብረተሰብ አባል
ለኅብረተሰቡ አስፈላጊ የሆነ ተግባሩን በማከናወን
ይህን ያህል ሰርቷል የሚል የምስክር ወረቀት ከሀ
ብረተሰቡ ይቀበላል ። በዚህም የምስክር ወረቀት ከሕዝብ
መጋዘኖች ተመጣጣኝ የሆኑ ለአገልግሎት የሚውሉ እቃ
ዎችን ያገኛል ። ለሀብረተሰቡ አገልግገሎት የሚውለው
ዋጋ ከተቀነሰ በኋላ እያንዳንዱ ሰራተኛ ለሀብረተሰቡ
ባበረከተው መጠን ያገኛል ።

« እኩልነት » በግልፅ ልቆ ይነግሳል ።

ነገር ግን ላሳል እንዲህ ያለ ሰርአተ ማህበርን
በማሰብ (ብዙውን ጊዜ ሶሻሊዝም የሚባለውና ማር
ክስ ግን የመጀመሪያ ደረጃ ኮሚዩኒዝም የሚለው) ይህ
« አድልዎ የሌለበት እደላ » ነው ይለዋል ። ይህም
«የሀብረተሰብ አባሎች ሁሉ የወዝ ውጤትን እኩል
ለመካፈል መብት አላቸው ማለት ነው ።» በዚህም የላ
ሳልን ስህተት ማርክስ ይፋ ያወጣዋል ።

« እኩል መብት» በርግጥ እዚህ አለን ይላል ማር
ክስ ፣ ነገር ግን እንደማንኛውም መብት እኩል ያለመ
ሆኑን በቅድሚያ የሚያስብ ገና « የቡርዧ መብት »
ነው ። ማንኛውም መብት የማይመሳሰሉና እርስ
በርስ እኩል ላልሆኑ ሰዎች እኩል መለኪያን ስራ
ላይ ማዋል ነው።ስለዚህ ነው «የእኩልነት መብት» በርግ
ጥም እኩልነትን የሚጥስና ፍትህን የሚያሳጣ ። እርግጥ
ማንም ሰው ከሌላው ሰው የተመጣጠነ ጉልበት
እስከሰጠ ድረስ ከወዙ ውጤት እኩል ድርሻ
(ከላይ የተጠቀሰው ከተቀነሰ በኋላ) ይሰጠዋል ።

ነገር ግን ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ አይደሉም ። አንዱ
ጠንካራ ሲሆን ሌላው ደካማ ነው ። አንዱ ያገባ ሲሆን



ሌላው ያላገባ አንዱ ብዙ ልጆች ሲኖሩት ሌላው ጥቂት
ይኖሩታል ። ሌላ ሌላም ልዩነቶች አሉ ። ማርክስ ሁኔ
ታውንእንደ ሚቀጥለው ያጠቃልለዋል ።

«. . . ለእኩል የጉልበት አስተዋጽኦ እኩል የሶ
ሻል መገልገያ ድርሻ ሲኖረው በርግጥ አንዱ ከሌ
ላው የበለጠ ይቀበላል ። በዚህም አንዱ ከሌላው
ኃብታም ይሆናል ። እነዚህንም ጉድለቶች ለማስ
ወገድ መብት እኩል ከመሆን ይልቅ እኩል እን
ዳይሆን ያስፈልጋል ።»

ስለዚህ የኮሚዩኒዝም የመጀመሪያ ደረጃ ፍትህንና
እኩልነትን ገና አያስገኝም ። በሀብት ልዩነቶች ፤ ልክ
ያልሆኑ ልዩነቶች ፣ ገና ይኖራሉ ። ነገር ግን የሰው በሰው
መበዝበዝ ፈፅሞ የማይቻል ይሆናል ። ምክንያቱም
የምርት መገልገያዎች፣ ፋብሪካዎች መሳሪያዎች ፣ መሬ
ትና የመሳሰሉት በግል ንብረትነት ስለማይያዙ ነው ።
የላሳልን የንዑስ ከበርቴ የተወናበደ ስለ «እኩልነት»
በአጠቃላይ አሳይቷል ። ስለ « ፍትህ » የሚሉ ሀረ
ጎች ከንቱ በማድረግ ማርክስ የኮሚዩኒስት ሀብረተ
ሰብን እድገት አቅጣጫ አሳይቷል ። ይህም በመጀመ
ሪያ የምርት መገልገያዎች በግለሰብ የመያዝን «በደል»
ብቻ ለመደምሰስ ይገደዳልና ። እንዲሁም በአንድ
ጊዜ ለአገልግሎት የሚውሉ እቃዎችን ማደል . . «በተ
ሰጠው የጉልበት ልክ መሰረት » እንጂ (እንደ የፍላ
ጎት ያልሆነውን) የሚያጠቃልሉ የቀሩትን በደሎች
ማጥፋት አይችልም ።

ስድ ኤኮኖሚስቶች ፣ የቡርዧ ምሁራንና «የኛ»
ቱጋን[29] ጭምር ሰዎች ሁሉ እኩል አለመሆናቸውን
ዘንግተው ይህንን እኩል ያለመሆን ለማጥፋት « ያል

ማሉ » በማለት ሶሻሊስቶችን አዘወትረው ይዘልፋሉ ። እንደምናየው እንዲህ ያለው ዘለፋ የሚያረጋግጠው የቡርዧ ርእዮተ አለም ቀያሾችን ድንቁርና ነው ።

ማርክስ በከፍተኛ ጥንቃቄ የማይቀረውን የሰውን እኩል ያለመሆን ከመገንዘቡም በላይ የምርት መገልገያዎች የህብረተሰቡ በሙሉ የጋራ ንብረት መሆናቸው ብቻ («ሶሻሊዝም» ተብሎ በሚጠራው) የማከፋፈልን ጉድለቶች እንደማያስወግድና ይህም እኩል ያለመሆን «የቡርዧ መብት» እቃዎች «በጉልበት አገልግሎት መጠን » እስከተከፋፈሉ ድረስ እንደሚቀጥል በዝርዝር ተረድቷል ። ከዚህም በማያያዝ ማርክስ የሚከተለውን ብሏል ፤

«ከካፒታሊስት ህብረተሰብ ገና ብቅ ባለው በኮሚዩኒስት ህብረተሰብ የመጀመሪያው ደረጃ እነዚህ ጉድለቶች የማይቀሩ ናቸው ። መብት ከአንድ ህብረተሰብ የኤኮኖሚ መዋቅር በላይ በፍፁም ሊሆን አይችልም ። የባህል እድገቱም ከዚህ ጋር የተዛመደ ነው ።»

ስለዚህ በኮሚዩኒስት ህብረተሰብ የመጀመሪያ ደረጃ (ብዙውን ጊዜ ሶሻሊዝም ይባላል) የ« ቡርዧ መብት» ከስረመሰረቱ አልተወገደም ፣ በከፊል ብቻ ፣ እስከዛሬ በተደረሰበት የኤኮኖሚ አብዮት ደረጃ መጠን ማለት ከምርት መገልገያዎች አንፃር እንጂ ። « የቡርዧው መብት » የግለሰቦች የግል ሀብት መሆናቸውን ያውቃል ። ሶሻሊዝም ግን ወደ ጋራ ንብረትነት ይለውጣቸዋል ። እስከዚህ ድረስ ብቻ «የቡርዧ መብት» ይጠፋል ።



ሌላው ክፍሉ እስካለ ድረስ ግን የቡርዧው መብት መኖሩን ይቀጥላል ። እቃዎችንም ተግባርንም በህብረተሰቡ አባሎች መካከል በማከፋፈል አስተካካይ በመሆን (ወሳኝ ምክንያት) ይቀጥላል ። « የማይሰራ አይብላ » የሚለው የሶሻሊዝም መርህ በግብር ላይ ውሏል ። « ለእኩል ስራ እኩል ዋጋ » የሚለውም ሌላው የሶሻሊዝም መርህ በግብር ላይ ውሏል ። ነገር ግን ይህ ገና ኮሚዩኒዝም አይደለም ፤ እኩል ያልሆኑ ግለሰቦች ላበረከቱት እኩል ላልሆነ (በርግጥም እኩል ላልሆነ) ጉልበት ፣ እኩል እቃዎችን የሚሰጠው የ« ቡርዧ መብት » ገና አልተደመሰሰም ።

ይህ « ጉድለት » ነው ይላል ማርክስ ፣ ነገር ግን በመጀመሪያው የኮሚኒዩኒዝም ደረጃ ሊወገድ አይችልም ።

ተምኔታዊነት ውስጥ ካልገባን በቀር ካፒታሊዝም እንደተወገደ ሰዎች በአንድ ጊዜ ያለ አንዳች የመብት መለኪያ ለህብረተሰብ መስራት ይጀምራሉ አንልም ። በርግጥም የካፒታሊዝም መደምሰስ ለእንደዚህ ያለ ለውጥ የኤኮኖሚ መሰረቶችን ከመቅፅበት ሊፈጥር አይችልም ።

ከ« ቡርዧ መብት » በስተቀር ሌላ መለኪያ የለም ። ይህ እስከሆነ ድረስ የምርት መገልገያዎች የህብረተሰቡ የጋራ ሀብት መሆናቸውን እየጠበቀ የስራ እኩልነትንና የእቃዎች በእኩልነት መከፋፈልን የሚያስከብር መንግስት መኖር አስፈላጊ ነው ።

መንግስት የሚመነምነው ካፒታሊስቶችና መደቦች ሲጠፉ ብሎም የሚጨቆን መደብ ሲጠፋ ነው ።

እኩል ያለመሆንን የሚንከባከበው የ « ቡርዧ መብት » ገና መከበር ስላለበት መንግስት ገና ጨርሶ

አልመነመነም ። መንግስት ጨርሶ እንዲመነምን ፍፁም የሆነ ኮሚዩኒዝም አስፈላጊ ነው ።

## 4. የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ከፍተኛ ደረጃ

ማርክስ በመቀጠል ፤

«በኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ከፍተኛ ደረጃ ፣ ግለሰብ ስራ መከፋፈል በሚገባ ከተንበረከከ ተገዥ ከሆነ በኋላ ፣ በአእምሮና በጉልበት ስራ መካከል ያለው ልዩነት ፈፅሞ ከጠፋ በኋላ ፣ ስራ የመኖር ምክንያት ብቻ ሳይሆን የመኖር ተቀዳሚ ፍላጐት ከሆነ በኋላ ፣ የምርት ሃይሎችም የግለሰቡን እድገት በየመስመሩ አሳድገውት የህብረት ሃብት ምንጭ በብዛት ሲፈስ ያኔ ብቻ ነው የቡርዧ መብት ጠባብ አድማስ ጨርሶ የሚሰረዘውና ህብረተሰብም «ከእያንዳንዱ እንደየችሎታው ለእያንዳንዱ እንደየፍላጐቶቹ » የሚለውን መርህ በአርማው ላይ የሚቀርፀው ! ።»

ኤንግልስ « ነፃነት » ና « መንግስት » የተሰኙትን ቃላት በየዋህነት በአንድነት ማጣመር የቀለደበትን አስተያየት ትክክለኛው መሆኑን በሙሉ ልብ የምናደንቀው ። አሁን ብቻ ነው መንግስት እስካለ ድረስ ነፃነት የለም ። ነፃነት በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ መንግስት አይኖርም ።

መንግስት ጨርሶ የሚመነምንበት የኢኮኖሚ መሰረት የኮሚዩኒዝም እድገት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ስለሚሆን በአእምሮና በጉልበት ስራ መካከል ያለው ቅራኔ ይጠፋል ። ከዚህም ተያይዞ ዘመናዊው የማህበራዊ አቋም አለመመጣጠን ምንጭ ይጠፋል ። ይህም ምንጭ የምርት መገልገያዎችን ወደ ህዝብ በማዞር ብቻ ፣ ካፒታሊስቶችን በመውረስ ብቻ በፍጥነት



ሊጠፋ አይችልም ። ይህ መወረስ የምርት ሃይሎችን ከፍተኛ ዕድገት እንዲያደርጉ የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ። ካፒታሊዝም አሁንም ቢሆን ለማመን በሚያቅት ሁኔታ ይህን ዕድገትን ምን ያህል እንዳዘገየው በምናይበት ጊዜ ፣ አሁን በተደረሰበት ጥበብ ደረጃ ምን ያህል መሻሻልን ማግኘት እንደሚቻል በምናይበት ጊዜ ፣ የካፒታሊስቶች መወረስ በርግጥ ለሰው ልጅ የምርት ሃይሎች ከፍተኛ እድገት እንደሚያስገኝ በሙሉ ልብ ለመናገር እንችላለን ። ነገር ግን ይህ እድገት በምን ያህል ፍጥነት እንደሚቀጥል ፣ የሥራ መከፋፈልን መቼ እንደሚያጠፋ ፣ በምን ያህል ፍጥነት በአእምሮ በጉልበት ስራ መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚያጠፋና ስራን ወደ « ህይወት አይነተኛ አስፈላጊነት » የሚለውጠው መቼ እንደሆነ አናውቅም ፣ ልናውቅም አንችልም ።

ስለዚህ ነው ስለማይቀረው የመንግስት መመንመን ብቻ ለመናገር የምንችለው ይህ ሂደት ጊዜ የሚፈጅ መሆኑን በመጠቆምና ከኮሚዩኒዝም ከፍተኛ ደረጃ የእድገት ፍጥነት ጋር የተዛመደ መሆኑን በማውሳት የሚያስፈልገውን የጊዜ ገደብ ጥያቄ ወይም የመመንመኑን ተጨባጭ ጉዳይ ችላ እንለዋለን ። ይህም የሆነበት ምክንያት እነኝህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ተጨባጭ ነገር ባለመኖሩ ነው ።

መንግስት ጨርሶ ሊመነምን የሚችለው ህብረተሰብ « ከእያንዳንዱ እንደየችሎታው ለእያንዳንዱ እንደየፍላጐቱ » የሚለው መርህ ስራ ላይ ሲያውል ነው ፤ ይህም ማለት ሰዎች የማህበራዊ ኑሮን መሰረታዊ ህጐች ማክበር በሚገባ ሲለምዱና ጉልበታቸውም ከፍተኛ ምርት የሚያገኝ ሆኖ በፈቃደኝነት እንደየችሎታቸው

ሲሰሩ ነው ። ያኔ አንደኛው ከሌላው ግማሽ ሰአት ይበልጥ አለ መስራቱንና አንደኛው ከሌላ ያነሰ አለ መከፈሉን ያለርህራሄ እንዳይሻይሎክ እንዲቆጣጠር የሚያደርገውን በጠባብ አድማስ የተወሰነውን የቡርዧውን መብት መሻገር ይቻላል ። በዚያን ጊዜ ህብረተሰብ እያንዳንዱ ነፃ ሆኖ « እንደ የፍላጎቱ » ይወስዳል ።

በቡርዧም አስተሳሰብ እንዲህ ያለው ስርአተ ማህበር « ፍፁም ተምኔታዊ » ነው ይባላል ። እያንዳንዱ ሰው በሚሰጠው የስራ አገልግሎት ላይ ቁጥጥር ሳይደረግበት የፈለገውን መጠን ፍራ ፍሬ ፣ መኪናዎች ፒያኖዎች ወዘተ ከህብረተሰቡ መቀበል እንደሚችል ተስፋ ይሰጡታል ብለው ቡርዧዎች በሶሺያሊስቶች ላይ ያፌዛሉ ። አሁንም ቢሆን ብዙሃኑ የቡርዧ « ምሁራን » በዚህ መልክ በማፌዝ ድንቁርናቸውንና የካፒታሊዝም ምንደኛ ተሟጋቾች መሆናቸውን አሳይተዋል ።

በርግጥም ድንቁርናና ነው ምክንያቱም የኮሚዩኒዝም ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ይመጣል የሚል « ተስፋ መስጠት» በማንም ሶሻሊስት አእምሮ ውስጥ አልገባም ። ይሁንእንጂ ታላላቅ ሶሻሊስቶች ከፍተኛው የኮሚዩኒስት የእድገት ደረጃ ወደፊት መምጣት ሲያዩ ያሁኑን የሥራ ውጤት ፣ ያሁኑን የተለመዱ ሰዎች ድርጊት በፓምያሎብስከ ታሪኮች ውስጥ እንደሚገኙት የሃይማኖት ተማሪዎች የተከማቸ የህዝብ ሀብት « ለቀልድ ያህል » እያሉ የሚያበላሹና የማይቻለውንም የሚጠይቁ እንዳሉ በመቀበል አይደለም ።

የኮሚዩኒዝም « ከፍተኛ » ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ህብረተሰቡና መንግስቱ ለስራና ለክፍያ መጠን ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ሶሻሊስቶች ይጠይቃሉ ። ነገር ግን



ይህ ቁጥጥር በካፒታሊስቶች መወረስ ፣ ወዛደሮች በካፒታሊስቶች ላይ በሚመሰርቱት ቁጥጥር መጀመር አለበት ። ቁጥጥሩም መካሄድ ያለበት በቡርዧ መንግስት ቢሮክራሲ ሳይሆን በታጠቁ ወዛደሮች መንግስት ነው ።

የቡርዧ ርእዮተ አለም ቀያሾች ምንደኞችና የካፒታሊዝም ተከላካዮች እና ተከታዮቻቸው (እነ ክቡራን ፀረቴሊት ፔርኖብ ወዘተ) የአሁኑን ጊዜ እንገብጋቢ የፖለቲካ ጥያቄዎች ወደፊት ባለው ጉዳይ ክርክርና ውይይት ይተካሉ ። እነዚህም የጊዜው ጥያቄዎች የካፒታሊስቶች መወረስ ፣ ሁሉንም ዜጎች ወደ አንድ ትልቅ « ማህበር » ሰራተኝነትና ተቀጣሪነት መለወጥ ፣ የዚህም ማህበር ስራ በጠቅላላው እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንግስት ስር ፣ የሠራተኛ ተመራጮችና የወታደር ወኪሎች መንግስት ስር መሆኑ ናቸው ።

በርግጥ አንድ የተማረ የዩኒቬርስቲ መምህር እርሱንም ተከትሎ ጠባብ አስተሳብ ያለው ሰው ይሄኛውንም እነሴሬቴልስና ቼርኖቭ በመከተል ስለማይሆን ተምኔት ሲናገሩ ፣ ስለ ቦልሼቪኮች የማይሆን የቅስቀሳ ተስፋ ሲተቹ ሶሻሊዝምን «ለማስተዋወቅ» አለመቻል ሲቀባጥሩ በአእምሮዋቸው ያለው የኮሚዩኒዝም ከፍተኛ ደረጃነው። ይህ ይሆናል ብሎ ደግሞ ማንም ተስፋ የሰጠ እንዲያውም «ለማስተዋወቅ» ያሰበም የለም ። ምክንያቱም በአጠቃላይ በግብር «ለማስተዋወቅ» የሚችል አይደለም ።

ይህ ደግሞ ኤንግልስ ከላይ በጠቀስነው ማስረጃ « ሶሻል ዲሞክራት » የሚለው ስያሜ ስህተት ነው ብሎ ወደጠቀሰው በሶሻሊዝምና በኮሚዩኒዝም መካከል

ወዳለው ሳይንሳዊ ልዩነት ይመራናል ። በፖለቲካ ረገድ በመጀመሪያው ወይም በዝቅተኛውና በከፍተኛው የኮሚዩኒዝም ደረጃ መካከል ያለው ልዩነት ምናልባት ሰፊ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን በካፒታሊዝም ስር ሆኖ ልዩነቶቹን ስለመገንዘብ መናገር አስቂኝ ነው ። ምናልባት ግለሰብ አናርኪስቶቹ በተቀዳሚ አስፈላጊ ያደርጉት ይሆናል ።

(ክሮፓትኪን ግሬ ብስ ኰርኔሊስና ሌሎች በአናር ኪዝም «ኲከቦች» በፕሌካኖባይቶች ወደ ሶሻል ትምክህተኞች ወይም ህሊናቸውንና ክብራቸውን ከጠበቁት ጥቂት አናርኪስቶች አንዱ ፡ ጊ ፤ እንዳስቀመጠው ወደ ሶሻል ትምክህተኝነት መለወጥ ምንም ያልተማሩ ሰዎች ከአናርኪስቶች መሀል ካሉ) ። በሶሻሊዝምና በኮሚዩኒዝም መካከል ያለው ሳይንሳዊ ልዩነት ግን ግልፅ ነው ። ግን ብዙውን ጊዜ ሶሻሊዝም የሚባለው ማርክስ የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ የ « መጀመሪያ » ወይም ዝቅተኛ ደረጃ የሚለው ነው ። የምርት መገልገያዎች የጋራ እስከሆኑ ድረስ «ኰሚዩኒዝም» የሚለው ቃል ተገቢ ነው ፤ ሆኖም ይህ ሙሉ ኮሚዩኒዝም አለመሆኑን መዘንጋት የለብንም ። የማርክስ አገላለፅ አብይነቱ የእድገት ቲዎሪ በሆነው በማቴሪያሊስት ዲያሌክቲክስ አስተሳሰብ መሰረት ኮሚዩኒዝምን ከካፒታሊዝም እንደ አደገ ነገር መመልከቱ ነው ። መፅሀፋዊ በሆነ ዘዴ ለቃላት የፈጠራ ትርጓሜዎችን ከመስጠትና (ሶሻሊዝም ምንድነው ? ኮሚዩኒዝም ምንድነው ?) ፍሬ ቢስ ክርክር ከማቅረብ ይልቅ ፡ ማርክስ ለኮሚዩኒዝም መብሰል ምልክት የሚሆኑትን የኤኮኖሚ ደረጃዎች ትንተና ይሰጣል ።



በመጀመሪያ ደረጃው ኮሚዩኒዝም በኤኮኖሚ የበሰለ ካለመሆኑም በላይ ከወግ ወይም ከካፒታሊዝም ንክኪ ፍፁም ነፃ ሊሆን አይችልም ። ስለዚህ ኮሚዩኒዝም በመጀመሪያ ደረጃው « የቡርዧ መብትን ጠባብ አድማስ» የሚያቆይ መሆኑ የሚያስደንቅ ክስተት ነው ። እርግጥ የግልጋሎት እቃዎችን ከማከፋፈል አንፃር ስንመለከተው የቡርዧ መብት የቡርዧን መንግስት መኖር ይጠቁማል ። ምክንያቱም መብት ያለ መብት ማስከበሪያ መሳሪያ ከንቱ ነው ።

ከዚህ የሚከተለው እንግዲህ በኮሚዩኒዝም የቡርዧ መብት ብቻ ሳይሆን የቡርዧ መንግስት ጭምር ከቡርዧው በስተቀር — ለጊዜው መቆየቱ ነው ።

ይህም ሲሰሙት ግራ የሚያጋባ ሊመስል ይችላል ። ወይም ብዙውን ጊዜ የማርክሲዝምን በጣም ልዩ የሆነ ታላቅ ይዘት ለማጥናት ምንም ጥረት የማያደርጉ ሰዎች እንደሚያደርጉት እንደዲያሌክቲክስ እንቆቅልሽ ሊገመት ይችላል ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በተፈጥሮም ሆነ በህብረተሰብ ውስጥ የቀድሞዎቹ ቅሪቶች ዘወትር በየደረጃው ይገጥሙናል ። ማርክስ « የቡርዧ » መብትን በራሱ ፈቃዱ ኮሚዩኒዝም ውስጥ መሸንቀሩ ሳይሆን ከካፒታሊዝም ማህፀን ውስጥ የሚወጣ ህብረተሰብ በኤኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ የማይዘለው ሁኔታ መሆኑን ለማሳየት ነው ።

ዲሞክራሲ ወዛደሩ ከካፒታሊዝም ጋር ለነፃነቱ የሚያደርገው ትግል በጣም አስፈላጊ ነው ። ይሁን እንጂ ዲሞክራሲ ፍፁም የማይጣስ ወሰን ሳይሆን ከፊው

ዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም ፡ ወደ ኮሚኒዝም መሸጋ
ገሪያ ከሆኑት ምእራፎች አንዱ ነው ።

ዲሞክራሲ ማለት እኩልነት ነው ። ወዛደሩ ለእኩ
ልነት የሚያደርገው ትግልና እኩልነትም እንደ
መፈክር ከፍተኛ መሆኑ ግልፅ ሊሆንልን የሚ
ችለው እኩልነት ማለት የመደቦች መጥፋት መሆኑን
በትክክል ስንረዳ ነው ። ይሁን እንጂ ዲሞክራሲ
ህጋዊ እኩልነት ብቻ ማለት ነው ። ለሁሉም የህብ
ረተሰብ አባላት በምርት መገልገያ ባለቤትነት በኩል
እኩልነት እንደተገኘ ፤ ማለትም የወዝ እኩልነትና
የደመወዝ እኩልነት ፡ የሰውን ልጅ ከህጋዊ እኩ
ልነት ወደ እውነተኛ እኩልነት የማሸጋገር ጥያቄ
ይገጥመዋል ። ይህም እርግጠኛ እኩልነት ማለትም
«ከእያንዳንዱ እንደየችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላ
ጐቱ » የሚለውን ደንብ ማስፈፀም ነው ። የሰው ልጅ
በምን ደረጃ በምን ተግባራዊ እርምጃዎች ወደዚህ ከፍ
ተኛ አላማ ማምራት እንዳለበት አናውቅም ፡ ልናውቅም
አንችልም ። ነገር ግን ተራው የቡርዧ አስተሳሰብ
ሶሻሊዝምን ህይወትየለሽ ፡ ግኡዝና ለዘለአለም የተ
ገተረ አድርጐ ሲያቀርበው ምን ያህል ያጭበርባሪ
ሀሳብ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ። ይሁንእንጂ
እውነታው ፈጣን ፡ ሀቀኛ ፡ በርግጥ የብዙሃንን የወደ
ፊት እንቅስቃሴ ፡ ማለትም በመጀመሪያ የአብዛኞቹን
በኋላም የመላውን ህዝብ የጋራና የግል ህይወት የሚ
ያጠቃልለው በሶሻሊዝም ብቻ ነው ።

ዲሞክራሲ ከመንግስት ብዙ መልኮች አንደኛው
ነው ። በዚህም መሰረት እንደማንኛውም መንግስት
በአንድ በኩል በሰዎች ላይ ጭቆናን የሚያካሂደው የተ
ደራጀ ኃይልን ሲወክል ፡ በሌላ በኩል ደግሞ የዜጐቹን



ህጋዊ እኩልነት መገንዘብን ፡ የመንግስትን መዋ
ቅር መወሰንና በማስተዳደሩም ረገድ ሁሉም እኩል
መብት እንዳለው ያመለክታል ። ይህ ደግሞ ከተወሰነ
የዲሞክራሲ የእድገት ደረጃ ሲደርስ በመጀመሪያ በካ
ፒታሊዝም ላይ አብዮታዊ ትግል የሚያካሄደውን የወ
ዛደሩን መደብ አንድነት ያጠነክረዋል ። ይህም በመ
ሆኑ ቡርዧውን ለመሰባበር ፡ ለማድቀቅና ጨርሶም
ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ያበቃዋል ። የሪፐብሊካዊ ቡርዧ
መንግስትን መሳሪያ ቋሚ ጦር ሠራዊት ፡ ፖሊስና
ቢሮክራሲውን ጭምር አጥፍቶ በይበልጥ ዲሞክራቲካዊ
በሆነ መንግስት ተክቶ በታጠቁ ብዙሃን ወዛደሮች
መልክ መላው ህዝብ ወደ ሚሳተፍበት ህዝባዊ
ጦር ያድጋል ።

እዚህ ላይ « መጠን ወደ ዓይነት » ይለወጣል ። እንዲህ
ያለው ዲሞክራሲም የቡርዧን ህብረተሰብ ወሰን ጥሶ
የሶሻሊስትን ህብረተሰብ መገንባት መነሻ ይሆናል ።
በርግጥ ሁሉም በመንግስቱ አስተዳደር ከተሳተፉ ካፒ
ታሊዝም መሰረቱን ይዞ ሊቆይ አይችልም ። የካፒታ
ሊዝም መዳበር ደግሞ « ሁሉም » በመንግስቱ አስተ
ዳደር ለመሳተፍ የሚያስችሉ መሰረቶች የሚጥል ነው።

ከነዚህም መሰረቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።
በብዙዎቹ ከፍተኛ የካፒታሊስት አገሮች የሚታየው
ሁሉም ማንበብና መፃፍ መቻሉ ፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ
ሰራተኞች በጣም ትልቅና በተወሳሰቡ እንደ ፖስታ
አገልግሎት ፡ የባቡር አገልግሎት ፡ ታላላቅ ፋብሪካዎች
ሰፋፊ ንግድ ፡ ባንኮች ወዘተ ውስጥ በአንድነት እየሠሩ
« ሙያ መማራቸውና ሥነ ስርአት መልመዳቸውን »
ያጠቃልላል ።

ይህንን የኤኮኖሚ መሠረቶች መነሻ በማድረግ ካፒ
ታሊስቶችና ቢሮክራቶች ከተፈነቀሉ በኋላ በእስቺ
ኳይ ፣ በአንድ ቀን ማምረትንና ምርት ማከፋፈልን
በመቆጣጠር ፤ ጉልበትንና ውጤቶቹን መዝግቦ በመያዝ
የታጠቁ ወዛደሮች ፣ መላው የታጠቁ ህዝብ በብልጫ
ይሰራል ። (የሂሳብ መዝገብ አያያዙና የቁጥጥሩ ጉዳይ
በሳይንሳዊ ትምህርት የታነፁ መሐንዲሶች ፣ በእርሻ
ሙያ የሰለጠኑና የመሳሰሉት ባለሙያዎች ከሚሠሩት
ጋር ሊደናገር አይገባም ። እነዚህ አዋቂዎች በዛሬው
ጊዜ ለካፒታሊስቶች ፍላጐት ታዛዥ በመሆን ይሰ
ራሉ ። ነገ ደግሞ የታጠቁ ወዛደሮቹን ፍላጐት በመታ
ዘዝ ከዚህ በተሻለ ይሰራሉ ።

የሂሳብ መዝገብ አያያዝና ቁጥጥር የመጀመሪያ
ደረጃ የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ያለ እንቅፋትና በት
ክክል እንዲሰራ «ለማዘጋጀት» ዋነኛ አስፈላጊ ነገር
ነው ። በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ዜጐች ሁሉ የታጠቁ
ወዛደሮችን ወደሚያጠልለው መንግስት ተቀጣሪነት
ተለውጠዋል ። ዜጐች ሁሉ ለአንድ አገር አቀፍ የመ
ንግስት «ማህበር» ተቀጣሪዎችና ሰራተኞች ይሆናሉ ።
ከነርሱም የሚጠበቀው እኩል እንዲሰሩ ፣ ተገቢ የስራ
ድርሻቸውን እንዲያከናውኑና እኩል እንዲከፈሉ
ነው ። ለዚህ ተግባር የሚያስፈልገው የሂሳብ መዝገብ
አያያዝና ቁጥጥር በካፒታሊዝም ስር እት ከመጠን
በላይ ስለተቃለለ መቆጣጠሩንና መመዝገቡን ፣
የአራት መደብና ተገቢውን ደረሰኞች ቆርጦ የመስ
ጠት ችሎታ ያለው ማንም ማንበብና መፃፍ የሚችል
ሰው ያከናውነዋል ። የመንግስት ተግባራት ወዛደ
ሮች ራሳቸው ወደሚያከናውኑት የሂሳብ መዝገብ



አያያዝና ቁጥጥር ዝቅ ቢደረግ መንግስት « የፖለ
ቲካ መንግስት » መሆኑ ይቋረጣል ። « ህዝባዊ
ተግባራትም የፖለቲካ ጠባዩን አጥቶ ወደ ቀላል
አስተዳደራዊ ተግባሮች ይለወጣል ። (ምእራፍ 4, 2
ኤንግልስ « ከአናርኪስቶች ጋር ያደረገው ክርክር »)
አብዛኛው ሕዝብ በገዛ ራሱ በያለበት እንዲህ ያለውን
መዛግብት ሲይዝና በካፒታሊስቶችና (አሁን ወደ ተቀጣ
ሪነት ተለውጠዋል) የካፒታሊስት ጠባይን ባቆዩ ምሁ
ራን ላይ ቁጥጥር ሲያደርጉ ፣ ይህ ቁጥጥር በርግጥ ሁለን
ታዊ አጠቃላይና የታወቀ ይሆናል ። ከዚህም ለማም
ለጥ አይቻልም ፤ «የሚኬድበትም ስፍራ» አይኖርም ።

በስራ እኩልነትና በደመወዝ እኩልነት መላው
ህብረተሰብ አንድ ቢሮ አንድ ፋብሪካ ይሆናል ።

ነገር ግን ወዛደሩ ካፒታሊስቱን ካሸነፈ በኋላና በዝባ
ዦችንም ከፈነቀለ በኋላ « ወደ መላው ህብረተሰብ የሚ
ስፋፋው ይህ'' የፋብሪካ ስነ ስርአት የመጨረሻው
ምኞታችንና ግባችን አይደለም ። ነገር ግን ለተጨማሪ
መሻሻልና ህብረተሰቡን አስከፊና ጨካኝ ከሆነው የካ
ፒታሊስት ብዝበዛ ለማንፃት ለሚደረገው ሂደት አስ
ፈላጊ እርምጃ ነው ።

መላው የህብረተሰቡ አባላት ፣ ወይም ብዙሀኑ ፣
እራሳቸው መንግስቱን ማስተዳደር ሲማሩ ፣ የዚህንም
ተግባር በእጃቸው ሲያስገቡ ፣ እጅግ በጣም አነስተኛ
በሆኑት ካፒታሊስቶችና የካፒታሊስቱን ጠባይ ለማቆ
የት በሚሹ መኳንንቶችና በካፒታሊዝም በተበላሹ
ወዛደሮች ላይ ቁጥጥር « ሲያካሄዱ » ከዚህ ጊዜ በኋላ
የማንኛውም አይነት አገዛዝ አስፈላጊነት መጥፋት ይጀ
ምራል ። ዲሞክራሲ እየተሟላ በሄደ ቁጥር አስፈላጊ

ወደ አለመሆን እየተቃረበ ይሄዳል ። የታጠቁ ወዛደሮችን የሚይዘው «መንግስት» በይበልጥ ዲሞክራቲካዊ ሲሆን መንግስቱም ቃሉ እንደሚያመለክተው መንግስት አይደለም ። ከዚህ በኋላ የመንግስቱ እያንዳንዱ ቅርፅ በአስቸካይ መመንመን ይጀምራል ። ሁሉም ምርትን ማስተዳደር ሲማሩና ራሳቸውን ችለው ምርትን ሲያስተዳድሩ ፡ ራሳቸውን ችለው የሂሳብ መዛግብትን ሲይዙና ስራ ፈቶችን ፡ መኳንንቶችን ፡ አጭበርባሪዎችንና «የካፒታሊስት ልምድ ጠባቂዎችን» ሲቆጣጠሩ ከዚህ ህዝባዊ የሂሳብ መዛግብት አያያዝና ቁጥጥር ማምለጡ ያልተለመደ ቢሆንም ጨርሶ አስቸጋሪ ይሆናል ። ምናልባትም ከዚሁ ጋር ፈጣንና ሃይለኛ ቅጣት ይከተል ይሆናል ። (የታጠቁ ወዛደሮችና ተግባራዊ ሰዎች እንጂ በስሜት የሚመሩ ምሁራን ባለመሆናቸው ማንም ቅንጣት ያህል እንዲያሞኛቸው አይሹም )። በዚህም ጊዜ ቀላልና መሰረታዊ የሆኑትን የማኅበራዊ ደንቦች የማክበር አስፈላጊነት በአስቸኳይ ልማድ ይሆናል ።

በዚያን ጊዜ ከኮሚዩኒስት ህብረተሰብ የመጀመሪያ ደረጃ ወደ ከፍተኛው ደረጃ የመሸጋገሪያው በር ወለል ብሎ ይከፈታል ፡ ከዚህም ጋር መንግስት ጨርሶ ይመነምናል ።

* * *

## ምዕራፍ 6
## ማርክሲዝም በአድርባዮች ሲበረዝ

የመንግስት ከሶሻል አብዮት ጋር ፡ የሶሻል አብዮት ከመንግስት ጋር ያለው የግንኙነት ጥያቄ ፡ በአጠቃላይ እንደ የአብዮት ጥያቄ ፡ የሁለተኛው ኢንተርናሽናል (1889—1914) መሪ የቲዎሪ አዋቂዎችንና የህግ አዋቂዎችን (ፐብሊስቶችን) እምብዛም አላስጨነቃቸ



ውም ሆኖም በ1941 የሁለተኛውን ኢንተርናሽናል ወደ ውድቀቱ ያመራው የአድርባይነት ቀስበቀስ እድገት ሂደት ዋናው ባህሪ እነዚህ ሰዎች ጥያቄው በቀጥታ ለመሸሽ መሞከራቸው አለበለዚያም ሲያጋጥማቸው ያለመገንዘባቸው ሀቅ ነው ።

በጠቅላላው የወዛደሩ መደብ አብዮት ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት መሸሽ አድርባይነትን የጠቀመውና የኮተኮተው ሽሽት — የማርክሲዝም ማጣመምና ጭራሽ መበረዝን አስከተለ ።

የዚህን የሚያሳዝን ሂደት ጠባይ ለማሳየት ፡ ባጭሩም ቢሆን ፡ በጣም የታወቁትን የማርክሲዝም ቲዮሪቲሺያኖችን ፔሌካኖቭንና ካውትስኪን እንወስዳለን ።

### 1. የፔሌካኖቭ ክርክር ከስርአተ አልበኞች ጋር

ፔሌካኖቭ በስርአት አልባነትና በሶሻሊዝም ላይ ስላለው ግንኙነት ስርአተ አልባነትና ሶሻሊዝም በሚል ርእስ አንድ ልዩ መፅሄት ፃፈና በ1894 በጀርመንኛ ታተመ ።

ፔሌካኖቭ ይህንን ርእስ ሲገልፅ በጣም አጣዳፊ ፡ አንገብጋቢና በፖለቲካም በጣም አስፈላጊ የሆነውን ከስርአተ አልባነት ጋር ያለውን የትግል ጥያቄ በመጣስ ፡ ማለትም የአብዮቱ ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነትና በአጠቃላይ የመንግስቱን ጥያቄ ፈፅሞ ችላ በማለት ትቷል ። በዚህች ትንሽ መፅሄት ውስጥ ጉልተው የሚታዩት ሁለቱ ክፍሎች አንደኛው ታሪካዊና ስነፅሁፋዊ ሆኖ ፡ በስቲርነር ፡ በፕሩዶንና በሌሎች ሃሳቦች ታሪክ ላይ ጠቃሚ ነገሮችን ይዟል ። ሌላው ጠባብና በአርእስቱ ላይ አቅለቢስ ጥናት የያዘ ሆኖ ስርአት አልበኛን ከወንበዴ የማይለይ ነው ።

የልዩ ልዩ ጉዳዮች አርእስት በሚያስደንቅ ሁኔታ መደ
በላቅ በሩሲያ አብዮት ዋዜማና በአብዮቱ ዘመን የፔሌ
ካኖቭ መላ ድርጊት መለያ ባህሪ ነበር ። በተግባር ከ1905
እስከ 1917 ባሉት አመታት ውስጥ ፒሌካኖቭ በእር
ግጥ ከፊል መምህርና ከፊል አወናባጅ መሆኑን አሳ
ይቷል ። በፖለቲካም ቡርዧው ሲነቃ ከኋላ ተጐትቷል።

ማርክስና ኤንግልስ ከስርአተ አልበኞች ጋር ባደ
ረጉት ክርክር ፥ አብዮቱ ከመንግስት ጋር ስላለው ግን
ኙነት ያላቸውን አስተያየቶች እንዴት በላቀ ጥን
ቃቄ እንደገለፁት አይተናል ። በ1891 በማርክስ
የጐታ ፕሮግራም ሄስ መቅድም ላይ ኤንግልስ እንዲህ
ብሎ ፅፏል «እኛ» ይኸውም ኤንግልስና ማርክስ «በዚ
ያን ጊዜ ፥ የሄይጉ ኰንግረስ (አንደኛው) ኢንተርናሽ
ናል[30] ጉባኤካለፈ ሁለት አመት እንኳን ሳይሆን፥ከባኩ
ኒንና ከስርአተ አልበኞቹ ጋር እጅግ ከፍ ባለ ሃይለኛ
አመፃዊ ትግል ውስጥ ነበርን ። »

ስርአተ አልባኞቹ የፓሪሱ ኮሚዩንን እንደራሳቸው
« የግል » የእምነት መመሪያ ትምህርት (ዶክትሪን)
ማረጋገጫ በማድረግ ለመጠቀም ሞክረዋል ፤ እናም
የፓሪስ ኮሚዩንን ትምህርቶችና የማርክስን የእነዚህን
ትምህርቶች ትንተና ለመረዳት ፍፁም ተሰናችዋል ።
ስርአት አልባነት ለማንኛውም ተጨባጭ የፖለቲካ
ችግሮች ተቀራረቢ እውነተኛ መፍትሄ እንኳን ለመስ
ጠት ተስኖታል ፥ ማለትም አሮጌው የመንግስት መሳሪያ
መሰባበር አለበትን ? እናም በለውጡ ምን መተካት
አለበት ?

የመንግስትን ጥያቄ በመሸሽ ፥ እንዲሁም ከኮሚ
ዩን በፊትና በኋላ የማርክሲዝምን አጠቃላይ እድገት



መገንዘብ እየተሳነ «ስለስርአት አልባነትና ሶሻሊዝም»
መናገር ማለት ከማይሻሹት አድርባይነት ውስጥ መን
ሸራተት ነው ። አድርባይነት ከሁሉም በላይ የሚያስፈ
ልገው እነዚህ ሁለት የተነሱትን ጥያቄዎች በፍፁም
አለማንሳት ነው ። ይህ ደግሞ እራሱ ለአድር ባይነት
አንድ ድል ነው ።

## 2. የካውትስኪ ክርክር ከአድርባዮች ጋር

ካለምንም ጥርጥር ቁጥራቸው እጅግ የበዛ የካውት
ስኪ ፅሁፎች ከማንኛውም ሌላ ቋንቋ ይበልጥ በሩሲያ
ቋንቋ ተተርጉመዋል ። አንዳንድ የጀርመን ሶሻል ዲሞ
ክራቶች በቀልድ መልክ ካውትስኪ ከጀርመን ውስጥ
ይበልጥ በሩሲያ ይነበባል የሚሉት ካለ ምክንያት አይደ
ለም ። (በቅንፍ ለመናገር ያህል ፥ ይህ ቀልድ መጀመ
ሪያ ቀልደኞች ከጠረጠሩት በላይ ጥልቅ የሆነ ታሪካዊ
አቢይነት አለው ። በ1905 የሩሲያ ወዛደሮች ከምን
ጊዜም በላቀና ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን በአለም
ውስጥ ካሉት እጅግ በጣም ጥሩ የሶሻል ዲሞክራቲክ
ፅሁፎችን በመሻትና የእነዚህ ፅሁፎችን ትርጉሞችና
እትሞች በሌላ አገር ታይቶ በማያውቅ መጠን ሲገኙ ፥
የተራመደውን የጐረቤት አገር አያሌ ልምድ በጣም
በተፋጠነ እርምጃ በወጣቱ የወዛደር ንቅናቄያችን አፈር
ላይ ለመትከል ችለዋል ። )

ካውትስኪ በተለይ በእኛ አገር የታወቀው ማርክ
ሲዝምን በማሳወቅ ብቻ ሳይሆን ከአድርባዮችና ከቁ
ንጮአቸው ከበርንስታይን ጋር ባደረገው ክርክር ነው።
እራሳችንን ወደ ምርምር ተግባር ብናስማራ ፥ ካውትስኪ
እንዴት ሊታመን በማይችል አሳፋሪ የውዥንብር አዘ
ቅት ውስጥ እንደተዘፈቀና በ1914—15 በነበረው ከፍተኛ

ቀውጢ ጊዜ ሶሻል ትምክህተኝነትን እንደደገፈ ሊታ
ለፍ የማይገባውና አንድ ያልታወቀ ሀቅ ነው ። ይህም
ሀቅ የሚከተለው ነው ። በፈረንሳይ (ሚላራንድና
ዦውሬ) እና በጀርመን( በርንስታይን) በጣም ከታወ
ቁት የአድርባይነት ወኪሎች ጋር ተቃውሞውን ለመ
ግለፅ ብቅ ከማለቱም አስቀድሞ በነበረው አጭር ጊዜ
ውስጥ ካውትስኪ በጣም ከግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚችል
ወላዋይነት አሳይቶ ነበር ። በ1901—02 በስቱትጋርት
ይታተም የነበረውንና ለአብዮታዊ የወዛደር መደብ
ሃሳቦች የሚታገለው የማርክሲስት መፅሄት ዘርያ[31] ፤
ካውትስኪ ያኔ እርሱ በ1900[32] በፓሪስ ኢንተርናሽናል
ሶሻሊስት ጉባኤ ያቀረበውን ሃሳብ ግማሽ ልብ አታ
ላይ ውሳኔ ፥ ከአድር ባዮች ጋር የሚያስታርቅና « ልፍ
ስፍስ» ነው ለማለት ከካውትስኪ ጋር ክርክር እንዲገባ
ተገዶ ነበር ። የበርንስታይንን ተቃውሞ ከማስፋፋቱ
በፊት ካውትስኪ ያሳየውን መወላወል በጀርመን
የታተሙት ደብዳቤዎቹ ይገልፃሉ ።

ሆኖም ታላቅ ቁምነገር ከአድርባዮች ጋር ያደረገው
ክርክር ጥያቄውን የመሰረተበትና የተመለከተበት
አኳኋን ፥ ካውትስኪ ወደኋላ ማርክሲዝምን የመክዳቱን
ታሪክ ስንመረምር ፥ በመንግስት ጥያቄ ላይ ስርአት
ባለው ሁኔታ ወደ አድርባይነት መሳቡን ለመመልከት
መቻላችን ሀቅ ነው ።

እስቲ በመጀመሪያ ከአድርባዮች ጋር ተቃውሞየገ
ጠመበትን የካውትስኪን የመጀመሪያ ታዋቂ ስራ ፤
በርንስታይንና የሶሻል ዲሞክራቲክ ፕሮግራም የሚ
ለው እንውሰድ ። ካውስትኪ በርንስታይን ልክ አለ
መሆኑን አንድ በአንድ በመውሰድ ይቃወማል ፥ ሆኖም
አንድ ልዩ ጠባይ ያለው ነገር እነሆ ።



በርንስታይን ፤ የሶሻሊዝም መንስኤ በሚለው መፅ
ሀፉ ውስጥ በሂሮስትራቲያን ዝና ማርክሲዝምን « ብላ
ንኩይዝም» በማለት ይወነጅላል ። (ከዚያን ጊዜ ወዲህ
በሩሲያ ውስጥ የአብዮታዊ ማርክሲዝም ተከታዮችን
ማለትም ቦልሼቪኮችን በሚቃረኑ በአድርባዮችና በሊበ
ራል ቡርዧ ሺህ ጊዜ የተደጋገመ ወንጀል ነው) ከዚህ
ጋር የተያያዘ በርንስታይን በተለይ የማርክስ በፈረንሳይ
የእርስ በርስ ጦርነት በሚለው መፅሀፉ ላይ በማተኮር
እንደምናየው በፍፁም አልተሳካለትም እንጂ ፥ በኮ
ሚዮኑ ትምህርቶች ላይ ያለውን የማርክስን አስተሳሰብ
ከፕሮዶን ጋር ለማመሳሰል ይሞክራል ። በርንስታይን
ማርክስ በ1872 በኮሚዩኒስት ማኔፌስቶ መቅድም መደ
ምደሚያ ላይ ባተኮረበት ይኸውም «የወዛደሩ መደብ
ያለውን መንግስታዊ አቋም በቀላሉ እንዳለ ተቀብሎ
በመጨበጥ ለራሱ ጥቅም ሊያውለው አይችልም ። »
ባለው ላይ የተለየ ግምት ይሰጠዋል ።

ይህ አባባል በርንስታይንን በጣም « ከማስደሰቱ »
የተነሳ በተዛባና በአድርባይነት ስሜት በመተርጎም
መፅሀፉ ውስጥ ከሶስት በማያንስ ጊዜ ደጋግሞታል ።

እንዳየነው ፥ ማርክስ የወዛደሩ መደብ የመንግስቱን
አቋም በሙሉ ማድቀቅ ፥ መሰባበር ፥ መበታተን (ፕስ
ሬንጎንግ—ማፈንዳት ፥ ኤንግልስ የተጠቀመበት
አገላለፅ) አለበት ነው ያለው ። ነገር ግን እንደ በርንስ
ታይን አባባል ማርክስ በእነዚህ ቃላት የወዛደሩ
መደብ ስልጣን ሲይዝ ከልክ ያለፈ አብዮታዊ ወኔ
እንዳይኖረው ያስጠነቅቀ ይመስላል ።
የማርክስን ሃሳብ ለማጣመም መሞከር ፥ ከዚህ የበ
ለጠ የከፋና አስቀያሚ መንገድ ሊኖር አይችልም ።

ታዲያ እንዴት ነው ፣ ካውትስኪ በርንስታይኒዝምን
ዝርዝር በሆነ መንገድ ተቃውሞውን የቀጠለው ?

ማርክሲዝም በአድርባይነት በጣም የመጣመሙን
ነጥብ ከመተንተን ተቆጥቧል ። እላይ የተጠቀሰውን
የወሰደው ኤንግልስ ለማርክስ የርስ በርስ ጦርነት መግ
ቢያ ከፃፈው ሆኖ እንደማርክስ አባባል የወዛደሩ መደብ
ያለውን መንግስታዊ አቋም በቀላሉ እንዳለ ተቀብሎ
ሊይዝ አይችልም ፣ ሆኖም በአጠቃላይ አነጋገር ፣
ሊይዝ ይችላል—የሚል ብቻ ነበር ። በርንስታይን ከእውነ
ተኛው የማርክስ አስተያየት ተቃራኒ ስለመሆኑ ፣ ማር
ክስ በ1852 ጀምሮ የወዛደሩ መደብ አብዮት ተግባር
የመንግስቱን አቋም መደምሰስ ነው ብሎ ስለመሰረተው
ጭብጥ እውነት ካውትስኪ አንድም ቃል አልተነፈ
ሰም ።

ውጤቱም በወዛደሩ አብዮት ተግባር ላይ በማርክሲ
ዝምና በአድርባይነት መካከል ያለውን አቢይ ልዩነት
በካውትስኪ መሸፋፈኑ ነበር !

« የወዛደሩን የበላይ ገዥነት ችግር መፍትሔ
ያለምንም ፍርሃት ለመጪው ጊዜ መተው እን
ችላለን ፤ » አለ ካውትስኪ ፤ በርንስታይንን
«በመቃወም» ሲፅፍ ። (ገፅ 172 የጀርመን እትም)

ይህ በርንሲታይንን በመቃወም የተደረገ የፅሁፍ ጦርነት
(ፖለሚክ) አይደለም ግን በይዘቱ ከእርሱ ጋር መስማማት
ለአድርባይነት መማረክ እንጂ ፣ ምክንያቱም አድ
ርባዮች በአሁን ጊዜ ለወዛደር መደብ አብዮት ተግባ
ሮች መሰረታዊ ጥያቄዎችን ሁሉ « ያለፍርሃት ለመ
ጪው ጊዜ ከመተው » የተሻለ ሌላ ምንም አይጠይ
ቁምና ።



ከ1852—1891 ለአርባ አመታት ፣ ማርክስና ኤን
ግልስ የወዛደሩን መደብ ያስተማሩት መንግስታዊ
አቋምን መሰባበር እንዳለበት ነበር ። ነገር ግን በ1899
ካውትስኪ የማርክሲዝም በአድርባዮች ፈፅሞ መከ
ዳት ሲያፋጥጠው ፣ በዚህ ነጥብ ላይ ይህን መሣሪያ
መደምሰስ ያስፈልጋል ወይ በሚለው ጥያቄ ፈንታ
ሊደመሰስ በሚችልበት ተጨባጭ ቅርፆች ጥያቄ በማ
ጭበርበር በመተካት ፣ ተጨባጭ ቅርፆች በቅድሚያ
ሊታወቁ አይችሉም . ! ! በሚለው «በማያከራክረው»
(ግን ባዶ) አወናባጅ እውነቱ ከለላ ስር ጥገኝነት ፈለገ ።

ማርክስና ካወትስኪ የወዛደሩን መደብ ለአብዮት
በማዘጋጀት የወዛደሩ ፓርቲ በተግባር ላይ ያላቸው
አቋም የሰማይና የመሬት ያህል የተራራቀ ነው ።

እስቲ የሚከተለውን በይበልጥ በሰል ያለውን ፣ ደግ
ሞም በብዛት የአድርባዮችን ስህተቶች በማጋለጥ ላይ
ያተኮረውን የካውትስኪን ስራ እንውሰድ ። ይህችም
የሶሻል አብዮት የተሰኘች ትንሽ መፅሀፍ ናት ። በዚ
ህች ፅሁፍ ውስጥ ደራሲው በተለይ «የወዛደሩ አብዮት»
«እና» «የወዛደሩ አገዛዝ» የሚለውን ጥያቄ እንደ ዋነኛ
ሃሳብ አድርጎ መርጧል ፣ ይህንንም ሲመለከት ከመ
ጠን በላይ ጠቃሚ የነበረ ነገር ሰጥቷል ፤ ነገር ግን የመ
ንግስትን ጥያቄ ወደ ጐን ትቷል ። ደራሲው በፅሁፉ
ውስጥ በሙሉ የመንግስት ስልጣንን ስለመያዝ ይና
ገራል — ከዚያ በላይ ምንም የለም ፤ ይኸውም የመን
ግስቱን አቋም ሳይደመስሱ ስልጣን ለመያዝ ይችላል
ብሎ እስካመነ ድረስ ለአድርባዮች የሚጠቅም ፎር
ሙላን ይመርጣል ። በኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ ፕሮግራም

ውስጥ ያለውንና በ1872 ማርክስ «ያፈጀ» ብሎ ያወጀው ነበር በ1902 በካውትስኪ የተንሰራራው !

በፅሁፍ ውስጥ አንድ የተለየ አንቀፅ « ለሶሻል አብዮት ቅርፆችና መሳሪያዎች »ተሰጥቷል ። እዚህ ላይ ካውትስኪ ስለሰፊው ህዝብ ፖለቲካዊ አድማ ፥ ስለ እርስ በርስ ጦርነት ፥ ስለ « የዘመናዊ ትልቅ መንግስት ሀይል አቋሞች ፥ እንደ ቢሮክራሲውና ጦር ሰራዊቱ » ስለመሳሰሉት ይናገራል ። ሆኖም ወዛደሮች ከኮሚዩን ስለተማሩት አንድም ቃል አይናገርም ። ኤንግልስ በተለይ ለጀርመን ሶሻሊስቶች ስለ መንግስት ስላላቸው « አምልኮአዊ ክብር » ማስጠንቀቂያ የሰጠው ካለምክንያት እንዳልነበር ግልፅ ነው ።

ካውትስኪ ነገሩን እንደሚከተለው ያብራራል ፤ አድራጊው ወዛደር « ዲሞክራቲክ ፕሮግራሙን ያካሄዳል » በማለት አንቀፆችን ያቀነባብራል ፤ ሆኖም የቡርዧውን ዲሞክራሲ በወዛደሩ ዲሞክራሲ በማፈኑ ጉዳይ ላይ በ1871 ስለተገኘው አዲስ ነገር አንድም ቃል አልተናገረም ። ካውትስኪ ጥያቄውን መሰረት የሌላቸው « ድፍን » ቃላትን በመናገር ይዘረዝራል ።

> « አሁንም ፥ በአሁን ሁኔታዎች መሰረት እኛ የበላይነትን ልንቀዳጅ እንደማንችል መናገር አያስፈልግም ። አብዮት እራሱ አስቀድሞ ረጅምና ጥልቀት ያለው ትግል መኖርን ይጠይቃልና ፥ እየቀጠለም ሲሄድ የአሉትን የእኛን የፖለቲካና ሶሻል መዋቅር ይለውጣል ። »

ያለምንም ጥርጥር ይህ ፈረሶች አጃ ይበላሉ ወይም የቮልጋ ወንዝ ካስፒያን ባህር ውስጥ ይፈሳል እንደሚባለው የታወቀ ሀቅ ነው ። ብቻ ያሳዝናል ፥ « በጥልቀት የሚጓዘው » ትግል የሚለውን ባዶና ከባድ ሀረጎች



መጠቀም ለአብዮታዊ ወዛደር ዋናው ፍላጎት የሆነውን ጥያቄ ማስወገጃ ዘዴ መሆኑ ፥ « በጥልቅ የሚጓዘው » የአብዮት ይዘቱ ከመንግስት ጋር ያለው ግንኙነት ፥ ከዲሞክራሲ ጋር ያለው ግንኙነትና ከፊተኞቹ የወዛደሩ ካልሆኑ አብዮቶች የሚለይበት የተገለጠ የት ነው ?

ምንም እንኳን በቃላት አድርባይነትን በመቃወም ጠንካራ ጦርነት ቢያውጅና « የአብዮትን ሃሳብ » ዋናነት ቢያጠነክርም ፥ ( ወዛደሮችን ስለአብዮት ተጨባጭ ትምህርቶችን ለማስተማር እስከተፈራ ድረስ ይህ « ሃሳብ » ምን ያህል ዋጋ ይኖረዋል ? ) ወይም « ከሁሉ ነገር በፊት አብዮታዊ ሃሳባዊነት » ቢልም ፥ የእንግሊዝ ወዛደሮች አሁን « ከንኡስ ከበርቴ በላይ አይደሉም » ብሎ ቢያውጅም ፥ ይህንን ጥያቄ በማስወገድ ፥ በዚህ በጣም ዋና በሆነ ነጥብ ላይ ካውትስኪ ተግባር ከአድርባይነት ጋር ስምምነት ያደርጋል ።

> « በጣም የተለያዩ የድርጅት ቅርፆች — ቢሮክራሲያዊ (??) ትሬድ ዩኒየኒስት ፥ የህብረት ስራ ፥ የግል . . . በሶሻሊስት ህብረተሰብ ውስጥ ጎን ለጎን ሊኖሩ ይችላሉ » ይላል ካውትስኪ ሲፅፍ ። « . . . ካለቢሮክራሲያዊ (??) ድርጅት ሊሰሩ የማይችሉ ድርጅቶች አሉ ፥ ለምሳሌ የባቡር መስመሮች ። እዚህ ላይ የዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች የሚከተለውን ቅርፅ ሊወስዱ ይችላሉ ። የስራን ደንብ የሚያወጡና የቢሮክራሲያዊውን መሳሪያ (አቋም) አስተዳደሩን የሚቆጣጠሩ በፓርላማ አይነት የሚመሰረቱ ወኪሎች ወዛደሮች ይመርጣሉ ። የሌሎች ድርጅቶች አስተዳደር

ወደ ሠራተኞች ማህበራት ሊለወጡ ይችላሉ ።
እንዲሁም ሌሎች የህብረት ስራ ድርጅቶች
ሊሆኑ ይችላሉ ። » (ገፅ 148—115 የሩሲያ
ትርጉም ፣ በጀኔቭ የታተመ 1903)

ይህም አስተሳሰብ ስህተት ነው ፤ በሰባኛዎች አመ
ታት ውስጥ (ከ1870—80 ባሉት አመታት ተርጓሚው)
ማርክስና ኤንግልስ የኮሚዩን ትምህርቶችን እንደም
ሳሌ በመጠቀም ከሰጡት ገለፃዎች ጋር ሲነፃፀር አንድ
እርምጃ ወደኋላ ነው ።

የ« ቢሮክራሲ » ድርጅት ያስፈልጋል እስከተባለ
ድረስ ፣ በባቡር ሀዲዶችና በማንኛውም ሌላ ድርጅት
በትልልቅ ኢንዱስትሪና በማንኛውም ፋብሪካ ፣
በትልልቅ መደብሮች ፣ ወይም ሰፋፊ የካፒታሊስት እርሻ
ድርጅት መካከል ምንም አይነት ልዩነት የለም ። እን
ደነዚህ ያሉት ድርጅቶች የአሰራራቸው ስርአት ጥብቅ
ዲሲፕሊን መኖር ፣ እያንዳንዱ የሰራውን ድርሻ ያለ
ምንም ስህተት ማከናወኑ የማይጣስ ፍፁም ግዴታ ነው፣
አለበለዚያ ድርጅቶች በሙሉ ወደ መቆም ይሄዳሉ ፣
ማሽነሪዎች ፣ ወይም የተመረቱት ምርቶች ይበላሹ
ይሆናል ። አዎን በእንደዚያ ያሉ ድርጅቶች ሁሉ ሰራ
ተኞች « በፓርላማ አይነት የሚመሰረቱ ወኪሎቻቸ
ውን ይመርጣሉ ። »

ነገር ግን ያ ዋናው ነጥብ ፣ እንደዚህ « አይነቱ ፓር
ላማ » እኛ እንደምናውቀው የቡርዧ ፓርላሜንታዊ
ተቋሞች ሊሆን አለመቻሉን ነው ። ዋናው ቁም ነገር
የዚህ « አይነት ፓርላማ » ሃሳቡ ከቡርዧ ፓርላማ
ክልል ውጭ የማያልፈው ካውትስኪ እንደሚያሳስበው
በቀላሉ « የስራ ደንቦችን የሚያወጣና የቢሮክራቲክ



ተቋሙን አስተዳደር የሚቆጣጠር » ብቻ አይሆንም ።
በሶሻሊስት ህብረተሰብ ይህ « አይነቱ ፓርላማ » የወ
ዛደር ወኪሎችን የያዘ ፣ በእርግጥ « የስራ ደንቦችን
የሚያረቅና » የተቋሞችንም « አስተዳደር የሚቆጣ
ጠር » ይሆናል — ነገር ግን ይህ ተቋም « ቢሮክራቲክ»
አይሆንም ። ወዛደሮች የፖለቲካ ስልጣን ተቀዳጅተው
አሮጌውን ቢሮክራቲክ ተቋም ይደመስሳሉ ፣ መሰረቱን
ይበታትናሉ ፣ ዋና ስሮቹን ይነቃቅሉታል ፤ ከወዛደሮ
ችና ከቢሮ ተቀጣሪዎች በተውጣጣ በአዲስ ቡድን
ይተኩታል ። እነዚህ ሰዎች ቢሮክራቶች እንዳይሆኑ
የሚወስደውን እርምጃም ማርክስና ኤንግልስ በሰፊው
ዘርዝረዋል ። 1. መምረጥ ብቻ ሳይሆን በተፈለገ ጊዜም
እንዲነሱ ፣ 2. የሚከፈላቸው ከወዛደሩ የሚበልጥ እን
ዳይሆን ፣ 3. ለጊዜው ሁሉም « ቢሮክራቶች » እንዲ
ሆኑና በኋላም ማንም « ቢሮክራት » እንዳይሆን በፍጥ
ነት በሁሉም ቁጥጥር እንዲደረግ ማድረግ ።

ካውትስኪ « ኮሚዩኑ በአንድ ጊዜ » ህግ አርቃቂና
ህግ አስፈፃሚ የሆነ የስራ አካል እንጂ ፓርላሜንታዊ
አልነበረም ። » የሚሉትን የማርክስን ቃላት በፍፁም
አልተገነዘበም ።

ዲሞክራሲን (ለህዝቡ ያልሆነ) ከቢሮክራሲ (ፀረ
ህዝብ የሆነ) ጋር በሚያደባልቀው ቡርዧ ፓርላሜ
ንታዊነትና ቢሮክራሲን ከስሩ ለመቁረጥ እርምጃ በሚ
ወስደው ፣ ይህንንም እስከመጨረሻው ለማድረስ ቢሮ
ክራሲን ጨርሶ ለማጥፋት ፣ ፍፁም ዲሞክራሲን ለህ
ዝብ ለማምጣት በሚችለው በወዛደሩ ዲሞክራሲ መካ
ከል ያለው ልዩነት ለካውትስኪ አልገባውም ።

እዚህ ካውትስኪ ያሳየው ያንኑ አሮጌ ለመንግስት
ያለውን የ« አምልኮ ክብር » እና በቢሮክራሲ « አም
ላካዊ እምነት » ነው ።

እስቲ አሁን ደግሞ ካውትስኪ ከአድርባዮች ጋር
ባደረገው ተቃውሞ ፤ መጨረሻውና ጥሩው ወደ
ሆነው ለስልጣን መንገድ የተሰኘችው የካውትስኪ ስራ
መፅሀፍ እንለፍ ። (እንደማምነው ከሆነ የታተመው
በ1909 አድሣሪነት የሰፈነበት ስለነበር ወደ ሩሲያ
ቋንቋ አልተተረጐመም ነበር )። ይህች መፅሀፍ
በበርንስታይን ላይ በ1899 እንደተፃፈው በአጠቃላይ
ስለ አብዮት ፕሮግራም ብቻ ባለማተቷ ፤ ወይም ደግሞ
እንደ 1902 አመቱ የሶሻል አብዮት የተሰኘው ፅሁፍ
የተፈፃመበትን ጊዜ የማትመለከት የሶሻል አብዮት
ተግባር ብቻ የምታትት ስላልሆነች ሲያስተውሉት የሚ
ገባ አስተያየት ሰንዝራለች ። በተጨባጭ ሁኔታዎች
«የአብዮት ዘመን » እየተቃረበ መሆኑን እንድንገዘብ
ታስገድደናለች ።

በእርግጥ ደራሲው በአጠቃላይ የመደብ ተፃራሪነ
ቶች እየጐሉ መሄድና ለኢምፔሪያሊዝምም ትልቅ
ድርሻ እንደሚጫወት አመልክቷል ። «ከ1789—1871»
የምእራብ አውሮፓ « የአብዮት ክፍለ ጊዜ » በኋላ በ1905
ተመሳሳይ ክፍለ ጊዜ በምስራቅም ጀምሯል ብሏል ።
የአለም ጦርነት በአስፈሪ ፍጥነት እየተቃረበ
ነው ። « ከእንግዲህ ወዲህ ወዛደሩ አብዮቱ ጮርቃ
ነው ብሎ የሚያወራበት ጊዜ አይደለም ። « ወደ አብ
ዮታዊ ክፍለ ጊዜ ገብተናል ። « አብዮታዊው ዘመን
እየጀመረ ነው ። »

እነኚህ አባባሎች በትክክል ግልፅናቸው ። ይህች
የካውትስኪ መፅሀፍ የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ ከኢ



ምፔሪያሊስት ጦርነት በፊት ነኝ ብሎ በሰጠን ተስፋና
ጦርነቱ በፈነዳ ጊዜ ካውትስኪም ተጨምሮ በሰመጠ
በት የውርደት አዘቅት ጥልቀት መካከል ያለውን ልዩ
ነት የመመዘኛ መለኪያ ሆኖ አገልግሏል ። « ያሁኑ
ሁኔታ እኛ (ይኸውም ጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ) በአደ
ጋው ጭነት ምክንያት በርግጥ ያልሆነውን በጣም ለስላሳ
መስለን እንታይ ይሆናል» ብሎ ካውትስኪ አሁን እኛ
በምንመረምረው መፅሀፍ ፅፎ ነበር ። ሀቁ ግን የጀር
መን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሆኖ ከሚታየው በላይ
በጣም ለስላሳና አድርባይ መሆኑ ነው !

ዋናው ልዩ ጠባይ ምንም እንኳን ካውትስኪ በእር
ግጥ የአብዮት ዘመን መጀመሩን ቢገልፅም መፅ
ሀፉ እርሱ እንዳለው በእርግጥ ትንተናውን ያዋለው
«በፖለቲካዊ አብዩት» ላይ ቢሆንም እንደገና የመን
ግስትን ጥያቄ በፍፁም ማግለሉ ነው ።

ጥያቄውን ወደጐን መተው ፤ ግድፈቶችና ስውር
ትርጉሞች መስጠት ፤ የዚህ ሁሉ ጠቅላላ ድምር ያለ
ጥርጥር ሙሉ በሙሉ ከዚህ ቀጥለን መመልከት ወደ
አለብን ወደ አድርባይነት መገልበጥ አምርቷል ።

የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ ፤ በካውትስኪ አማካኝ
ነት የሚከተለውን ያወጀ ይመስላል ፤ እኔ አብዮታዊ
አስተያየቶችን አደግፋለሁ (1899) ፤ እኔ በተለይ የወዛ
ደሩ ሶሻል አብዮት የማይቀር መሆኑን አውቃለሁ
(1902) ፤ እኔ የአብዮቶች አዲስ ዘመን መድረሱን (መቃ
ረቡን) አውቃለሁ (1909) እኔ አሁንም ወደ ኋላ በመ
ሄድ በ1852 መጀመሪያ ገደማ ማርክስ ያለውን በማ
ስታወስ የወዛደሩ አብዮት ተግባሮች ከመንግስቱ ጋር
ስለሚኖረው ግንኙነት ጉዳይ አነሳለሁ 1912 ።

በትክክል ካውትስኪ ከፓኔኮክ ጋር ባደረገው
ክርክር ጥያቄው የቀረበው በቀጥታ በዚህ ቅርፅ ነበር ።

## 3. የካውትስኪ ክርክር ከፓኔኮክ ጋር

ካውትስኪን በመቃወም ፣ ከነ ሮዛ ሉክስምበርግ ፣
ካርል ራዴክና ሌሎችን በውስጡ ከያዛቸው « የግራ
ስርነቀል » ዝንባሌ ተወካዮች ውስጥ ፓኔኮክ እንደ
አንዱ በመሆን የወጣ ነው ። ካውትስኪ የ« መሃል» አቋ
ም በመውሰዱ መርህ በሌለው ሁኔታ በማርክሲዝምና
በአድርባይነት መሀከል መወላወሉን ስላመኑበት እነርሱ
በአንድ ላይ በመሆን አብዮታዊ ታክቲኮችን ደገፉ ።

የዚህም አስተያየት ትክክለኛነት በጦርነቱ ሙሉ በ
ሙሉ ተረጋገጠ ። (በስህተት ማርክሲስት የተባለው)
ይህ « መሃል ሰፋሪ »አዝማሚያ ወይም ካውት
ስኪዝም ፣ እራሱን የገለፀው ሙሉ በሙሉ በአንድ
አስከፊ አስቀያሚና ምስኪን በሆነ ሁኔታ ነበር ።

« ህዝባዊ ድርጊትና አብዮት » ( ማሳየት ፣ 1912 ፤
ቅፅ 30 ፤ 2) በተሰኘው የጋዜጣ ፅሁፍ ፓኔኮክ የካው
ትስኪን አስተሳሰብ ሲያስረዳ እንደ አንድ በስራ ላይ
የማይውል ቸልተኛ « ስርነቀልነት » የድርጊት አልባ
« ተስፋ ቲዎሪ » ብሎታል ። ፓኔኮክ ሲፅፍ « ካውት
ስኪ የአብዮትን ሂደት ለማየት እምቢ ያለ ነውይላል »
(ገፅ 616) ። ፓኔኮክ በዚህ መልክ ነገሩን በማቅረብ
የወዛደሩ አብዮት ተግባሮች ከመንግስት ጋር ስለሚኖ
ረው ግንኙነት ስላየው እኛም ፍላጎት እሳድሮብናል ።

> « የወዛደሩ ትግል » ይላል ሲፅፍ « እንዲያው ከቡ
> ርዧው ጋር ስለመንግስት ስልጣን የሚደረግ የተ
> ቃውሞ ትግል ብቻ አይደለም ። ነገር ግን ከመን
> ንግስቱ ስልጣን ጋር የሚደረግ አንድ ትግል እንጂ



> የወዛደሩ አብዮት ይዘት በወዛደሩ ሀይልና መሳ
> ሪያ ረዳትነት የመንግስቱን የስልጣን መሳሪያ
> ማፍረስና ማጥፋት ነው ። . . ትግሉ ሊቆም የሚ
> ችለው የእርሱ (የወዛደሩ መደብ ተርጓሚ) የመን
> ግስት ድርጅት ሲደመሰስ ብቻ ነው ። የአብዛኛው
> ድርጅት ከዚህ በኋላ የጥቂቶቹን ገዥ ድርጅት
> በመደምሰስ የበላይነትን የሚገልፅበት ነው ። »
> (ገፅ 548)

የፓኔኮክ የሃሳቦች አቀራረብ ስልት ጠለቅ ያለ
ጉድለት ቢኖረውም ፣ ምንም ቢሆን ትርጉሙ ግልፅ
ነው ። ስለሆነም ካውትስኪ እንዴት ለመከላከል እንደ
ሞከረ መመልከቱ አስደሳች ነው ።

> « እስካሁን » ይላል ካውትስኪ ፣ « በሶሻል ዲሞ
> ክራቶችና በስርአት አልበኞች መካከል ያለው
> ልዩነት ፣ የፊተኛው የመንግስት ስልጣንን ለመ
> ጨበጥ ሲመኝ ፣ የኋለኛው ደግሞ ለመደምሰስ
> ይመኛል ። ፓኔኮክ ግን ሁለቱንም ለማድረግ
> ይፈልጋል ። » (ገፅ 724)

የፓኔኮክ ገለፃ ጥራትና ትክክለኛነት ቢጎለውም
ከአሁኑ ርእስ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን በፅሁፉ
ውስጥ ስላሉት ሌሎች ጉድለቶች ላነጋገር ፤ ካው
ትስኪ በፓኔኮክ የተነሳውን የመርህ ነጥብ ምክን
ያት በማድረግና በዚህ የመሰረታዊ የመርህ ነጥብ
ላይ የማርክሲስቶችን አቋም ፍፁም በመተው ወደ
አድርባይነት ሙሉ በሙሉ ሄድዋል ። በሶሻል
ዲሞክራቶችና በስርአት አልበኞች መካከል ስላ
ለው ልዩነት የሰጠው ትርጉም ያለጥርጥር ስህተት ነው
በዚህም ማርክሲዝምን በርዞና አጣሟል ።

በማርክሲስቶችና በስርአት አልበኞች መሀከል ያለው ልዩነት ይህ ነው ፤ 1/ የመጀመሪያዎቹ ሙሉ በሙሉ መንግስትን ለማጥፋት ሲያልም ፥ ይህም አላማ በስራ ሊተረጐም የሚችለው መደቦች በሶሻሊስት አብዮት ሲወገዱ ፥ ሲጠፉና የዚህም ውጤት ሶሻሊዝምን ሲመሰርት መንግስትም ቀስ በቀስ እየመነመነና እየጠፋ የሚሄድ መሆኑን ይቀበላሉ ። የኋለኞቹ ደግሞ መንግስት በምን አይነት ሁኔታ እንደ ሚጠፋ መረዳት ስለተሳናቸው መንግስትን በአንድ ሌሊት ለማጥፋት ይፈልጋሉ ። 2/ የመጀመሪያዎቹ ወዛደሩ የፖለቲካ ስልጣን ከጨበጠ በኋላ የአሮጌውን መንግስት ተቋም መደምሰስና በምትኩም አዲስ የኮሚዩን አይነት የታጠቁ ወዛደሮችን የያዘ የሚተካው መሆኑን ያውቃሉ ። የኋለኞቹ የመንግስቱን አቋም እንዲደመሰስ ሲያስገድዱ ፥ ወዛደሩ በቦታው ምን እንደሚተካ አብዮታዊ ሀይሉን እንዴት እንደሚጠቀምበት ፥ ስርአት አልበኞቹ ፥ ሌላው ቀርቶ አብዮታዊው ወዛደር የመንግስት ስልጣን መጠቀም እንዳለበት እንኳን አያምኑም ። የእነርሱንም አብዮታዊ የበላይ ገዥነት ይክዳሉ ። 3/ የመጀመሪያዎቹ ወዛደሩ የአሁኑን መ ግስት በመጠቀም ለአብዮት እንዲዘጋጁ ሲጠይቁ ፥ ስርአት አልበኞቹ ይህንን ይቃወማሉ ።

በዚህ ክርክር ውስጥ ማርክሲዝምን የወከለ ካውትስኪ ሳይሆን ፓኔኮክ ነው ። ወዛደሩ የመንግስት ስልጣን ሲጨብጥ አሮጌውን የመንግስት አቋም ወደ አዲስ እጅ በቀላሉ ማሳለፍ በሚል ስሜት ሳይሆን ፥ ይህንን አቋም መደምሰስና መሰባበር ፥ በአዲስ መተካት እንዳለበት ነበር ማርክስ ያስተማረው ።



ካውትስኪ ማርክሲዝምን በመተው ወደ አድርባዮች ፊና (ካምፕ) ገባ ። በአድርባዮች ተቀባይነት የሌለውን የመንግስት መሳሪያ መደምሰስን ከክርክሩ ውስጥ በጭራሽ በማጥፋትና ቀዳዳ በመተው ለእነርሱ ያ «ማሸነፍ» ማለት ብዙሃኑን ማቀፍ ተብሎ በቀላሉ እንዲተረጐም አድርጓል ።

በእርሱ የተጣመመውን ማርክሲዝምን ለመሸፈን ፥ ካውትስኪ የመፃህፍት ሰው በመምሰል ከእራሱ ከማርክስ በ « መጥቀስ » ያቀርባል ። ማርክስ በ1850 «ጠንካራ የሀይል ዋህድነት በመንግስት ስልጣን እጅ» የመሆኑን አስፈላጊነት ፅፎ ነበር ። ካውትስኪ በድል አድራጊነት ፓኔኮክ « ዋህድነትን » ለማጥፋት ይፈጋልን ? ብሎ ይጠይቃል ።

ይህ ባጭሩ በርንስታይን ማርክሲዝምና ፕሮዶኒኒዝም በፌደራልዝምና በዋህድነት ላይ ያላቸው አስተያየት ተመሳሳይ ነው እንዳለው ያለ ቀልድ ነው ።

የካውትስኪ « ጥቅስ » ከዚህም ወይ ከዚያም አይደለም ። ዋህድነት በአሮጌውም ሆነ በአዲሱ መንግስት መሳሪያ (አቋም) ሊሆን ይችላል ። ወዛደሮች በፈቃደኛነት የጦር ሃይላቸውን አንድ ቢያደርጉ ይህ ዋህድነት ነው ። ሆኖም የሚመሰረተው ዋህዳዊ የሆነውን የመንግስት ቋሚ ጦር ሠራዊት ፖሊስና ቢሮክራሲውን «በሙሉ በመደምሰስ» ነው ። ካውትስኪ ማርክስና ኤንግልስ በኮሚዩን ላይ ያላቸውን በደንብ የታወቁ ክርክሮችን በመተው ፥ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ጥቅሶች እየለቀመ በማውጣት ያጭበረብራል ።

«ምናልባት ፓኔኮክ ፥ » ይላል ካውትስኪ መበቀጠል ፥ «የመንግስት ባለስልጣኖችን ተግባር

ለማጥፋት ይፈልጋል ? ሆኖም በመንግስት አስተ
ተዳደር ይቅርና በፓርቲውና በሠራተኛ ማኅበሮች
እንኳን ያለ ባለስልጣኖች ልንራመድ አንችልም
ፕሮግራማችን የመንግስት ባለስልጣኖችን ይጥፉ
ብሎ አይጠይቅም ፤ በህዝብ ይመረጡ ነው እንጂ
. . . እዚህ ላይ እኛ የምንወያይበት 'የወደፊቱ መን
ግስት' የአስተዳደር ተቋም ቅርፅ ምን እንደሚመ
ስሉ ፥ አይደለም ግን እኛ የፖለቲካ ትግል የመ
ንግስቱን ስልጣን ከመያዛችን በፊት (ሰረዝ የካ
ውትስኪ) የመንግስትን ሀይል ያጠፋው እንደሆነ
ነው ። የትኛው ሚኒስቴር ነው ከባለስልጣኖቹ ጋር
መደምሰስ ያለበት ? «ከዚያም በማከታተል የትምህ
ርት ፥ የህግ ፥ የገንዘብ እና የጦር ሚኒስቴሮች ዝርዝር
ይቀጥላል ። » አይደለም ፥ አንዳቸውም የአሁኖቹ
ሚኒስቴሮች እኛ ከአገዛዙ ጋር ባለን የፖለቲካ
ትግል አይነሱም ። አለመግባባትን ለማስወገድ
አሁንም እደግመዋለሁ ከዚህ ላይ እኛ የምንወያይ
በት አሸናፊው ሶሻል ዲሞክራሲ የሚሰጠንን የወ
ደፊቱን መንግስት ቅርፅ ሳይሆን ፥ የአሁኑን መን
ግስት በእኛ ተቃውሞ እንዴት እንደሚለውጥ
ነው ። » (ገፅ 725)

ይህ ግልፅ የሆነ ማታለል ነው ፡— ፓኔኮክ ያነ
ሳው የአብዮት ጥያቄ ነው ። የፅሁፉ ርእስም ሆነ ከላይ
ያሳየነው ጥቅስ በግልፅ ይህንን ያመለክታል ። ወደ
«ተቃውሞ » ጥያቄ በመዝለል ካውትስኪ አብዮታዊ
ውን በአድርባይ አስተያየት ይተካዋል ። እርሱ ያለው
እንዲህ ነው ፡— በአሁን ጊዜ እኛ ተቃዋሚዎች ነን ፥
ስልጣን ከያዝንም በኋላ የምንሆነውን ያኔ እናያለን ።



አብዮትም ጠፍቷል ! እና ያንን ነው በእርግጥ አድርባዮቹ
የፈለጉት ።

በክርክር ላይ ያለው ነጥብ ስለተቃውሞ ወይም ስለ
ጠቅላላ የፖለቲካ ትግል ሳይሆን ስለ አብዮት ነው ።
አብዮት ወዛደሩ «የአስተዳደር ተቋሙንና» መላውን
የመንግስት መሳሪያ ደምስሶ የታጠቁት ወዛደሮ
ችን በያዘ አዲስ መሳሪያ መተካት ነው ። ካውትስኪ
ለ «ሚኒስቴሮች» «አምልእኰአዊ ክብር» ያሳያል ፤ ግን
ለምን እነሱን (ሚኒስቴሮችን — ተርጓሚ) በወዛደሮ
ችና በወታደሮች ተወካይ ሶቨዬቶች የበላይነት በሚ
ሠሩ የባለሙያዎች ኰሚቴ መተካት አይቻልም ?
ቁም ነገሩ « ሚኒስቴሮች » እንዳሉ ይቀራሉ ፥ ወይም
« የባለሙያዎች ኮሚቴዎች» ወይም ሌላ ተቋሞች
ይቋቋማሉ አይደለም ፥ ያ ምንም ዋጋ የለውም ። ቁም
ነገሩ የአሮጌውን መንግስት መሳሪያ (በብዙ ሺህ ክሮች
ከቡርዧው ጋር በጣም ጥልቅ በሆነ መንገድ የተወሳሰ
በውና በተለምዶ ስራና በግፊት የተበከለው እንዳለ
ይቀራል ፤ ወይም መደምሰስና በሌላ በአዲስ መተካት
አለበት የሚል ነው ። አብዮት አዲሱ መደብ በአ
ሮጌው መንግስታዊ አቋም ረዳትነት ማዘዝ ፥ ማስተ
ዳደር ብቻ ሳይሆን ፥ ይህ መደብ ይህንን አቋም መሰ
ባበርና በአዲሱ አቋም ረዳትነት ማዘዝና ማስተዳደር
ነው ። ካውትስኪ የማርክሲዝምን መሰረተ ሃሳቦች
አዋርዷል ወይም ነገሩን በፍፁም ሊረዳው አልቻለም ።

እርሱ በባለስልጣኖች ላይ ያለው ጥያቄ በግልፅ የሚ
ያሳየው ከኮሚዩኑ የተገኘውን ትምህርት ወይም በማ
ርክስ የተሰጡትን ትምህርቶች በምንም አይነት እንዳል
ተረዳው ነው ። « ያለ ባለስልጣኖች ሌላው ቀርቶ በፓ

ርቲውና ሠራተኛ ማህበሮች ሳይቀር ልንራመድ አንች
ልም . . . »

በካፒታሊዝም ስር ፥ በቡርዧው የአገዛዝ ስር
ያለ ባለስልጣኖች ልንራመድ አንችልም ። ወዛደሩንና
በአጠቃላይ ሰፊው ለፍቶ አደር ህዝብ በካፒታሊዝም
ተጨቁናል ። በካፒታሊዝም ስር ፥ በሰፊው ህዝብ የደ
ሞዝ ባርነት ፥ ችግርና ስቃይ ሁኔታዎች ዲሞክራሲ
የተወሰነ ፥ የጠበበ ፥ የተገደበ ፥ የተቆራረጠ ነው ።
የፖለቲካ ድርጅቶቻችንና የሠራተኛ ማህበሮቻችን
ብልሹ የሆኑበት ምክንያት ይህ ብቻ ነው ወይም ፥
በይበልጥ ትክክል ለመሆን ፥ ወደ ብልሹነት ያዘነበ
ሉት የካፒታሊዝም ሁኔታዎች ወኤአቸውን ስለ ገደሉባ
ቸው በተዘዋዋሪ መንገድ ቢሮክራቶች ለመሆን ፥
ማለትም ልዩ መብት ያላቸው ሰዎች በመሆን ከሰፊው
ህዝብ በመገንጠል ከሰፊው ህዝብ በላይ የመቆም
ፍላጎት ስላሳደረባቸው ነው ።

ያ ነው በመሰረቱ የቢሮክራሲ ባህሪ ፤ ካፒታሊስቶች
ካልተወረሱና ቡርዧው ካልተገረሰሰ ፥ ሌላው ቀርቶ
የወዛደሩ አገልጋዮችም የተወሰነም ቢሆን « ቢሮክራ
ሲያዊ» መሆናቸው የማይቀረው ።

እንደ ካውትስኪ ከሆነ ፥ በምርጫ የመጡ የህዝብ
አገልጋዮች በሶሻሊዝም ውስጥ ስለሚቆዩ ባለስልጣና
ችም ይቆያሉ ፤ ቢሮክራሲም ይቆያል ! ይህ ነው በትክ
ክል የእርሱ ስህተት ። ማርክስ የኮሚዩኑን ምሳሌ በት
ክክል በመጠቀም ነው በሶሻሊዝም ስር የህዝብ አገል
ጋዮች « ቢሮክራቶች » ከመሆን ፥ « ባለስልጣኖች »
ከመሆን ይቆማሉ ያለው ፥ እነርሱም ከመጠን በላይ
ከመሆን የሚቆሙበት ፥ የባለስልጣኖች መምረጥ መርህ



ሌላ በአስፈለገ ጊዜ መልሶ የመጥራት መርህ ስለሚታ
ከልበት ነው ። ከዚህም በላይ ደመወዝ በመካከለኛ
ሰራተኛ ምንዳ ልክ ይቀንሳል ። እንዲሁም የፓርላማ
ተቋሞች « በጣምራ ህግ አውጪና አስፈፃሚ በሆኑ
የስራ አካሎች » ይተካል ።

በመሰረቱ ካውትስኪ በፓኔኮክ ላይ ያነሳው ክር
ክር ፥ በተለይም በፓርቲያችንና በሰራተኛ ማህበሮች እን
ኳን ቢሆን ያለባለስልጣኖች ምንም ለማድረግ አንች
ልም የሚለውን አስገራሚ አስተሳሰብ ቀደም ሲል በር
ንስታይን በማርክሲዝም ላይ ያነሳውን ክርክር እንደገና
ካውትስኪ መድገሙ ነው ። የሶሻሊዝም መንስኤ በሚ
ለው መፅሀፉ በርንስታይን የ « ጥንታዊ » ዲሞክራሲን
ሃሳቦች ይቃወማል ፤ « ዶክቲሪነር ዲሞክራሲ » ብሎ
የሰየመውን ማለትም ሀላፊነት የተሰጠው አዛዥ የማይ
ከፈላቸው ባለስልጣኖች ፤ ደካማ ማእከላዊ ተወካይ
ክፍሎች ፤ ወዘተ . . ይቃወማል ። « ጥንታዊ ዲሞክ
ራሲ » ትክክል አለመሆኑን ለማረጋገጥ በዌብል አተ
ረጓጎም መሰረት የእንግሊዞችን ሰራተኛ ማህበሮችን
ልምድ በርንስታይን ይጠቅሳል ። « በሙሉ ነፃነት »
የተደረገው የሰባ አመት እድገት ,የጥላላል (የጀርመን
እትም ገፅ 137) ጥንታዊ ዲሞክራሲ ዋጋ ቢስ መሆኑን
የሰራተኛ ማህበሮች በተራ ዲሞክራሲ ማለትም በፓርላ
ማና በቢሮክራሲ እንዲተኩት አሳምኗል ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሰራተኛ ማህበሮች«በሙሉ ነፃነ
ት» አላደጉም ፥ ያደጉት በፍፁም የካፒታሊስት የባርነት
ውስጥ ክፋት በሰፈነበት ፥ ውንብድና ፥ ሃሰትና
ድሃውን « ከከፍተኛ » አስተዳደሩ ጉዳይ መገለሉን መስ
ማማቱ « ሊያስወግዱት የማይቻል » ነበር ። በሶሻሊ

ዝም ስርአት ውስጥ ብዙ « የጥንታዊ » ዲሞክራሲ
መመለሱ የማይቀር ነው ፤ ይኸውም በሰለጠነው ህብ
ረተሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ በድምፅ መስጠት ምርጫ
ብቻ ሳይሆን በየእለቱ የአስተዳደር ጉዳይ ጭምር
ህዝቡ ነፃ የሆነ ተሳትፎ የሚወስድበት ደረጃ ይደርሳል።

ማርክስ በአርቆ አስተዋይነት እንዳስገነዘበው ፣ የኮ
ሚዩንን ተግባራዊ እርምጃ ዋናው የለውጥ ነጥብ ነው።
ይህንንም አድርባዮች ስለሚፈሩ ለማወቅ አይፈልጉም።
ምክንያቱም ችኩል ስለሆኑና ታላላቅ የሶሻል ለውጦች
ንም ስለማይረዱና ስለማይገባቸው ነው ። በአድርባይነት
የተወጠሩ ፤ በመሰረቱ ከልባቸው በአብዮቱ የማያምኑ ፣
በአብዮት ንቃት ህሊና የልታደሱና አብዮትን በጣም
የሚፈሩት ሰዎች ፣ « የአሮጌውን የመንግስት መሳሪያ
ለመደምሰስ ማሰብ የለብንም ፣ ያለ ሚኒስቴሮችና ያለ
ባለስልጣኖች እንዴት እንሆናለን ? » በማለት (እንደ
እኛዎቹ ሜንሼቪኮችና ሶሻሊስት አብዮታውያን) ይከ
ራከራሉ ።

« የአሮጌውን የመንግስት መሳሪያ መደምሰስ ብቻ
ማሰብ አለብን ፤ ያለፉትን የወዛደር አብዮቶች ተጨባጭ
ትምህርት መመርመርና በተደመሰሰው እግር የሚተካ
ውንና እንዴትም እንደሚተካ ማሰብ ጥቅም አይሰ
ጥም ።» በማለት አናርኪስቶች (በእርግጥ ጥሩዎች አና
ርኪስቶች እነ ክሮፓትኪንና ጓደኞቹን የሚከተሉት
ከቡርዧው ንቃት ኋላ የሚጎተቱት ፤ ሳይሆኑ ) ይከራ
ከራሉ ። በዚህ ምክንያት ስርአተ አልበኞቹ የሚጠቀ
ሙበት ዘዴ ከተስፋ መቁረጥ የመጣ እንጂ ፣ የብዙሃን
ንቅናቄ ሁኔታን በመገንዘብ ተጨባጭ ችግሮችን ለማ
ቃለል ምህረት የሌለው አብዮታዊ እርምጃ አልወሰ
ዱም ።



እነዚህን ሁለት ስህተቶች እንድናስወግድ ማር
ክስ አስተምሮናል ። መላውን የአሮጌው መንግስታዊ
አቋም ለመደምሰስ ከፍተኛ ድፍረት እንዲኖረን ያስተ
ምረናል ። ከዚህም አያይዞ ጥያቄውን በተጨባጭ ሁኔታ
እንድናየው ያስተምረናል ። ኮሚዩኑ በጥቂት ሳምንታት
ውስጥ የወዛደሩን አዲስ መንግስታዊ አቋም ለመገንባት፣
በመጀመር ለመጀመሪያ ሰፊ ዲሞክራሲ ለማግኘትና ቢሮ
ክራሲን ከስሩ ለመንቀል ልዩ ልዩ እርምጃዎች ወስደ
ዋል ። ከኮሚዩኑ ተሳታፊዎች እስቲ አብዮታዊ ድፍረ
ትን እንማር ፣ ከተወሰዱትም ድርጊታዊ እርምጃዎች
አስቸኳይና ሊደረጉ የሚችሉ የድርጊቶችን እቅድ ለማ
የት እንሞክር ፣ ይህንንም መንገድ በመከተል ቢሮክራ
ሲን በፍፁም ለመደምሰስ እንችላለን ።

የመደምሰሱም ዋስትና የሚያገኘው ሶሻሊዝም የስራ
ቀኖችን ስለሚቀንስ ፣ ሰፊውን ህዝብ ወደ አዲስ ህይ
ወት ስለሚያሳድግ ፣ ለአብዛኛው ህዝብ እንዲህ ዓይነት
ሁኔታን በመፍጠር እያንዳንዱ ሰው አንድም ሳይቀር
የመንግስት ተግባራትን እንዲያከናውን ሲያደርግ ማን
ኛውም አይነት የመንግስት ቅርፅ በአጠቃላይ በፍፁም
መንምኖ እንዲጠላ ያደርጋል ።

«የሰፊው ህዝብ የስራ ማቆም» አላማ ይላል ካውት
ስኪ ፤ «የመንግስትን ስልጣን ለመደምሰስ ፍፁም
ሊሆን አይችልም ፤ አላማው በአንዳንድ ጥያቄዎች
ላይ ስምምነትን ከአገዛዙ ለማግኘት ብቻ ነው ፣
ወይም ይህንን የማያደርግ የጠላት አገዛዝን በሌላ
የወዛደሩን ፍላጎቶች ለቀቅ በሚያደርግ እንዲተካ
ማድረግ ነው።. . . ነገር ግን በምንም ሁኔታ» (ይኸ
ውም በጠላት አገዛዝ ላይ የወዛደሩ ድል ) «የመ

ንግስቱን ስልጣን ለመደምሰስ ማምራት የለበትም
ሊያደርግ የሚችለው በመንግስቱ የስልጣን ግን
ኙነቶች ላይ ለውጥን ማምጣት ብቻ ነው . . . ። ከዚህ
በፊት እንደሆነው ፡ የፖለቲካ ትግላችን አላማ
መሆን የሚችለው ፡ በፓርላማ ውስጥ አብዛኛ
ውን ድምፅ ማግኘትና ፓርላማ የአገዛዙ አዛዥ
እንዲሆን ማድረግ ነው ። » (ገፅ 726.727.732)

ይህ ጥርት ያለ ስድ አድርባይነት እንጂ ሌላ አስተሳ
ሰብ አይደለም ፡ ይህም አብዮትን በአፍ መቀበልና
በድርጊት ግን መቃወም ነው ። የካውትስኪ አስተሳሰብ ፤
« ለወዛደሩ ፍላጎት ለቀቅ . . . ለሚያደርግ አገዛዝ »
ከሚለው ፈቀቅ ለማለት አልቻለም ። ይኸው ወደኋላ
ከማሰብ ወደ 1847 ማለትም የኮሚኒዩስት ማኒፌስቶ »
ወዛደሩን እንደገዥው መደብ ማደራጀት ብሎ ባወጀበት
ጊዜ ከነበረው አድርባይነት ጋር የሚወዳደር ነው ።

ካውትስኪ « የወዛደሩን ፍላጎት ለቀቅ ለሚያደርግ»
አገዛዝ ለሚለው የሚታገሉ እነ ሺድማስ ፕሌካኖቭ
ቨንደርቬልድ ጋር ሊኖር የሚፈልገውን « አንድነት »
መፍጠር አለበት ።

ነገር ግን እኛ ሶሻሊዝምን ከከዱ ጋር ተለይተን ከእ
ነዚህ የታጠቀው ወዛደር ራሱ ገዥ ይሆን ዘንድ አሮ
ጌው የመንግስት መሳሪያ በፍፁም እንዲደመሰስ
እንታገላለን ። እነዚህ በጣም የተለያዩ ሁለት ነገሮች
ናቸው ።

ካውትስኪ « በመንግስት ውስጥ የሀይል ሚዛን
ለማዘዋወር » « ከሚሹ የፓርላማውን ከፍተኛ
ድምፅ ለማሸነፍ » ከሚፈልጉና ፓርላማውን ወደ
«አገዛዙ አዛዥነት» ለመለወጥ ከሚወዱ ከእነ ሌጂን ፡



ዴቢድ ፡ ፕሌካኖብ ፓትሬስብ ፡ ፅሬቴሊ ፡ እና ቼር
ንብስ ጋር መልካም ወዳጅነትን ለማድረግ ይችላል ።
ይኸውም በአድርባዮች ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ማን
ኛውንም ነገር በቡርዧው የፓርላማ ሪፐብሊክ ቁጥጥር
ስር የሚያመጣ አላማ ነውና ።

ነገር ግን እኛ በጠቅላላው ከእነዚህ ከአድርባዮች እን
ገነጠላለን ። በትግሉ የነቃው ወዛደር ከእኛ ጐን ይሰ
ለፋል ። ይኸውም « የሀይል ሚዛን ለማዘዋወር »
ሳይሆን ፡ ቡርዧውን ለመደምሰስ ፡ የቡርዧውን ፓር
ላማዊነትን ለመደምሰስና በኮሚዩን የተመሰለ ዲሞክ
ራሲን ለመመስረት ወይም የወዛደሮችን ሶቭዬቶችና
የወታደሮችን ተወካዮች ለማቋቋም የወዛደሩን የበላይ
ገዥነት ለመመስረት ነው ።

በኢንተርናሽናል ሶሻሊዝም ውስጥ ከካውትስኪ በስ
ተቀኝ፡እንደ ሶሻሊስት ማንዚሊ[33] በጀርመን አገር(ሌጀን
ዴቪድ ፡ ኮልብ ፡ እና ሌሎችም ፡ ከእስካንድኔቪያን እስ
ታውኒንግ እና ብራንቲንግ ጭምር) ፤ በፈረንሳይና
በቤልጅየም የዠርና የቫንደርቬልድ ተከታዮች ፤ ቱራቴ
ትሬቪስና ሌሎች የኢጣሊያ ፓርቲ የቀኝ ክንፍ ተወካ
ዮች ፤ ፋብያኖችና «ኢንዲፔንዴንትስ» (በሊበራሎች[34]
ላይ ጥገኛ የሆነው የኢንዲፔንዳንት ሊበር ፓርቲ ) በእ
ንግሊዝ አገር ፤ እና ሌሎችም ይገኛሉ ። እነዚህ ሁሉ
ክቡራን በፓርላሜንታዊ አሰራር ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸ
ውና እንዲሁም በፓርቲዎች ጋዜጣ ተካፋይ የሆኑ ከመ
ሆናቸውም ሌላ የወዛደሩን የበላይ ገዥነት የሚቃወ
ሙና ግልፅ የሆነ አድርባይነት የሚያሳዩ ናቸው ።
በእነኝህ ክቡራን አይን የወዛደሩ « የበላይ ገዥነት »
ዲሞክራሲን ይፃረራል ! ! በእነኝህና በንኡስ ከበርቴ
ዲሞክራቶች በእርግጥ ምንም ልዩነት የለም ።

ይህንን ሁኔታ በማሰብ የእርሱ ተወካዮች የሆኑትንም እና ብዙ ባለስልጣኖችንም ስናይ ፥ ሁለተኛው ኢንተርናሽናል ወደ አድርባይነት እንደሰጠመ እንረዳለን ። የኮሚዩኑ ልምድ መረሳቱ ብቻ ሳይሆን ተጣሟል ።

የወታደር ሀይል ያላቸው መንግስታት በኢምፔሪያሊስት ፉክክር ምክንያት በተፋፋመበት ወቅት በወታደር ኃይል እጅግ በጣም ትልቅ በሆነበትና የትኛው ፋናንስ ካፒታል እንግሊዝ ወይስ ጀርመን አለምን ይግዛ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን በሚያወድሙበት ጊዜ የወዛደሩ አብዮት ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጣመምና ጥያቄው እንዳይነሳ ማድረግ ትልቅ ሚና መጫወቱ አይጠረጠርም ።

የወዛደሩ አብዮት ከመንግስቱ ጋር ያለውን ግንኙነት በማጣመምና ጥያቄውም እንዳይነሳ የወታደር ሃይል ያላቸው መንግስት ወደ ኢምፔሪያሊስት ውድድር እንደ ገቡና በወታደር ሃይል አስፈሪ በመሆን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን በማውደም የፋናንስ ካፒታል—ማለትም እንግሊዝና ወይም ጀርመን—ዓለምን እንድትገዛ ለማድረግ ምክንያት ሆነ ። *

## ምዕራፍ 7

## የ1905 እና 1917 የሩሲያ አብዮት ልምድ

በዚህ ምዕራፍ ርእሰ ስር የተጠቀሰው ጉዳይ ሰፊ በመሆኑ ብዙ ቅፆች ሊፃፍበት ይቻላል ። ለአሁኑ ፅሁፋችን ወደዋና ዋና ተግባራዊ ትምህርቶች ላይ በማተኮር ፥ በቀጥታ የወዛደሩን አብዮት በመንግስት ስልጣን ጋር ያለውን ግንኙነት በሚነኩት ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን ። (እዚህላይ ፅሁፉ ያበቃል ፤ አዘጋጅ)

* የእጅ ፅሁፍ (ረቂቅ) እንደሚከተለው ይቀጥላል ።



## ለመጀመሪያው እትም ተጨማሪ ማስታወሻ

ይህች ፅሁፍ የተፃፈችው በነሐሴና መስከረም 1917 ነው ። « 1905ና የ1917 የሩሲያ አብዮት ልምድ » የሚለውን የዚህን ፅሁፍ ተከታይ ሰባተኛ ምእራፍ ለመፃፍ አቅጄ ነበር ። ግን ከአርእስቱ በስተቀር ከምእራፍ አንዲት መስመር እንኳን ለመፃፍ ጊዜ ሳላገኝ በጥቅምቱ 1917 አብዮት ዋዜማ በነበረው የፖለቲካ ውዝግብ «ተደናቀፍኩ»። እንዲህ አይነቱ «መደናቀፍ» እንኳ መልካም ነው ። ግን የዚች ፅሁፍ ሁለተኛ ክፍል (1905ና 1917 የሩሲያ አብዮት ልምድ) መፃፍ ለረጅም ጊዜ ሳይዘገይ አይቀርም ። ስለ አብዮቱ ከመፃፍ ይልቅ « የአብዮቱን ልምድ » ማግኘቱ ይበልጥ ጠቃሚና አስደሳችም ነው ።

ፔትሮግራድ
ህዳር 30፡1917

ደራሲው

* * *

## መግለጫዎች

1. ሌኒን በ1917 በነሀሴና መስከረም ውስጥ ተደብቆ ሳለ መንግስትና አብዮት የምትለዋን መፅሀፍ ፃፈ ። ስለ መንግስት ቲዎሪያዊ ስራ እንደሚያስፈልግ ሌኒን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1916 ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ተናግሯል ። በዚያን ጊዜ ነው «ወጣቱ ኢንተርናሽል» (ጠቅላላ ስራዎች 4ኛ የሩሲያ እትምቅፅ 23 ፥ ገፅ 153—56 ተመልከቱ) የሚለውን ማስታወሻ በመፃፍ ቡካሪን ስለ መንግስት ያለውን ፀረ ማርክሲት አቋም በማጋለጥ ማርክሲስቶች መንግስትን እንዴት እንደሚመለከቱት ሰፋ ያለ ፅሁፍ ለማቅረብ ቃል የገባው ። በታህሳስ 17፡1917 ለኤ. ኤም ኩለንታይ

በፃፈው ደብዳቤ ስለመንግስት የማርክሲስቶች አስተያየት የሚለውን ፅሁፍ ለመጨረስ የተቃረበ መሆኑን ገልጿል ። ይህች ፅሁፍ ሰማያዊ ሽፋን ባላት ማስታወሻ ደብተር በእጅ የተፃፈችና « ማርክሲዝም ስለ መንግስት» የሚል ርእስ ነበራት ። በውስጧም ከማርክስና ኤንግልስ የተወሰዱ ጥቅሶችና ከካውትስኪ ፣ ፓንኮይክና በርንስታይን የተወሰዱ ሀሳቦችና የሌኒን ሂሶች ፣ መደምደሚያና ማጠቃለያ ሀሳቦች ነበሩበት ።

በንድፉ መሰረት መንግስትና አብዮት ሰባት ምእራፍ ሊኖራት ነበር ፣ ግን ሰባተኛውና የመጨረሻው ምእራፍ « 1905ና 1917 የሩሲያ አብዮት ልምድ » የሚለው ሳይፃፍ ቀርቷል ፤ በእጃችን ያለው ግን ዝርዝር ንድፉ ብቻ ነው ። (ሌኒን ጥቃቅን ፅሁፎች ሩሲያ እትም ቅፅ 21,1933 ፣ ገፅ 25—26 ይመልከቱ) የመፅሀፉን መታተም አስመልክቶ ሌኒን ለአሳታሚው በፃፈው ማስታወሻ « ሰባተኛውን ምእራፍ ለመፃፍ ብዙ ጊዜ ከወሰደበት ወይም በጣም ከበዛ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ምእራፎች እንደ ክፍል አንድ ይታተሙ» ብሎአል ።

በረቂቁ መጀመሪያ ገፅ ላይ የመፅሀፉ ደራሲ ኤፍ ኤፍ ፣ ኢባኖብስኪ በሚል የብእርስም ተጠቅሟል ። ሌኒን በዚህ ስም የተጠቀመበት ምክንያት ጊዜያዊ አብዮታዊው መንግስት መፅሀፉን እንዳይወርስበት ነበር መፅሀፉ በብእር ስም መጠቀም እስከማያስፈልግበት ፣ እስከ 1918 ድረስ አልታተመችም ነበር ። ሁለተኛው እትም «በ1852 በማርክስ የጥያቄው አቀራረብ» የሚለው አዲስ ክፍል በሁለተኛው ምእራፍ ላይ በ1919 በሌኒን ተጨምሯል ።



2. ፋብያናውያን — በ1884 የተቋቋመው የብሪታኒያ ቡርዧ ምሁራን ቡድን አድርባይና ጥገናዊ የነበረ ነው። ማህበሩ የሩሲያን ማህበር አባላት ናቸው ። መጠሪያ ስሙን የወሰደው ታክቲኮችን በማዘግየትና ድል የሚገኝባቸውን ጦርነቶች ችላ በማለት ዝናን ካተረፈው ከሮማዊው ጄኔራል ፋቢየስ ኮንክታቶር (« አዘግይ ») ነው ። የፋቢያን ማህበር የሚቆመው ሌኒን እንደገለፀው « ለመጨረሻው የአድርባይነትና ለሊበራል ሌበር ፖለቲካ መግለጫ ነው ። » ፋቢያኖች ወዛደሩን ከመደብ ትግል አቅጣጫ ለማሳየት በመፈለግ በሰላማዊና ዝግ ባለ ጥገናዊ ለውጥ ህብረተሰባዊነት ሊገኝ መቻሉን ይሰብኩ ነበር ። በኢምፔሪያሊስቱ የአለምም ጦርነት (1914—18) ጊዜ ፋቢያውያን የሶሻል ትምክህተኝነት አቋም ወስደዋል ። ስለ ፋቢያውያን ባህሪ በይበልጥ ለመረዳት የሌኒን «የጄ. ኤፍ ቤከር ፣ ጄ. ዲትስገን ፣ ኤፍ ኤንግልስ ፣ ኬ. ማርክስና ሌሎችም የተፃፈ ደብዳቤዎች የሩሲያ እትም መቅድም ይመልከቱ (ቪ. አይ ሌኒን ፣ ማርክስ ኤንግልስ ማርክሲዝም ሞስኰ 1953 ገፅ 245—56) በሩሲያ አብዮት ውስጥ የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ የእርሻ ፕሮግራም » (ጠቅላላ ስራዎች 4ኛ የሩሲያ እትም ቅፅ 15 ፤ ገፅ 154) እና « የእንግሊዞች ጭፍን ሰላም ወዳድነትና የእንግሊዞች የቲዎሪ ጥላቻ » (ከበፊቱ ቅፅ 2 ፣ ገፅ 234) (ገፅ 2)

3. የፍሬዴሪክ ኤንግልስን « የቤተሰብ የግል ንብረትና የመንግስት አመጣጥ » ይመልከቱ (ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክስ ኤንግልስ ምርጥ ስራዎች እንግሊዝኛ እትም ፣ ሞስኮ 1951 ፣ ቅፅ 2 ፣ ገፅ

288—89) ዝቅ ብሎ በገፅ 11 12 ፣ እና 14-19 ፣ ሌኒን ከዚሁ መፅሀፍ ይጠቅሳል (ከበፊቱ ገፅ 289—92) (ገፅ 7)

4. ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፀረ ዱሪንግ ፣ እንግሊዝኛ እትም ፣ ሞስኮ 1947 ፣ ገፅ 416—17 ይመልከቱ ዝቅ ብሎ በዚህ ፅሁፍ ገፅ—ላይ ሌኒን እንደገና ከዚሁ ከኤንግልስ መፅሀፍ ይጠቅሳል ። (ከበፊቱ ገፅ 275) (ገፅ 22)
5. ካርል ማርክስ « የፍልስፍና ድህነት » እንግሊዝኛ እትም ሞስኮ ገፅ 24 ይመልከቱ (ገፅ 29)
6. ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ « የኮሚዩኒስት ፓርቲ ማኒፌስቶ » (ምርጥ ሰራዎች እንግሊዝኛ እትም ሞስኮ 1951 ፣ ቅፅ ፣ 1 ፣ ገፅ 32—61) ይመልከቱ ። (ገፅ 29)
7. ካርል ማርክስ « የጉታ ፕሮግራም ሂስ » (ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ምርጥ ስራዎች እንግሊዝኛ እትም ሞስኮ 1951 ፣ ቅፅ 2 ፣ ገፅ 13—45) ይመልከቱ

የጉታ ፕሮግራም በፊት ሁለት ተነጣጥለው የነበሩት የጀርመን ሶሻሊስት ፓርቲዎች አይዘናውያንና ለስላውያን አንድ ሁነው የጀርመን ሶሻሊስት ወዛደሮች ፓርቲን በ1875 ሲመሰርቱ በጐታ ኰንግሬስ የተቀመጠ ፕሮግራም ነው ። ፕሮግራሙ ፍፁም አድርባይ ነበር ። ምክንያቱም አይዘናውያን ከላስላውያን ጋር በዋና ዋና ነጥቦች ላይ ተስማምተው የለስላውያንን ፎርሙላ ተቀብለው ነበረ ። ማርክስና ኤንግልስ ይህን ፕሮግራም አጋልጠው ነቅፈውታል ። (ገፅ 29)

8. ካርል ማርክስ «የፍልስፍና ድህነት» እንግሊዝኛ እትም ሞስኮ ገፅ 174 ይመልከቱ ። (ገፅ 30)



9. ካርል ማርክስና ፍሬደሪክ ኤንግልስ ኰሚዩኒስት ፓርቲ ማኒፌስቶ» ምርጥ ሰዎች ፣ እንግሊዝኛ እትም ፣ ሞስኮ 1951 ፣ ቅፅ 1 ፣ ገፅ 43 እና 50) ይመልከቱ ። (ገፅ 31)
10. ካርል ማርክስ «የሉዊ ቦናፓርት 18ኛው ብሩሜይር » (ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፣ ምርጥ ስራዎች እንግሊዝኛ እትም ሞስኮ 1951 ቅፅ 1 ፣ ገፅ 301 ) ይመልከቱ ።

ዝቅ ብሎበዚህ መፅሀፍ ገፅ 37 ሌኒን ለተጠቀሰው መፅሀፍ ኤንግልስ ለ3ኛው የጀርመን እትም ከፃፈው መግቢያ ይጠቅሳል ። (ገፅ 38)

11. ዲኖይሳይት 1883 እስከ 1923 ድረስ በስቱ ትጋርት እየታተመ ይወጣ የነበረ የጀርመን ሶሻል ዲሞክራሲ መፅሄት ። በ1885—95 መፅሄቱ ጥቂት የኤንግልስ ስራዎችን አውጥቷል ። ኤንግልስ ብዙ ጊዜ ለአሳታሚው (አዘጋጅ) ምክር በመለገስና ከማርክሲዝም እየራቁ መሄዳቸውን አጥብቆ ነቅፏል ። በአስራዘጠነኛው ምእት አመት ሁለተኛው አጋማሽ ከኤንግልስ ሞት በኋላ መፅሄቱ በዘዴ የተቀልባሾችን ፅሁፍ ማውጣት ያዘ ። በመጀመሪያ የኢምፔሪያሊዝም ጦርነት ጊዜ የካውትስካውያንን የመሀል ሰፋሪ አቋም በመውሰድ ሶሻል ትምክህተኝነትን ደገፍዋል ። (ገፅ 45)
12. የካርል ማርክስና የፍሬዴሪክ ኤንግልስን ፣ ምርጥ ስራዎች እንግሊዝኛ እትም ፣ ኤፍ.ኤል.ፒ.ኤች. ሞስኮ ፣ 1951፣ ቅፅ 2 ገፅ 410 ። (ገፅ 46)

13. የካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስን ፣ ምርጥ ስራዎች እንግሊዝኛ እትም ፡ ኤፍ. ኤል. ፒ. ኤች. ሞስኰ ቅፅ 11 ገፅ 420 ይመልከቱ ። (ገፅ 51)

14. ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ፤ ምርጥ ስራዎች « የኰሚዩኒስት ፓርቲ ማኒፌስቶ » ኤፍ. ኤል. ፒ. ፔኪን 1975 ፡ ገፅ 2 ፡ (ገፅ 50)

15. የቪ. አይ. ሌኒን ፡ ሥራዎች 4ኛ የሩሲያ እትም ፡ ሞስኰ ፡ 1951 ፡ ቅፅ 12 ፡ ገፅ 83—91 ፡ ገፅ 52

16. ካርል ማርክስ « የርስ በርስ ጦርነት በፈረንሳይ » ኤፍ. ኤል. ፒ. ፔኪንግ 1974 ገፅ 68-69 ዝቅ ብሎ በዚህ መፅሀፍ ገፅ 54, 55, 62, እና 66-67 ላይ ሌኒን እንደገና ከዚህ ከማርክስ ፅሁፍ ይጠቅሳል ። (ከበፊቱ ገፅ 72, 68,69-70 እና 71-73 ፡ ገፅ 58

17. ይህ የማርክስ አንቀፅ በሌኒን የተጠቀሰው «የርስ በርስ ጦርነት በፈረንሳይ» የሚለው የጀርመን እትም ከዋናው የእንግሊዝኛ ኰፒ መጠነኛ ልዩነት አለው ። (ገፅ 62)

18. የፍሬዴሪክ ኤንግልስ፡የመኖሪያ ቤት ጥያቄ፡ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ምርጥ ሥራዎች እንግሊዝኛ እትም ፡ ኤፍ. ኤል. ፒ. ኤች. ሞስኮ 1951 ቅፅ ፡ 1 ገፅ 517—18 ይመልከቱ ፤ እታች በዚህ መፅሀፍ ገፅ 71 እና 72 ላይ ሌኒን እንደ ገና ከዚሁ ከኤንግልስ መፅሀፍ (ስራ) ይጠቅሳል ) ከበፊቱ ገፅ 569 እና 555) (ገፅ 80)

19. ሌኒን እዚህ ላይ በሚጠቅሰው የማርክስን ፅሁፍ « ፖለቲካል ኤንዲፈረንቲዝም » ( ፖለቲካዊ ገለልተኛነት ) የሚለውን ነው ። (ካርል ማር



ክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ስራዎች ፡ ጀርመን እትም ፡ በርሊን ፡ 1962 ቅፅ 18 ፡ ገፅ 299—304 እና የኤንግልስ ስለ « ስልጣን » ( ካርል ማር ክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፡ ምርጥ ስራዎች ኤፍ. ኤል. ፒ. ኤች. መስኮ 1951 ፡ ቅፅ 1 ገፅ 575—78) እታች በዚህ መፅሀፍ ገፅ 73 እና 74-76 ሌኒን ከዚሁ ፅሁፍ ይጠቅሳል ።

(ገፅ 83)

20. ካርል ማርክስ « የጐታ ፕሮግራም ሂስ » ኤፍ. ኤል. ፒ. ፔኪንግ 1972 ፡ ገፅ 42-43

(ገፅ 90)

21. የኤርፈርት ፕሮግራም የ1875ቱ የጐታ ፕሮግራም ለመተካት ፡ በጥቅምት 1891 በኤርፈትኰንግረስ የተ ቀመረ የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ፕሮ ግራም ነው ። በኤርፈርት ፕሮግራም ውስጥ የሚገኙት ስህተቶች በኤንግልስ « በ1891 የጀርመን ሶሻል ዲሞ ክራቲክ ንድፍ ፕሮግራም ላይ ሂስ » በሚለው ፅሁፍ ተንቅፍዋል ። (ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ስራዎች ፡ የጀርመን እትም ፡ በርሊን ፡ 1963 ቅፅ 22 ፡ ገፅ 225—40)

(ገፅ 93)

እታች በዚህ መፅሀፍ ገፅ 82-89 ሌኒን ይህንኑ የኤን ግልስን ስራ ይጠቅሳል (ከበፊቱ ገፅ 232 — 37)

22. የቪ. አይ. ሌኒን «የመርህ ጥያቄ» ። የሌኒን ስራዎች ፡ 4ኛ የሩሲያ እትም ሞስኰ ቅፅ 24 ፡ ገፅ 497-99 ገፅ 102 (ገፅ 102)

23. እዚህ ላይ የተጠቀሰው ኤንግልስ ለማርክስ «የርስ በርስ ጦርነት በፈረንሣይ» ኤፍ. ኤል. ፒ. ፔኪንግ 1974 ገፅ 1-18 ከፃፈው መቅድም ነው ። (ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፣ ምርጥ ስራዎች ፣ እንግሊዝኛ እትም ፣ ሞስኮ ፣ 1951 ፣ ቅፅ 1 ፣ ገፅ 429—40)

እታች በዚህ መፅሀፍ ገፅ 90-91 እና 92-96 ሌኒን እንደገና ከዚሁ ከኤንግልስ ስራ ይጠቅሳል (ከበፊቱ ፣ ገፅ 3-4,10 እና 15-17 )

(ገፅ 103)

24. ካቬኛክ ሉዊ ዮጂን—የፈረንሳይ ጄኔራል እና ፀረ-አብዮት የነበረ ከግንቦት 1848 አብዮት በኋላ የጦር ሚኒስቴር ሆኖ በ1848 የሰኔ ቀናት ጊዜ የፓሪስ ወዛደሮችን ንቅናቄ በተለዬ ጭካኔ ያፈነ ።

25. ስለ አለም አቀፍ አርእስቶች ከ «የህዝቡ መንግስት»

(ገፅ 112)

26. ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፣ «ፎርቮርት ሱር ብሮሺውር ኢንተርናዮናል አውስዴም ፎክስሽታት»(1871-75) ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ጠቅላላ ስራዎች ጀርመን እትም ፣ በርሊን 1963 ቅፅ 2 ፣ 417—18)

(ገፅ 112)

27. « ብዙሀን » በሩሲያ ቋንቋ « ቦልሺንስቶቮ » ስለዚህም « ቮልሼቪክ » የሚለው ስም ነው ።

(ገፅ 113)

28. ካርል ማርክስ « የጐታ ፕሮግራም ሂስ » (ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ፣ ምርጥ ስራዎች

(ገፅ 118)



29. ሌኒን የሚጠቅሰው የሩሲያ የቡርዧ ኤኮኖሚስት የሆነውን ቱጋን ባራኖብስኪን ነው ።

(ገፅ 129)

30. በሄግ የመጀመሪያው ኢንተርናሽናል ኰንግሬስ በመስከረም 2—7፣1872 ተደረገ ። ስብሰባውን የተካፈሉት መልእክተኞች 65 ነበሩ ። ከነሱም መሀል ማርክስና ኤንግልስ ይገኙ ነበር ። ከብዙ ጉዳዮች መሀል የሚከተሉት ፣ በስብሰባው አጀንዳ ቀርበው ነበር ።

1. የጠቅላላው ሸንጐ ስልጣን 2. የወዛደሩ የፖለቲካ ተግባር ። ኰንግረሱ በሚካሄድበት ጊዜ ከቡካኒን ስቶች ጋር ጠንካራ ትግል ተደርጓል ። ኰንግሬሱ የጠቅላላውን ሸንጐ ስልጣን ለማስፋፋት ወስኗል ። « የወዛደሩን የፖለቲካ ተግባር » ሲያትት ፣ ወዛደሩ የማኅበራዊ አብዮትን ድል ለማረጋገጥና የሱም ታላቁ ተግባር የፖለቲካ ስልጣንን መቀዳጀት ስለሆነ የራሱ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ማደራጀት እንዳለበት ገልጿል ። ኰንግሬሱ ቡካኒንና ጉዬሚን እንደ ፀረ ድርጅትና እንደ ፀረ ወዛደር ፓርቲ መስራቾች በመቁጠር ከመጀመሪያው ኢንተርናሽናል አስወጥቷቸዋል ።

(ገፅ 144)

31. ዛሪያ (ጐህ) 1901 — 02 በኤስክራ አዘጋጆች በስቱት ጋርት እየታተመ ይወጣ የነበር የሳይንሳዊ ፖለቲካዊ ማርክሲስት መፅሄት ። አራት እትሞች ሶስት ጊዜ ይዞ ወጥቶአል ። (የአንደኛው እትም ቁጥር ተደግሞአል ። የሚከተሉት የሌኒን ፅሁፎች በዛሪያ ወጥተዋል ። «ቀላል ማስታወሻዎች» የዚምስቶብ አስጨናቂዎችና የሊብራሊዝም ሀኒባሎች » ፣ የእርሻ

ጥያቄና የማርክስ ቲዎች ከሚለው የመጀመሪያዎች አራት ምእራፎች፥) « ክቡራን የእርሻን ጥያቄ ተቺዎች» በሚል ርእሰ ስር)፥ « የውስጥ ጉዳዮችን ምርመራ » እና « የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራሲ የእርሻ ፕሮግራም »

(ገፅ 146)

32. ይህ የሚያመለክተው ከመስከረም 23 እስከ 27 በፓሪስ የተደረገውን የሁለተኛው አለም አቀፍ አምስተኛውን አለም አቀፍ ኮንግሬስ ነው ። በዋናው ጥያቄ ፥ በወዛደሩ ስልጣን መቀዳጀት ላይ የኮንግሬሱ ብዙሀን በካውትስኪ የቀረበውንና ሌኒንም « ከአድርባዮች ጋሪ አስ ማሚ ነው » ያለውን ውሳኔ አሳልፈዋል ። ከውሳኔዎች ውስጥ የሁሉም አገር ሶሻሊስት ፓርቲዎች ተወካዮች የሚገኙበት ፅህፈት ቤቱ በብረ ስለስ የሆነ አንድ አለም አቀፍ ሶሻሊስት ቢሮ ለማቋቋም ወስኗል ።

(ገፅ 146)

33. በሶሻሊስት መንዝሊ (ሶሻሊስቲሽ ሞናትሼፍት) በጀርመን ሶሻል ዲሞክራት ፓርቲ ውስጥ ለነበሩት አድርባዮችና የዓለም አቀፍ አድርባይነት ዋና ጋዜጣ ። 1897 እስከ 1933 በበርሊን ይታተም ነበር ። በ1914—18 የኢምፔሪያሊስቱ አለም ጦርነት ጊዜ የሶሻል ትምክህተኝነትን አቋም ወስደዋል ።

(ገፅ 167)

34. ነፃ የወዛደር ፓርቲ በ1893 የተመሰረተና በጀምስ ኬር ሀርዴ ፥ በጄ. ራምሳይ ማክዶላንድና በሌሎችም የሚመራ ፓርቲ ነበር ። ከቡርዧው የፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃ ነኝ ይል ነበር ፥ በእርግጥ ግን « ከሶሻሊዝም



ነፃና ግን በሊብራሊዝምነት ላይ ፥ ጥገኛ ነበር » (ሌኒን) በ1914 — 18 በኢምፔሪያሊስት የአለም ጦርነት መጀመሪያ ላይ ፥ በነሐሴ 13፥1914 ጦርነቱን በመቃወም መግለጫ አውጥቶ ነበር ። ግን በኋላ የካቲት 1915 በሎንደን በተደረገው የተባበሩት የሶሻሊስት ስብሰባ ተወካዮች በስብሰባው የተወሰደውን ሶሻል ትምክህተኝነት አቋም ደግፈዋል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነፃ ወዛደር ፓርቲ መሪዎች በጭፍን ሰላማዊ ሀረጎች ከለላ የሶሻል ትምክህተኝነት አቋም ወስደዋል ። በ1919 የኮሚዩኒስት ኢንተርናሽናል (ሶስተኛው ኢንተርናሽናል ተርጓሚ ( በተቋቋመበት ጊዜ የነ. ወ. ፓ. መሪዎች ወደ ግራ በተነሱት አባሎች በመገደድ ከሁለተኛው አለም አቀፍ እንዲወጡ ወስነዋል ። በ1921 ነ. ወ.ፓ ራሱን ሁለት ተኩልኛ አለም አቀፍ ብሎ በሰየመው ድርጅት ውስጥ ገባ ። ድርጅቱ ሲወድቅ ወደ ሁለተኛው አለም አቀፍ ተመለሰ ።

(ገፅ 167)

## ይ ዘ ት


ለመጀመሪያ እትም መግቢያ ... ... ... ... 1
ለሁለተኛው እትም መግቢያ ... ... ... ... 4

ምእራፍ 1

የመደብ ህብረተሰብና መንግስት ... ... ... 5
1. መንግስት እንደ የማይታረቁ የመደብ ቅራኔዎች ውጤት ... ... ... ... ... 5
2. የታጠቁ ሰዎች እስር ቤቶች ወዘተ የተለዩ አካሎች ... ... ... ... ... 10
3. መንግስት—እንደየጭቁን መደብ መበዝበዣ መሳሪያ ... ... ... ... ... ... 14
4. የመንግስት «መመንመንና መጥፋት» እና በሀይል ላይ የተመሰረተ አብዮት ... ... 20

ምእራፍ 2

መንግስትና አብዮት የ1848—51 ልምድ ... ... 30
1. የአብዮቱ ዋዜማ ... ... ... ... ... 30
2. አብዮት ሲጠቃለል ... ... ... ... 36
3. የጥየቄው አቀራረብ በማርክስ በ1852 ... 45

ምእራፍ 3

የ1871 የፓሪስ ኰሚዩን ልምድ የማርክስ ትንተና 49
1. የኰሚዩናርዶች ሙከራ ጀግንነቱ ከምን ላይ ነው ያለው ? ... ... ... ... ... 49
2. የተንኰታኰተው የመንግስት መሳሪያ በምንድን ነው የሚተካው ? ... ... ... 55
3. ፓርላሚንታዊነትን ማስወገድ ... ... 62
4. የብሄሩን አንድነት ማደራጀት ... ... 70
5. ተውሳክ የሆነውን መንግስት ማውደም ... 75





ምእራፍ 4

ተከታታይ ፤ ተጨማሪ ማብራሪያ በኤንግልስ ... 79
1. የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ... ... ... ... 79
2. ከአናርኪስቶች ጋር የተደረገ ክርክር ... 83
3. ደብዳቤ ለቤብል ... ... ... ... ... 89
4. በኤርፉርት ፕሮግራም ረቂቅ ላይ የቀረበ ሂስ 93
5. ለማርክስ የፈረንሳይ የርስ በርስ ጦርነት ። የ1891 መቅድም ... ... ... ... ... 103
6. ኤንግልስ ዲሞክራሲን ስለማስወገድ ... 111

ምእራፍ 5

ለመንግስት መመንመን ኢኮኖሚ መሰረት ... 115
1. በማርክስ የጉዳዩ አቀራረብ ... ... ... 115
2. ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚኒዝም ሽግግር ... 119
3. የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ የመጀመሪያው ደረጃው ... ... ... ... ... ... 126
4. የኮሚዩኒስት ህብረተሰብ ከፍቱኛ ደረጃ 132

ምእራፍ 6

ማርክሲዝም በአድርባዮች ሲበረዝ ... ... ... 142
1. የፕሌካኖብ ክርክር ከስርአተ አልበኞች ጋር ... ... ... ... ... ... ... ... ... 143
2. የካውትስኪ ክርክር ከአድርባዮች ጋር ... 145
3. የካውትስኪ ክርክር ከፓኒክኮ ጋር ... 156
... ... ... ... 168
ምዕራፍ 7. ... ... ... ... 169
ለመጀመሪያው እትም ተጨማሪ ማስታወሻ ... 169
... ... ... ... ...
መግለጫዎች ... ...

ንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ

ዋጋው ሁለት ብር ብቻ